بسم الله الرحمن الرحيم

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና አዛኝ በሆነው፡፡

ለአለማቱ ጌታ ምስጋና የተገባ ይሁን፡፡ ሰላትና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን፡፡

የአለም አፈጣር እና ስር መሰረቱ የሰውን ልጅ በተለይም ሙስሊም ያልሆነውን ክፍል ከድሮ ጀምሮ የሚያወዛግብ እና አእምሮ የሚያናውዝ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ርዕሱ ለሙስሊም ግልፅ በመሆኑ ነው፡፡ ኢስላም ከመጣ ጀምሮ የሰዎችን ማብራሪያ በማይፈልግ መልኩና ግልፅ በሆነ መልኩ አስቀምጦታል፡፡ በመሆኑም ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች የሚዳክሩበት የውዝግብ፣ የመላምት እና የግራ መጋባት ኑሮ ሙስሊሞች ሲኖሩት አትመለከትም፡፡ ዘሬ አንድ መላምት ላይ ቢደርሱ ነገ ሌላ መላምት መጥቶ የበፊቱን ያስዋሻል፡፡ በተቃኒው ደግሞ እኛ ሙስሊሞች ቁርአን እና ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጡትን ማብራሪያ እና ገለፃ እውነተኛ ስለመሆኑ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች እና አማኞች ነን፡፡ እነሱ የገለጹትን እውነታ እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ የማንኛውም ተመራማሪ መላምት ሊያስዋሸው ቀርቶ አስተያየት ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ምክንያቱም እነሱን በመቃረን የተነሳ አስተሳሰብ በሙሉ ከመለኮታዊው እውነታ ስር የውርደት ካባን ተከናንቦ በአፉ ይደፋል፡፡

የሚታየውንም ሆነ የማይታየውን የዚህ ዓለም ክፍል ፈጣሪው አላህ (ሰ.ዐ.ወ) ነው፡፡ አላህ (ሰ.ወ) ከማንኛውም ፍጡር የተብቃቃ ሲሆን ፍጡረን በሙሉ ደግሞ ወደ አላህ ከጃዮች እና ለማኖች ናቸው፡፡

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

يَا أَيُّهَا النَّاسُ أَنتُمُ الْفُقَرَاءُ إِلَى اللَّهِ ۖ وَاللَّهُ هُوَ الْغَنِيُّ الْحَمِيدُ [٣٥:١٥]إِن يَشَأْ يُذْهِبْكُمْ وَيَأْتِ بِخَلْقٍ جَدِيدٍ [٣٥:١٦]وَمَا ذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ بِعَزِيزٍ [٣٥:١٧]

«እናንተ ሰዎች ሆይ! እናንተ (ሁል ጊዜ) ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ፡፡ አላህም እርሱ ተብቃቂው ምስጉኑ ነው፡፡ ቢሻ ያስወግዳችኋል፡፡ አዲስንም ፍጡር ያመጣል፡፡ ይህም በአላህ ላይ ምንም አስቸጋሪ አይደለም፡፡»

በእምነት እና በምትሰራው በጎ ሥራዎች ተጠቃሚው እራስህ ብቻ ነህ፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ

إِن تَكْفُرُوا فَإِنَّ اللَّهَ غَنِيٌّ عَنكُمْ ۖ وَلَا يَرْضَىٰ لِعِبَادِهِ الْكُفْرَ ۖ وَإِن تَشْكُرُوا يَرْضَهُ

لَكُمْ ۚ

«ብትክዱ አላህ ከእናንተ የተብቃቃ ነው፡፡ ለባሪያዎቹም ክህደትን አይወድም፡፡ ብታመሰግኑም፤ እርሱን ይወድላችኋል፡፡»

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ በሀዲሰል ቁድስ እንዲህ ይላል፡- ባሮቼ ሆይ እኔ በራሴ ላይ በደልን እርም አድርጌያለሁ፡፡ በናንተ መካከልም እንዲሁ፡፡ አንዱ አንዱን አይበድል፡፡ ባሮቼ ሆይ ሁላችሁም መንገድ የሳታችሁ ናችሁ እኔ የመራሁት ሲቀር፡፡ ቅናቻውን መንገድ ምራን በሉ እመራችኋላሁ፡፡ ባሮቼ ሆይ ሁላችሁም የተራባችሁ ናችሁ እኔ ያበላሁት ሲቀር፡፡ አብላኝ በሉ አበላችኋለሁ፡፡ ባሮቼ ሆይ ሁላችሁም የታረዛችሁ ናችሁ እኔያለበስኩት ሲቀር፡፡ አልብሰኝ በሉ አለብሳችኋለሁ፡፡ ባሮቼ ሆይ እናንተ ቀን ከሌት ትወነጀላላችሁ እኔ ደግሞ ወንጀልን በሙሉ መሀሪ ነኝ፡፡ ማረኝ በሉኝ እምራችሁ ዘንድ፡፡ ባሮቼ ሆይ እናንተ እኔን ለመጉዳትም ሆነ ለመጠቀም አትችሉም፡፡ ባሮቼ ሆይ ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ መጨረሻ ለ ሰው እንዲሁም እንዲሁም አጋንንት ሁሉ ልክ አላህን በጣም እንደሚፈራ ሰው ቢሆኑ ከንግስናዬ ላይ ቅንጣት ያህል እንኳ አይጨምርም፡፡ ባሪቼ ሆይ ከመጀመሪ አሰውአንስቶ እስከመጨረሻ ያለ ሰው እንዲሁም አጋንንት ሁሉ በአንድ ሜዳ ላይ ቆመው ቢጠይቁኝ እና ለሁሉም የጥያቄውን ብሰጥ መርፌ ውቅያኖስ ውስት ገብታ ስትወጣ የምትቀንሰውን ያህል ቢሆን እንጂ እኔ ጋር ካለው የሚቀንስ አይደለም፡፡ ባሮቼ ሆይ ነገር ግን የምቆጥርላችሁ የሰራችሁትን ነው፡፡ ከዛም እንደየስራችሁ እመነዳችኋለሁ፡፡ ጥሩን ነገር ያገኘ ሰው አላህን ያመስግን፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ያገኘ ሰው ራሱን እንጂ ሌላን እንዳይወቅስ፡፡

ኢስላም ማለት አላህ (ሱ.ወ) ለባሮቹ ወዶት የመረጠላቸው ሀይማኖት እና የሕይወት መንገድ ነው፡፡ ሰዎች ሀሳቦቻቸው፣ የግልም ሆነ ማህበራዊ ኑሮዋቸው፣ እንዲሁም ውጪያዊም ሆነ ውስጣዊ ህይወታቸው፣ እንዲስተካከል ይህ ሀይማኖት በጣም ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህ ሀይማኖት እኮ ለመሠረታዊ ጉዳዮች በጣም ትልቅ ትኩረት እየሰጠ ቅርንጫፋዊ ነገራቶችን የማይንቅ እንዲሁም በመንፈሳዊ እና አካላዊ የህይወት መስመር መሀል ያመዛዘነ ነው፡፡ አንድ ሰው ህን ሀይማኖት አጥብቆ ከያዘ በዚህ አለም የመንፈስ እረፍት እና እርጋታ እንዲሁም የልብ ስክነትን በማግኘት ዘላቂ ደስታን ይጎናጸፋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

الَّذِينَ آمَنُوا وَلَمْ يَلْبِسُوا إِيمَانَهُم بِظُلْمٍ أُولَٰئِكَ لَهُمُ الْأَمْنُ وَهُم مُّهْتَدُونَ [٦:٨٢]

«እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ እነዚያ ለእነርሱ ጸጥታ አላቸው፡፡ እነሱም የተመሩ ናቸው፤

**በመጪው አለም ደግሞ የጌታን ውዴታ በማግኘት እና ጀነት ውስ ዘውታሪ በመሆን ከእድለኞች ይሆናል፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ጥበቃ ስር ይውላል፡፡»**

**አላህ ውዴታ ያገኘ ሰው መጨረሻው የአላህ ስጦታ ወደሆነው ጀነት መግባት ነው፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ كَانَتْ لَهُمْ جَنَّاتُ الْفِرْدَوْسِ نُزُلًا [١٨:١٠٧]خَالِدِينَ فِيهَا

لَا يَبْغُونَ عَنْهَا حِوَلًا [١٨:١٠٨]

«እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው፡፡ በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ከእርሷ መዛወርን የማይፈልጉ ሲኾኑ፤ (መስፈሪያቸው ነው)፡፡»

**የኢስልምናን ዲን የእለተ ትንሳኤ ቀን ድረስ በአላህ ይበቃ ስር ነው፡፡ አላህ(ሱ.ወ)እንዲህ ብሏል**

إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ [١٥:٩]

«እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡»

**ምንም እንኳን የእስልምና ጠላቶች የኢስላምን ገፅታ ለማበላሸት እና በውሸት ለማጠልሸት የተቻላቸውን ቢለፉ አላህ (ሱ.ወ) ደግሞ ስለቁርዓን እንዲህ ይላል፡-**

لَّا يَأْتِيهِ الْبَاطِلُ مِن بَيْنِ يَدَيْهِ وَلَا مِنْ خَلْفِهِ ۖ تَنزِيلٌ مِّنْ حَكِيمٍ حَمِيدٍ [٤١:٤٢]

«ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም፡፡ ጥበበኛ ምስጉን ከኾነው ጌታ የተወረደ ው፡፡»

**የሁኔታዎች ውጤት ሁልግዜም የሚሆነው የአላህ (ሱ.ወ) ፍላጎት ግልጽ መውጣት፣ የእርሱ ቃል ከፍማለት እና የእርሱ ሰራዊት ማሸነፍ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

إِنَّ الَّذِينَ يُحَادُّونَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ كُبِتُوا كَمَا كُبِتَ الَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ ۚ وَقَدْ أَنزَلْنَا آيَاتٍ

بَيِّنَاتٍ ۚ وَلِلْكَافِرِينَ عَذَابٌ مُّهِينٌ [٥٨:٥]

«ግልጾች ማስረጃዎችን ያወረድን ስንኾን እነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩ እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩት እንደተዋረዱ ይዋረዳሉ፡፡ ለከሓዲዎችም አዋራጅ ቅጣት አልላቸው፡፡»

ምንም እንኳ ጠላቶች ይህንን ሀይማኖት ለማጥፋት ላሰለሰ ጥረት ቢያደርጉም መጨረሻቸው ውርደት እና ኪሳራ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

إِنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا يُنفِقُونَ أَمْوَالَهُمْ لِيَصُدُّوا عَن سَبِيلِ اللَّهِ ۚ فَسَيُنفِقُونَهَا ثُمَّ تَكُونُ عَلَيْهِمْ حَسْرَةً ثُمَّ يُغْلَبُونَ ۗ وَالَّذِينَ كَفَرُوا إِلَىٰ جَهَنَّمَ يُحْشَرُونَ [٨:٣٦]

«እነዚያ የካዱት ከአላህ መንገድ ሊከለክሉ ገንዘቦቻቸውን ያወጣሉ፡፡ በእርግጥም ያወጡዋታል፡፡ ከዚያም በእነሱ ላይ ጸጸት ትኾንባቸዋለች፡፡ ከዚያም ይሸነፋሉ፡፡ እነዚያም የካዱት ወደ ገሀነም ይሰበሰባሉ፡፡»

የአላህ ሀይማኖት ዘውታሪ፣ ህግጋቶቹ ፀዳቂ እንዲሁም ትእዛዛቶቹ ተተግባሪ ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

يُرِيدُونَ لِيُطْفِئُوا نُورَ اللَّهِ بِأَفْوَاهِهِمْ وَاللَّهُ مُتِمُّ نُورِهِ وَلَوْ كَرِهَ الْكَافِرُونَ [٦١:٨]

«የአላህን ብርሃን በአፎቻቸው ሊያጠፉ ይሻሉ፡፡ አላህም ከሓዲዎቹ ቢጠሉም እንኳ ብርሃኑን ገላጭ ነው፡፡»

አላህ (ሱ.ወ) ሀይማኖቱን ለመርዳት እና የበላይ ለማድረግ ቃል ገብቷል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

هُوَ الَّذِي أَرْسَلَ رَسُولَهُ بِالْهُدَىٰ وَدِينِ الْحَقِّ لِيُظْهِرَهُ عَلَى الدِّينِ كُلِّهِ ۚ وَكَفَىٰ بِاللَّهِ شَهِيدًا

[٤٨:٢٨]

«እርሱ ያ መልክተኛውን በመሪ መጽሐፍና በእውነተኛ ሃይማኖት በሃይማኖት ሁሉ ላይ ሊያልቀው የላከ ነው፡፡ መስካሪም በአላህ በቃ፡፡»

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- ይህ ዲን ቀን እና ለሊት የደረሱበት ቦታ ሁሉ ይደርሳል፡፡ አላህ ይህን ሀይማኖት ከጭቃ የተሰራ ቤትም ይሁን ከግመል ቆዳ የተደራ ቤት ይሳይቀር አሸናፊዎችን እንዲያሸንፉ በማድረግም ይሁን ተሸናፊዎችን በሚዋረድ ያስገባዋል፡፡ ይህ ማሸነፍም ኢስላምን ከፍ ሲያደርግ ሽንፈቱንም ክህደትን ያዋርዳል፡፡ (ሙስነድ ኢማም አህመድ)

ምንም እንኳን ሙስሊሞች በተገቢው ሁኔታ ሀይማኖቱን እያስተማሩ ባይሆንም እስልምና ግን በጣም በከፍተኛ ቁጥር እየተስፋፋ እና እያደገ ይገኛል፡፡ ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ደግሞ ኢስላም ከሰው ተፈጥሮአዊ ስርዓት ስለሚስማማ፣ ፍላጎቱን ስለሚያሟላና ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ፣

ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መደላደልን ስለሚያረጋግጥ ነው፡፡ በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ) በባሮቹ ላይ ከሚለግሰው ውስጣዊ ጥንካሬ እና እገዛ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ጠላቶች ሀይማኖቱ ላይ ጦነት በመክፈት፣ ሰዎች እንዳይቀበሉት በመከላከል፣ መንገድ ላይ መሰናክል በመጋረጥ እና ሀይማኖቱን ኋላቀር እና ሽብርተኝነትን የሚያበረታታ በማስመሰልና ሰዎችን በማስፈራራት እንዲርቁት ለማድረግ ያላቸውን ሰዋዊም ሆነ ገንዘባዊ አቅም በሙሉ በመጠቀም ይንቀሳቀሳሉ፡፡

ይህን የሚያደርጉትም ኢስላም ከሚያልሙት ግብ፣ ከጥቅማቸው እና ህዝብን ለራሳቸው ጥቅም ከመበዝበዝ ስለሚያግዳቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ኢስላም በማንኛውም መልኩ ድንበር ማለፍን፣ በደልን፣ ብዝበዛንና የሰው ልጅ ከአላህ ውጪ ለሱ ነገር ባሪያ ማድረግን አጥብቆ ይቃወማል፡ ይህ ከወንጀልም ከባድ ወንጀል ነው፡፡ በተሌም ደግሞ ተበዳዮቹ ደካማዎች እና ምስኪኖች ሲሆኑ፡፡ ኢስላም አንድን ማህበረሰብ ከሌላ ማህበረሰብ፣ አንድን ጎጥ ከሌላ ጎጥ እንዲሁም ግለሰብን ከግለሰብ በተሌየ መነፅር ማየትን የሚከለክል ሀይማኖት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡፡

يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا ۚ إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ ۚ

«እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡»

በዚህች አነስተኛ መፅሀፍ ውስጥ እንደማስረጃ ቁርአንን በመሠረታዊነት እጠቀማለሁ፡፡ ምክንያቱም ይህ ቁርአን የፍጡራን መጀመሪያ የሰው ልጅ በራሱ ተመራምሮ ሊደርስበት የማይችለው ነገር መሆኑን በየገለጸ መሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

مَّا أَشْهَدتُّهُمْ خَلْقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَلَا خَلْقَ أَنفُسِهِمْ وَمَا كُنتُ مُتَّخِذَ الْمُضِلِّينَ عَضُدًا [١٨:٥١]

«የሰማያትንና የምድርን አፈጣጠር አላሳየኋቸውም፡፡ የነፍሶቻቸውንም አፈጣጠር (እንደዚሁ)፡፡ አሳሳቾችንም ረዳቶች አድርጌ የምይዝ አይደለሁም፡፡»

በተጨማሪነትም የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሶሂህ ሀዲሶችን እንደማስረጃ እጠቀማለሁ፡፡ ከቁርአን እና ከሀዲስ የተገኙ መረጃዎችን አሁን ካሉት ሳይንሳዊ ንድፈ ሀሳብ እና ግኝቶች ውስጥ ስለመቀየራቸው ምንም ማስተማመኛ ስለሌላቸው ነው፡፡ ይህን በተጨባጭ ህይወታችን ውስጥ ያስተዋልነው እና ያየነው መሬት ላይ ያለ እውነታ ነው፡፡ ብዙ ይታመንባቸው የነበሩ ሀሳቦች እና መላምቶች ሳይንስ በመሻሻሉ ምክንያት ውድቅ ሆነው ቀረተዋል፡፡ አላህ ሁሌም እውነትን ይናገራል፡፡

وَمَا أُوتِيتُم مِّنَ الْعِلْمِ إِلَّا قَلِيلًا [١٧:٨٥]

«ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም» በላቸው፡፡ ››

ዶ/ር አብዱራህማን ቢን አብዱልከሪም አሻይሀ

## <u>በአላህ ማመን</u>

በአላህ ማመን፣ አምላክ መኖሩን እውነት ማለትና ብቸና መሆኑን መመስከር የሀይማኖቱ መሠረት ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህኛው የእምነት መሠረት ማመን ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጅብሪል (ዐ.ሰ) በጠየቃቸው ግዜ ያብራሩትን ሌሎች መሠረቶች እንድናምን ስለሚያደርገን ነው፡፡

ጅብሪል (ዐ.ሰ) ፦ ስለ አማን ነገረኝ፡፡

ነብዩ (ሰዐ.ወ):- "በአላህ ማመን፣ በመላዕኮቶቹ፣ መፅሀፍቶቹ፣ በመልዕክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀን እና ጥሩም ይሁን መጥፎ በቅድመ ውሳኔ (በቀጽር) ማመን ነው፡፡"

እስልምና ዋና ዋና መሰረቶች በዚህ ሀዲስ አማካኝነት ተዘርዝረዋል፡፡ ቀጥለን እናብራራዋለን፡፡

### <u>አላህ (ሱ.ወ) እውነተኛው አምላክ</u>

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

هُوَ الْأَوَّلُ وَالْآخِرُ وَالظَّاهِرُ وَالْبَاطِنُ ۖ وَهُوَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٌ [٥٧:٣]

«እርሱ ፊትም ያለ፣ ኋላም ቀሪ፣ ግልጽም፣ ስውርም ነው፡፡ እርሱም ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡»

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ عَالِمُ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ ۖ هُوَ الرَّحْمَٰنُ الرَّحِيمُ [٥٩:٢٢]هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ ۚ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ [٥٩:٢٣]هُوَ اللَّهُ الْخَالِقُ الْبَارِئُ الْمُصَوِّرُ ۖ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ ۚ يُسَبِّحُ لَهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۖ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ [٥٩:٢٤]

«እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ የኾነ ነው፡፡ እርሱ እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ ነው፡፡ እርሱ አላህ ነው፡፡ ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ፣ ጸጥታን ሰጪው፣ ባሮቹን ጠባቂው፣ አሸናፊው፣ ኀያሉ፣ ኩሩው ነው፡፡ አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ፡፡ እርሱ አላህ ፈጣሪው (ከኢምንት) አስገኚው፣ ቅርጽን አሳማሪው ነው፡፡ ለእርሱ መልካሞች ስሞች አልሉት፡፡ በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ ለእርሱ ያሞግሳል፡፡ እርሱም»

እንዲሁም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْحَيُّ الْقَيُّومُ ۚ لَا تَأْخُذُهُ سِنَةٌ وَلَا نَوْمٌ ۚ لَّهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ ۗ مَن ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِندَهُ إِلَّا بِإِذْنِهِ ۚ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ ۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيْءٍ مِّنْ عِلْمِهِ إِلَّا بِمَا شَاءَ ۚ وَسِعَ كُرْسِيُّهُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ ۖ وَلَا يَئُودُهُ حِفْظُهُمَا ۚ وَهُوَ الْعَلِيُّ الْعَظِيمُ [٢:٢٥٥]

«አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ሕያው ራሱን ቻይ ነው፡፡ ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም፡፡ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፡፡ ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል፡፡ በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)፡፡ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ፡፡ ጥበቃቸውም አያቅተውም፡፡ እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው፡፡»

በእስልምና ሀይማኖት መሠረት አላህ የሚታወቅ አምላክ ነው። ሀይማኖታችን አላህ ምን ዓይነት ባህሪ እንዳለውና እንዴት ልንለምነው እና ልንቀርበው እንደምንችል ያስተምራል።

አላህ (ሱ.ወ)፡-

1. <u>ያለ አምላክ ነው፡-</u> እሱ ስለመኖሩ አለም እና በውስጡ ያሉ ፍጥረታት ሁሉ ማስረጃ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

   قُلِ انظُرُوا مَاذَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ وَمَا تُغْنِي الْآيَاتُ وَالنُّذُرُ عَن قَوْمٍ لَّا يُؤْمِنُونَ

   [١٠:١٠١]

   «በሰማያትና በምድር ያለውን (ተዓምር) ተመልከቱ» በላቸው፡፡ ተዓምራቶችና አስፈራሪዎችም ለማያምኑ ሕዝቦች አይጠቅሙም፡፡»

2. <u>ብቸኛ፣ መጠጊ የሆነ እና ስልጣኑን የሚጋራ ሌለው ነው።</u> ወላጅ፣ ልጅ፣ ተፎካካሪም ሆነ ባለቤት የለውም። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

   قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ [١١٢:١]اللَّهُ الصَّمَدُ [١١٢:٢] لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ [١١٢:٣]وَلَمْ يَكُن لَّهُ كُفُوًا

أَحَدٌ [١١٢:٤]

«በል «እርሱ አላህ አንድ ነው። «አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። «አልወለደም፤ አልተወለደምም። «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።»

3. እውቀቱ ሁሉንም ነገር ያደረሰ አዋቂ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፦

وَمَا يَعْزُبُ عَن رَّبِّكَ مِن مِّثْقَالِ ذَرَّةٍ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي السَّمَاءِ وَلَا أَصْغَرَ مِن ذَٰلِكَ وَلَا أَكْبَرَ إِلَّا فِي كِتَابٍ مُّبِينٍ [١٠:٦١]

4. ሁልግዜ ዘውታሪ፣ የማይሞት እና ህያው ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

هُوَ الْحَيُّ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَادْعُوهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ ۗ الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ [٤٠:٦٥]

«እርሱ ብቻ (ሁል ጊዜ) ሕያው ነው፤ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ ሃይማኖትንም ለእርሱ ያጠራችሁ ስትኾኑ «ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለአላህ ይኹን» የምትሉ ኾናችሁ ተገዙት።»

5. <u>አላህ ፍትሀዊ ጌታ ነው</u>። አይበድልም፣ አይጨቁንም በደል ከሱ በኩል ይመጣል ተብሎም አይፈራም።

وَنَضَعُ الْمَوَازِينَ الْقِسْطَ لِيَوْمِ الْقِيَامَةِ فَلَا تُظْلَمُ نَفْسٌ شَيْئًا ۖ وَإِن كَانَ مِثْقَالَ حَبَّةٍ مِّنْ خَرْدَلٍ أَتَيْنَا بِهَا ۗ وَكَفَىٰ بِنَا حَاسِبِينَ [٢١:٤٧]

«በትንሣኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን። ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም። (ሥራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርሷን እናመጣታለን። ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ።»

6. በአካል፣ በባህሪም ሆነ በስራ እሱን የሚመስል የለም። ምሉዕ የሆነ ነገር ሁሉ የሱ መገለጫ ነው። እሱ የፈለገው ይሆናል። እሱ ያልፈለገው ደግሞ አይሆንም። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ [٢٠:٨]

‹‹ አላህ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ ለእርሱ መልካሞች የኾኑ ስሞች አልሉት፡፡››

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

فَاطِرُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا وَمِنَ الْأَنْعَامِ أَزْوَاجًا ۖ يَذْرَؤُكُمْ فِيهِ ۚ لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ ۖ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ [٤٢:١١]

«ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ነው፡፡ ከነፍሶቻችሁ ሴቶችን ከቤት እንስሳዎችም ዓይነቶችን (ወንዶችና ሴቶችን) ለእናንተ አደረገላችሁ፡፡ በእርሱ ያበዛችኋል፡፡ የሚመስለው ምንም ነገር የለም፡፡ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡»

አላህ (ሱ.ወ) ፍጹምነቱን እና ታላቅነቱን የሚያመለክቱ ብዙ ስሞች እና ባህሪያቶች አሉት፡፡ የፈለገ ሰው በዚህ ርዕ ላይ ሰፊ ማብራሪያ የሚሰቱ መፅሀፍቶችን ማመሳከር ይችላል፡፡ነገር ግን የአላህ (ሱ.ወ) ስሞች እና ባህሪያቶች በቁጥር ያልተገደቡ እና ያልተወሰኑ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡፡ “አንድ ባሪያ ባሪየ ጭንቀትም ይሁን ሀዘን በገጠመው ግዜ የሚከተለውን ካለ ‘አላህ ሆይ እኔ ባሪያህ ነኝ፡፡ የሁለት ባሪያዎችህ ልጅ ነኝ፡፡ ሁሉ ነገሬ በእጅህ ነው፡፡ ፍርድህ በኔላይ የጸና ነው፡፡ ውሳኔህ ለነ ፍትሀዊ ነው፡፡ ባሉህ ስሞች ሁሉ እጠይቅሀለሁ፤ እራስህን በሰየምከውም፤ በመፅሀፍቶችህ ላይ ባወረድከውም፣ ከፍጡራኖች አንዱን ባሳወቅከውወይም በማይታየው የእውቀት አለም አንተ ዘንድ በጠበቅከው ቁርአንን ለቀልቤ ህይወት ዘሪ፣ለአይኔ ብርሀን፣ ለሀዘኔ አስወጋጅ እና ለጭንቀቴ ገላጭ አድርግልኝ፡፡’ አላህ ጭንቀቱን ያስወግድለታል፣ በሀዘኑ ቦታ ደስታን ይተካለታል” (ሶሂህ ኢብኑ ሂባን)

⇒ አላህ (ሱ.ወ) ስሞች እና ባህሪያቶች አሉት፡፡ ነገር ግን ፈጽሞ ከፍጡራን ጋር የሚመሳሰል አይደለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) አለ፡፡ የአላህ መኖር ግን ከፍጡራን መኖር ጋር የሚመሳሰል አይደለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ተመልካች ነው፡፡ መስማቱና መመልከቱ ግን ከፍጡራኑ ጋር የሚመሳሰል አይደለም፡፡ ይህ ህግ ሁሉም ስሞቹን ባህሪያቶቹ ላይ ይሰራል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ስለራሱ እንዲህ ይላል፡-

وَلَا يُحِيطُونَ بِهِ عِلْمًا [٢٠:١١٠]

«በእርሱም ዕውቀትን አያካብቡም፤ (አያውቁም)፡፡»

አላህ (ሱ.ወ) ከሰው ልጅ አዕምሮ እና እውቀት በላይ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

لَّا تُدْرِكُهُ الْأَبْصَارُ وَهُوَ يُدْرِكُ الْأَبْصَارَ ۖ وَهُوَ اللَّطِيفُ الْخَبِيرُ [٦:١٠٣]

«ዓይኖች አያገኙትም፤ (አያዩትም)፡፡ እርሱም ዓይኖችን ያያል፡፡ እርሱም ርኅራኄው ረቂቁ ውስጠ ዐዋቂው ነው፡፡»

መጠየቅ፣ መመራመር እና የነገራቶችን ተጨባጭ ለማወቅ መስራት የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባህሪ እንደመሆኑ መጠን አላህ (ሱ.ወ) ስለመኖሩ ማሰብና ማሰላሰል እምነትን የሚጣረስ ነገር ሳይሆን እንዳውም የእውነተኛ ኢማን ምልክት ነው፡፡

አቡሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች የሆኑ ሰዎች መጢና እንዲህ አሏቸው፡፡ "እኛ እኮ ምላሳችን ልትናገር የሚከብዳትን ነገር በልቦቻችን ውስጥ ሲመላለሱ እናገኛለን፡፡" ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "ይህ ከኢሣን ግልጽ ምልክቶች አንዱ ነው፡፡" አሉ ሶሒህ ሙስሊም

⇒ እነዚህ ሀሳቦች ምንጫቸው ከሸይጧን ውስወሳ ነው፡፡ በሚችል አቅም ሁሉ ሰዎችን ከአላህ ሀይማኖት ለማራቅ ይጥራል፡፡ በዚህም ላይ ቃልገብቷል፡፡ አላህ (ሰ.ዐ) እንዲህ ብሏል፡-

قَالَ أَرَأَيْتَكَ هَٰذَا الَّذِي كَرَّمْتَ عَلَيَّ لَئِنْ أَخَّرْتَنِ إِلَىٰ يَوْمِ الْقِيَامَةِ لَأَحْتَنِكَنَّ ذُرِّيَّتَهُ إِلَّا

قَلِيلًا [١٧:٦٢]

«ንገረኝ ይህ ያ በእኔ ላይ ያበለጥከው ነውን= እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ብታቆየኝ ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ወደ ስህተት በእርግጥ እስባቸዋለሁ» አለ፡፡»

በተመሳሳይህም ይህን የሸይጣን ተንኮል ነብዩ (ዐ.ሰ) አብራርተውታል፡፡ ኢብኑ አባስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና፡- የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በነፍሴ ውስጥ ከምናገረው ይልቅ ከሰማይ ብወረወር የሚቀለኝ ሀሳብ ይመላለስብኛል አለ፡፡ ረሱልም (ሰ.ዐ.ወ) "አላሁ አክበረር! አላሁ አክበር! ምስጋና ለዚያ (የሸይጣንን) ተንኮል ላከሸፈበት አምላክ አላህ የተገባነው፡፡" (ሙስነድ ኢማሙ አህመድ)

ሸይጣን በሰው ልጅ አዕምሮ አቅም መድረስ በማይቻል ነገር ሊወሰውስህ ሲሞክር የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) ምክር እና አደራ ተግብር፡፡ "ሰዎች ከመጠየቅ አይወገዱም ይህን

እስከማሉ ድረስ "ፍጡራንን አላህ ፈጠረ። አላህን ማን ፈጠረ? ይህ ነገር ያጋጠመው ሰው 'በአላህ አምኛለሁ'ይበል።" (ሶሂህ ሙስሊም)

ከዚህ ችግር እንዴት እንደምንወጣ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አብራርተዋል። "ሸይጣን ወደአንደኛችሁ ይመጣና እንዲህ ላል፦ "እንትንን ማን ፈጠረ? እንትንን ማን ፈጠረ? በመጨረሻም 'ጌታህን ማን ፈጠረ?' ይለዋል። ይህ ነገር ካጋጠማችሁ ተጠበቁ እና ንቁ። (ሰሂህ ቡኻሪ) አላህም እውነት ተናገረ፦

وَإِمَّا يَنزَغَنَّكَ مِنَ الشَّيْطَانِ نَزْغٌ فَاسْتَعِذْ بِاللَّهِ ۚ إِنَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ [٧:٢٠٠]

«ከሰይጣንም (በኩል) ጉትጎታ ቢያገኝህ በአላህ ተጠበቅ፡፡ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነውና፡፡»

## አላህ (ሱ.ወ) ስለመኖሩ ማስረጃዎች

በዚህ ዓለም ውስጥ የሚገኙ ፍጥረታት በሙሉ ያስገኛቸው ፈጣሪ ስለመኖሩ ጥርጣሬ ውስጥ በማይከትቱ መልኩ ግልጽ ማስረጃ ናቸው። ጤነኛ አዕምሮ እና ብሩህ አስተሳሰብ ያለው ሰው ሁሉ ይህንን መረዳት አያቅተውም። አላህ (ሱ.ወ) መኖሩን የሚክዱ ሰዎች በሰሜን ህዋሶቻቸው የሚደርሱበትን ነገር እንደማስረጃ እንድናመጣ ይጠይቃሉ። በዚህ የመከራከሪያ ሀሳቦቻቸው ግን እራሳቸውን እንደሚቃረኑ አልተረዱም። ምክንያቱ ደግሞ በዚህ ዓለም ላይ ባሉ የማዳሰሱ፣ በማይታዩ እና በማይጨበጡ ብዙ ነገራቶች ስለሚያምኑ ነው። የእነዚህን ነገራቶች ውጤት እና ፋና ግን አግኝተዋል። ለምሳሌ ያህል በመሬት ስበት ያምናሉ። ምንም እንኳ አይተዋት የማያውቁ ቢሆንም። ነገር ግን የዚህን ሀይል ውጤት የሚክድ የለም። እንዲሁም በመግነጢስ ሀይል ያምናሉ ምንም እንኳን አይተዋት የማያውቁ ቢሆኑም። ነገር ግን የዚህን ሀይል ውጤት የሚክድ የለም። እሱም ብረት ነክ ነገርን ወደራሱ የመሳብ ሀይል ነው። በተመሳሳ ሁኔታ የአእምሮ መኖር ያምናሉ። ውጤቱን እንጂ ያየውሰው ግን የለመው። ምንም እንኳ አንድ አንዴ የስሜት ህዋሶቻችን ስለ እነዚህ ነገራቶች የተሳሳተ ምስል ቢሰጡንም ትክክለኛ ማንነታቸውን ግን በአዕምሮአችን አሰላስለን እንደርስበታል። ለምሳሌ ያህል ውሀ ውስጥ የሰመጠ ቀጥያለ እንጨት በጣም የጎበጠ ይመስላል፤ ሁለት ትይዩ መስመሮች ከአይን እይታ በራቁ ቁጥር የሚቆራረጡ ይመስላል፤ ጭንቅላታችን በሰሜንም፣ በደቡብም ሆነ በምድር ወገብ ብንሆን ስንሄድ ወደላይ ያለ ይመስለናል። እነዚህ ምሳሌዎች አዕምሮ ባይኖር ኖሮ የስሜት ህዋሶቻችን የተሳሳተ መረጃ ያስጨብጡን እና መሀይም ሆነን እንቀር እንደነበር ያሳያል። ስለዚህ እውቀትን መገብየት የሚቻለው በ5ቱ የስሜት ህዋሳት ብቻ ነው ብለው የገደቡ ሰዎች በእርግጠም ተሳስተዋል። ታዲያ

**አላህ (ሱ.ወ) ስሜት ህዋሶቻቸውን ስላልደረሰበት መኖሩን ሲክዱ አዕምሮአቸው ከራሳቸው ጋር ነበርን?**
**በዚህ በኩል ደግሞ በአካባቢያቸው ዙሪያ ባሉ በማይጨበቱ ነገራቶች በውጤታቸው እና በፋናቸው ላይ በመመርኮዝ መኖራቸውን ያምናሉ። አላህ መኖሩን ለማመን ተዳሳሽ ማስረጃን መፈለግ አምላክን ለማወቅ ከሚደረገው ትግል በጣም የራቁ መሆንን ያሳያል።ፈርዓውንበአላህ ላሳመነ ቁሳቁ የሆነን ማስረጃ ጠይቆ ነበር። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል።**

وَقَالَ فِرْعَوْنُ يَا هَامَانُ ابْنِ لِي صَرْحًا لَّعَلِّي أَبْلُغُ الْأَسْبَابَ [٤٠:٣٦]أَسْبَابَ السَّمَاوَاتِ

فَأَطَّلِعَ إِلَىٰ إِلَٰهِ مُوسَىٰ وَإِنِّي لَأَظُنُّهُ كَاذِبًا ۚ وَكَذَٰلِكَ زُيِّنَ لِفِرْعَوْنَ سُوءُ عَمَلِهِ وَصُدَّ عَنِ

السَّبِيلِ ۚ وَمَا كَيْدُ فِرْعَوْنَ إِلَّا فِي تَبَابٍ [٤٠:٣٧]

*«ፈርዖንም አለ «ሃማን ሆይ! መንገዶችን እደርስ ዘንድ ረዢም ሕንጻን ለእኔ ካብልኝ። «የሰማያትን መንገዶች (እደርስ ዘንድ)፣ ወደ ሙሳም አምላክ እመለከት ዘንድ። እኔም ውሸታም ነው ብዬ በእርግጥ እጠረጥረዋለሁ» (አለ)። እንደዚሁም ለፈርዖን መጥፎ ሥራው ተሸለመለት። ከቅን መንገድም ታገደ። የፈርዖንም ተንኮል በከሳራ ውስጥ እንጅ አይደለም።»*

**ፊርዓውን ምንም እንኳን አምላክ ስለመኖሩ ቢያምንም ኩራት፣ መንጠባረር እና ሰዎችን ጨቁኖ የመግዛት ጥማቱ ይህንን በምላሱ ከማወጅ ከልክሎታል።**
**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ላል፡-**

وَجَاوَزْنَا بِبَنِي إِسْرَائِيلَ الْبَحْرَ فَأَتْبَعَهُمْ فِرْعَوْنُ وَجُنُودُهُ بَغْيًا وَعَدْوًا ۖ حَتَّىٰ إِذَا أَدْرَكَهُ الْغَرَقُ

قَالَ آمَنتُ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا الَّذِي آمَنَتْ بِهِ بَنُو إِسْرَائِيلَ وَأَنَا مِنَ الْمُسْلِمِينَ [١٠:٩٠]آلْآنَ وَقَدْ

عَصَيْتَ قَبْلُ وَكُنتَ مِنَ الْمُفْسِدِينَ [١٠:٩١]فَالْيَوْمَ نُنَجِّيكَ بِبَدَنِكَ لِتَكُونَ لِمَنْ خَلْفَكَ

آيَةً ۚ وَإِنَّ كَثِيرًا مِّنَ النَّاسِ عَنْ آيَاتِنَا لَغَافِلُونَ [١٠:٩٢]

«የእስራኤልንም ልጆች ባሕሩን አሳለፍናቸው፡፡ ፈርዖንና ሰራዊቱም ወሰን ለማለፍና ለመበደል ተከተሏቸው፡፡ መስጠምም ባገኘው ጊዜ፡- «አመንኩ፡፡ እነሆ ከዚያ የእስራኤል ልጆች በርሱ ከአመኑበት በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ እኔም ከታዛዦቹ ነኝ» አለ፡፡ ከአሁን በፊት በእርግጥ ያመጽክ ከአጥፊዎችም የነበርክ ስትሆን አሁን (አመንኩ ትላለህ)= ዛሬማ ከኋላህ ላሉት ተዓምር ትሆን ዘንድ በድን ሆነህ (ከባሕሩ) እናወጣሃለን (ተባለ)፡፡ ከሰዎችም ብዙዎቹ ከተዓምራታችን በእርግጥ ዘንጊዎች ናቸው፡፡»

**ይህ ባህሪ ዘመን ከዘመን የሚለዋወጥ ሳይሆን ከሀዲዎችን እና አስዋሾችን የሚያመሳስላቸው ሁሉም የሚቀጥል ነው፡፡ ይህም ከመሀይምነታቸው የተነሳ ነው፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ያላል፡-**

وَقَالَ الَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ لَوْلَا يُكَلِّمُنَا اللَّهُ أَوْ تَأْتِينَا آيَةٌ ۗ كَذَٰلِكَ قَالَ الَّذِينَ مِن قَبْلِهِم مِّثْلَ قَوْلِهِمْ ۘ تَشَابَهَتْ قُلُوبُهُمْ ۗ قَدْ بَيَّنَّا الْآيَاتِ لِقَوْمٍ يُوقِنُونَ [٢:١١٨]

«እነዚያም የማያውቁት (አንተ መልክተኛ ስለመኾንህ) አላህ አያናግረንም ኖሮአልን? ወይም (ለእውነተኛነትህ) ታምር አትመጣልንም ኖሮአልን? አሉ፡፡ እንደዚሁ እነዚያ ከነሱ በፊት የነበሩት እንደ ንግግራቸው ብጤ ብለዋል፡፡ ልቦቻቸው (በክሕደት) ተመሳሰሉ፡፡ ለሚያረጋግጡ ሕዝቦች አንቀጾችን በእርግጥ አብራርተናል፡፡»

**አልያም ከኩራት የመጣነው፡- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَقَالَ الَّذِينَ لَا يَرْجُونَ لِقَاءَنَا لَوْلَا أُنزِلَ عَلَيْنَا الْمَلَائِكَةُ أَوْ نَرَىٰ رَبَّنَا ۗ لَقَدِ اسْتَكْبَرُوا فِي أَنفُسِهِمْ وَعَتَوْا عُتُوًّا كَبِيرًا [٢٥:٢١]يَوْمَ يَرَوْنَ الْمَلَائِكَةَ لَا بُشْرَىٰ يَوْمَئِذٍ لِّلْمُجْرِمِينَ وَيَقُولُونَ حِجْرًا مَّحْجُورًا [٢٥:٢٢]

«እነዚያም መገናኘታችንን የማይፈሩት በእኛ ላይ ለምን መላእክት አልወረደም፡፡ ወይም ጌታችንን ለምን አናይም= አሉ፡ በነፍሶቻቸው ውስጥ በእርግጥ ኮሩ፡፡ ታላቅንም አመጽ አመፁ፡፡ መላእክትን በሚያዩበት ቀን በዚያ ጊዜ ለአመጸኞች ምስራች የላቸውም፡፡ «የተከለከለ ክልክልም አድርገን» ይላሉ፡፡»

**ወይም አይሁዶች እንዳደረጉ ከበዳይነት መንፈስ የመጣ ነው፡፡ ስለ እነሱ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَإِذْ قُلْتُمْ يَا مُوسَىٰ لَن نُّؤْمِنَ لَكَ حَتَّىٰ نَرَى اللَّهَ جَهْرَةً فَأَخَذَتْكُمُ الصَّاعِقَةُ وَأَنتُمْ تَنظُرُونَ

[٢:٥٥]

«ሙሳ ሆይ! አላህን በግልጽ እስከምናይ ድረስ ላንተ በፍጹም አናምንልህም» በላችሁም ጊዜ (አስታውሱ)፡፡ እናንተም እየተመለከታችሁ መብረቅ ያዘቻችሁ»

## አላህ (ሱ.ወ) ስለመኖሩ ተጨማሪ ማስረጃዎች

⇒ **ተፈጥሮአዊ የሆነው የጤና እና የንፁህ አስተሳሰብ ውጤት፡-**

በእርግጥ የሰው ልጅ ሲፈጠር ንፁህ፣ ያልተበከለ እና ማስተንተን የሚችል ተደርጎ ነው፡፡ የሰው ልጅ ማንኛውም ነገር ያለ አስጠን እና ያለምክንያት እንደማይገኝ እንዲያውቅ ተደረጎ የተፈጠረ ፍጡር ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ክፍል ውስጥ ስንገባ ጠረጴዛ ብታገኝ በእርግጠኝት ይህች ጠረጴዛ በራሷ ዘላ የገባች ሳትሆን ሰርቶ ክፍሉ ውስጥ ስገባት ሰው እንዳለ ትረዳለህ፡፡ አንድ የበረሀ ዘላን ይህንን ብትጠይቀው ተፈጥሮአዊ በሆነው የማሰብ ብቃቱ ይህንን ይረዳል፡፡ ጌታህን በምን አወቅከው ተብሎ ቢጠየቅም ይህንን ይመልሳል "የግመል ፍጋፍግ ግመል መኖሩን ያመለክታል፣ ፋንዳያ አህ መኖሩን ይናገራል፣ የጫማ ምልክት ያለፈ ሰው መኖን ይመሰክራል፡፡ ጨለማው ለሊት፣ ብርሃናማው ቀን በከዋክብት የደመቀ ሰማይ፣ በሸለቆዎች የተዋበ መሬት እንዲሁም በማዕበል የሚናወጠው ባህር አዛን እና ውስጥ አዋቂ ወደሆነውአምላክ አያመለክትምን? በእርግጥም ያመላክታል!!!

⇒ **የቅዱስ ቁርአን አናቅፆች**

ዙርአን በብዙ አንቀፅ ወዳካበበን ዩኒቨርሰቲ ዘወር ብለን እንድንመለከት እና እንድናስተነትን ይወተውተናል፡፡ ይህን ካደረግን ያለንምንም ጥርጣሬ ይህን አለም የሚያስተናብር ሀይል መኖሩን እንደረዳለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

قُلِ انظُرُوا مَاذَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ وَمَا تُغْنِي الْآيَاتُ وَالنُّذُرُ عَن قَوْمٍ لَّا يُؤْمِنُونَ

[١٠:١٠١]

* የዩኒቨርሱ አፈጣጠር፣ የቅርጽ እና የስርዓት ፍጹማዊነቱ፣ የከዋክብት እና የፕላኔቶች ስነምህዋር፣ ከስርአታቸው ጥቂት መዛነፍ ቢከሰት አላህ እንጂ ሌላ የሚያስቀው ከባባዱ የተፈጥሮ አደጋዎችን እናስተናግድ ነበር፡፡ ታዲያ ከዩኒቨርሱ መፈጠር ጀምሮ እስከአሁን እና ወደፊት ይህንን ፍፁማዊነት ጠብቆ የሚያስተናብር ማንነው?

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:-**

“ “ “ “ :-

فَسُبْحَانَ اللَّهِ حِينَ تُمْسُونَ وَحِينَ تُصْبِحُونَ [٣٠:١٧]وَلَهُ الْحَمْدُ فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ

وَعَشِيًّا وَحِينَ تُظْهِرُونَ [٣٠:١٨]يُخْرِجُ الْحَيَّ مِنَ الْمَيِّتِ وَيُخْرِجُ الْمَيِّتَ مِنَ الْحَيِّ وَيُحْيِي

الْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَا ۚ وَكَذَٰلِكَ تُخْرَجُونَ [٣٠:١٩]وَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ إِذَا

أوَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا لِّتَسْكُنُوا إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً

وَرَحْمَةً ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ [٣٠:٢١]ًنتُم بَشَرٌ تَنتَشِرُونَ [٣٠:٢٠]وَمِنْ

آيَاتِهِ خَلْقُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَاخْتِلَافُ أَلْسِنَتِكُمْ وَأَلْوَانِكُمْ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ

لِّلْعَالِمِينَ [٣٠:٢٢]وَمِنْ آيَاتِهِ مَنَامُكُم بِاللَّيْلِ وَالنَّهَارِ وَابْتِغَاؤُكُم مِّن فَضْلِهِ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ

لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَسْمَعُونَ [٣٠:٢٣]وَمِنْ آيَاتِهِ يُرِيكُمُ الْبَرْقَ خَوْفًا وَطَمَعًا وَيُنَزِّلُ مِنَ السَّمَاءِ

مَاءً فَيُحْيِي بِهِ الْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَا ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ [٣٠:٢٤]وَمِنْ آيَاتِهِ

أَن تَقُومَ السَّمَاءُ وَالْأَرْضُ بِأَمْرِهِ ۚ ثُمَّ إِذَا دَعَاكُمْ دَعْوَةً مِّنَ الْأَرْضِ إِذَا أَنتُمْ تَخْرُجُونَ

[٣٠:٢٥]وَلَهُ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۖ كُلٌّ لَّهُ قَانِتُونَ [٣٠:٢٦]وَهُوَ الَّذِي يَبْدَأُ الْخَلْقَ

ثُمَّ يُعِيدُهُ وَهُوَ أَهْوَنُ عَلَيْهِ ۚ وَلَهُ الْمَثَلُ الْأَعْلَىٰ فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ وَهُوَ الْعَزِيزُ

الْحَكِيمُ [٣٠:٢٧]

«ምስጋናም በሰማያትና በምድር ውስጥ ለርሱ ብቻ (የተገባው) ነው፡፡ በሰርክም፤ በቀትር ውስጥ በምትገቡም ጊዜ፤ (አጥሩት)፡፡ሕያውን ከሙት ያወጣል፡፡ ሙታንም ከሕያው ያወጣል፡፡ ምድርንም ከሞተች በኋላ ህያው ያደርጋታል፡፡ እንደዚሁም (ከመቃብር) ትወጣላችሁ፡፡ እናንተንም ከዐፈር መፍጠሩ ከዚያም እናንተ ወዲያውኑ የምትበታተኑ ሰዎች መኾናችሁ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አሉሉ፡፡ ሰማያትንና ምድርንም መፍጠሩ፣ የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁም መለያየት፣ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለዐዋቂዎች ተዓምራቶች አልሉበት፡፡ በሌሊትና በቀንም መተኛታችሁ፣ ከችሮታውም መፈለጋችሁ ከምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉበት፡፡ ብልጭታንም ፈሪዎችና ከጃዮች ስትሆኑ ለእናንተ ማሳየቱ፣ ከሰማይም ውሃን ማውረዱ፣ በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስቡ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉበት፡፡ ሰማይና ምድርም (ያለምሰሶ) በትዕዛዙ መቆማቸው፣ ከዚያም (መልአኩ ለትንሣኤ) ከምድር ጥሪን በጠራችሁ ጊዜ እናንተ ወዲያውኑ የምትወጡ መሆናችሁ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ ሁሉም ለእርሱ ታዛዦች ናቸው፡፡ እርሱም ያ መፍጠርን የሚጀምር ከዚያም የሚመልሰው ነው፡፡ እርሱም (መመለሱ) በእርሱ ላይ በጣም ገር ነው፡፡ ለእርሱም በሰማያትም በምድርም ከፍተኛ ባሕርይ (አንድነትና ለእርሱ ብጤ የሌለው መኾን) አልለው፡፡ እርሱም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡»

" " " " :-

وَالشَّمْسَ وَالْقَمَرَ وَالنُّجُومَ مُسَخَّرَاتٍ بِأَمْرِهِ ۗ أَلَا لَهُ الْخَلْقُ وَالْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ اللَّهُ رَبُّ

الْعَالَمِينَ [٧:٥٤]

«ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲኾኑ (ፈጠራቸው)፡፡ ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡»

* አስደናቂ የሆነው የሰው ልጅ አፈጣጠር፣ ውብ የሆነው የሰው ልጅ ተክለሰውነት እና አላህ (ሰ.ወ) የሰጠንን ችሎና ብቃት እንድናስተውል ቁርአን ያስተምራል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَفِي الْأَرْضِ آيَاتٌ لِّلْمُوقِنِينَ [٥١:٢٠]وَفِي أَنفُسِكُمْ ۚ أَفَلَا تُبْصِرُونَ [٥١:٢١]

«በምድርም ውስጥ ለሚያረጋግጡ ሰዎች ምልክቶች አሉ፡፡ በነፍሶቻችሁም ውስጥ (ምልክቶች አሉ)፤ ታዲያ አትመለከቱምን?›››

* **የሰው ልጅ ለመብላት፣ ለመጠጣት ለመልበስ እንዲሁም ለመጓጓዣነት የሚጠቀምባቸው እንስሳቶችን እንድናስተውል ቁርአን ያስተምራል፡፡**
**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَإِنَّ لَكُمْ فِي الْأَنْعَامِ لَعِبْرَةً ۖ نُّسْقِيكُم مِّمَّا فِي بُطُونِهِ مِن بَيْنِ فَرْثٍ وَدَمٍ لَّبَنًا خَالِصًا سَائِغًا لِّلشَّارِبِينَ [١٦:٦٦]وَمِن ثَمَرَاتِ النَّخِيلِ وَالْأَعْنَابِ تَتَّخِذُونَ مِنْهُ سَكَرًا وَرِزْقًا حَسَنًا ۗ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَةً لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ [١٦:٦٧]وَمِن ثَمَرَاتِ النَّخِيلِ وَالْأَعْنَابِ تَتَّخِذُونَ مِنْهُ سَكَرًا وَرِزْقًا حَسَنًا ۗ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَةً لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ [١٦:٦٧]وَأَوْحَىٰ رَبُّكَ إِلَى النَّحْلِ أَنِ اتَّخِذِي مِنَ الْجِبَالِ بُيُوتًا وَمِنَ الشَّجَرِ وَمِمَّا يَعْرِشُونَ [١٦:٦٨]ثُمَّ كُلِي مِن كُلِّ الثَّمَرَاتِ فَاسْلُكِي سُبُلَ رَبِّكِ ذُلُلًا ۚ يَخْرُجُ مِن بُطُونِهَا شَرَابٌ مُّخْتَلِفٌ أَلْوَانُهُ فِيهِ شِفَاءٌ لِّلنَّاسِ ۗ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَةً لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ [١٦:٦٩]

«ለናንተም በግመል፣ በከብት፣ በፍየል በእርግጥ መገምገሚያ አልላችሁ፡፡ በሆዶቹ ውስጥ ካለው ከፈረስና ከደም መካከል ጥሩ ወተትን ለጠጪዎች ተዋጭ ሲሆን እናጠጣችኋለን፡፡ ከዘምባባዎችና ከወይኖችም ፍሬዎች (እንመግባችኋለን)፡፡ ከእርሱ ጠጅንና መልካም ምግብንም ትሠራላችሁ፡፡ በዚህም ውስጥ ለሚያስቡ ሕዝቦች በእርግጥ ተዓምር አልለ፡፡ ጌታህም ወደ ንብ እንዲህ ሲል አስታወቀ «ከተራራዎች፣ ከዛፍም፣ (ሰዎች) ከሚሠሩትም (ቀፎ) ቤቶችን ያዝ፡፡ «ከዚያም ከፍሬዎች ሁሉ ብይ፡፡ የጌታሽንም መንገዶች (ላንቺ) የተገሩ

ሲኾኑ ግቢ፡፡» ከሆዶችዋ መልኮቹ የተለያዩ መጠጥ ይወጣል፡፡ በእርሱ ውስጥ ለሰዎች መድኃኒት አለበት፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች በእርግጥ ተዓምር አልለበት፡፡»

* **የሰው ልጅ ለምግብነት፣ ለመጠጥነት፣ ለመኖሪያነት እንዲሁም እንደ መድሀኒትነት የሚጠቀምባቸውን በቀለምና በቅርፅ የሚለያዩትን ዛፎች፣ አዝዕርቶች እና ቡቃያዎች እንድናስተነትን ቁርአን ያስተምረናል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَهُوَ الَّذِي مَدَّ الْأَرْضَ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَاسِيَ وَأَنْهَارًا ۖ وَمِن كُلِّ الثَّمَرَاتِ جَعَلَ فِيهَا

زَوْجَيْنِ اثْنَيْنِ ۖ يُغْشِي اللَّيْلَ النَّهَارَ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ [١٣:٣]وَفِي

الْأَرْضِ قِطَعٌ مُّتَجَاوِرَاتٌ وَجَنَّاتٌ مِّنْ أَعْنَابٍ وَزَرْعٌ وَنَخِيلٌ صِنْوَانٌ وَغَيْرُ صِنْوَانٍ يُسْقَىٰ بِمَاءٍ

وَاحِدٍ وَنُفَضِّلُ بَعْضَهَا عَلَىٰ بَعْضٍ فِي الْأُكُلِ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ [١٣:٤]

‹‹ እርሱም ያ ምድርን የዘረጋ በሷም ተራራዎችንና ወንዞችን ያደረገ በውስጧም ከፍሬዎች ሁሉ ሁለት ሁለት ዓይነቶችን ያደረገ ነው፡፡ ሌሊትን በቀን ይሸፍናል፡፡ በዚህም ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አሉ፡፡

በምድርም የተጎራበቱ ቁርጥራጮች አልሉ፡፡ ከወይኖችም አትክልቶች አዝርዕቶችም መንታዎችና መንታዎች ያልኾኑ ዘንባባዎችም አልሉ፡፡ በአንድ ውሃ ይጠጣሉ፤ (በጣዕምም ይለያያሉ)፡፡ ከፊሉዋንም በከፊሉ ላይ በሚበላው ሰብል እናበልጣለን፡፡ በዚህም ውስጥ ለሚያውቁ ሕዝቦች ተዓምራት አለበት፡፡»

* **በመሬት ላይ የሚንቀሳቀሱ በቅርፅም በባህሪም የሚለያዩ ፍጥረታትን እንድናስተውል ቁርዓን ይመክረናል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

خَلَقَ السَّمَاوَاتِ بِغَيْرِ عَمَدٍ تَرَوْنَهَا ۖ وَأَلْقَىٰ فِي الْأَرْضِ رَوَاسِيَ أَن تَمِيدَ بِكُمْ وَبَثَّ

فِيهَا مِن كُلِّ دَابَّةٍ ۚ وَأَنزَلْنَا مِنَ السَّمَاءِ مَاءً فَأَنبَتْنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوْجٍ كَرِيمٍ [٣١:١٠]هَٰذَا

خَلْقُ اللَّهِ فَأَرُونِي مَاذَا خَلَقَ الَّذِينَ مِن دُونِهِ ۚ بَلِ الظَّالِمُونَ فِي ضَلَالٍ مُّبِينٍ [٣١:١١]

«ሰማያትን ያለምታዩዋት አዕማድ (ምሰሶዎች) ፈጠረ፡፡ በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለ፡፡ በእርሷም ላይ ከተንቀሳቃሽ ሁሉ በተነ፡፡ ከሰማይም ውሃን አወረድን፡፡ በእርሷም ውስጥ ከመልካም ዓይነት ሁሉ አበቀልን፡፡ ይህ የአላህ ፍጡር ነው፡፡ እነዚያ ከእርሱ ሌላ ያሉት ምንን እንደፈጠሩ እስኪ አሳዩኝ፡ ፡ በእውነቱ በዳዮቹ በግልጽ ጥመት ውስጥ ናቸው፡፡»

*** አስደናቂ የሆነው የፍጥረት አለሙ ትስስር እና ቁርኝትን እንድናስተውል ቁርዓን ያበረታታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَاللَّهُ خَلَقَ كُلَّ دَابَّةٍ مِّن مَّاءٍ ۖ فَمِنْهُم مَّن يَمْشِي عَلَىٰ بَطْنِهِ وَمِنْهُم مَّن يَمْشِي عَلَىٰ رِجْلَيْنِ وَمِنْهُم مَّن يَمْشِي عَلَىٰ أَرْبَعٍ ۚ يَخْلُقُ اللَّهُ مَا يَشَاءُ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

[٢٤:٤٥]

«አላህም ተንቀሳቃሽን ሁሉ ከውሃ ፈጠረ፡፡ ከእነሱም በሆዱ ላይ የሚኼድ አልለ፡፡ ከእነሱም በሁለት እግሮች ላይ የሚኼድ አልለ፡፡ አላህ የሚሻውን ሁሉ ይፈጥራል፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና፡፡»

*** አስገራሚ የሆነው ለሁሉም ፍጡራን ተገቢውን ሲሳይ ማከፋፈል እና ሀላፊ መሆንን ከአላህ ውጪ ማንም እንደማይችል ቁርአን ያስረዳል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَمَا مِن دَابَّةٍ فِي الْأَرْضِ إِلَّا عَلَى اللَّهِ رِزْقُهَا وَيَعْلَمُ مُسْتَقَرَّهَا وَمُسْتَوْدَعَهَا ۚ كُلٌّ فِي كِتَابٍ مُّبِينٍ [١١:٦]

«በምድርም ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም ምግቧ በአላህ ላይ ያለ ቢኾን እንጂ፡፡ ማረፊያዋንም መርጊያዋንም ያውቃል፡፡ ሁሉም ግልጽ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡»

**በሌላ አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል፡-**

وَكَأَيِّن مِّن دَابَّةٍ لَّا تَحْمِلُ رِزْقَهَا اللَّهُ يَرْزُقُهَا وَإِيَّاكُمْ ۚ وَهُوَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ [٢٩:٦٠]

«ከተንቀሳቃሽም ምግቧን ለመሸከም የማትችለው ብዙ ናት፡፡ አላህ ይመግባታል፡፡ እናንተንም (ይመግባል)፡፡ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነውና፡፡»

አላህ (ሱ.ወ) በዚህ ዓለም ላይ ያሉ ፍጡር ሁሉ ሁለት ሁለት ተዛማች ጥንድ ሁነው እንደተፈጠሩ ይነግረናል፡፡ ሰማይና ምድር፣ ቀን እና ሌሊት፣ ሞትና ህይወት፣ ደስታ እና ሀዘን፣ ፀሀይ እና ጨረቃ፣ የማይንቀሳቀስ እና የሚንቀሳቀስ፣ ሞቃት እና ቀዝቃዛ፣ ጥሩ እና መጥፎ፣ ክህደት እና እምነት እንዲሁም ከእንስሳቶች እና ከቡቃያዎች ከነዚህም ውጪ ያለነገርስ ያወቅነውም ይሁን ያላወቅነው ነገር፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَمِن كُلِّ شَيْءٍ خَلَقْنَا زَوْجَيْنِ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ [٥١:٤٩]

«ትገነዘቡም ዘንድ ከነገሩ ሁሉ ሁለት (ተቃራኒ) ዓይነትን ፈጠርን፡፡»

ስለፍጥረታት ማስተንተን እና ማሰላሰል ፈጣሪን ይበልጥ ለማወቅ የሚረዳ ትልቅ መሳሪያ ነው፡፡ ይህም የምሁራን፣ የምጡቆችና የአስተዋዮች ባህሪ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

أَلَمْ تَرَ أَنَّ اللَّهَ أَنزَلَ مِنَ السَّمَاءِ مَاءً فَأَخْرَجْنَا بِهِ ثَمَرَاتٍ مُّخْتَلِفًا أَلْوَانُهَا ۚ وَمِنَ الْجِبَالِ جُدَدٌ بِيضٌ وَحُمْرٌ مُّخْتَلِفٌ أَلْوَانُهَا وَغَرَابِيبُ سُودٌ [٣٥:٢٧]وَمِنَ النَّاسِ وَالدَّوَابِّ وَالْأَنْعَامِ مُخْتَلِفٌ أَلْوَانُهُ كَذَٰلِكَ ۗ إِنَّمَا يَخْشَى اللَّهَ مِنْ عِبَادِهِ الْعُلَمَاءُ ۗ إِنَّ اللَّهَ عَزِيزٌ غَفُورٌ [٣٥:٢٨]

‹‹ አላህ ከሰማይ ውሃን ማውረዱን አላየህምን? በእርሱም ዓይነቶቻቸው የተለያዩ ፍሬዎችን አወጣን፡፡ ከጋራዎችም መልኮቻቸው የተለያዩ ነጮች፣ ቀዮችም፣ በጣም ጥቁሮችም የኾኑ መንገዶች አልሉ፡፡ ከሰዎችም፣ ከተንቀሳቃሾችም፣ ከቤት እንሰሳዎችም እንደዚሁ መልኮቻቸው የተለያዩ አልሉ፡፡ አላህን ከባሮቹ ውስጥ የሚፈሩት ዐዋቂዎቹ ብቻ ናቸው፡፡ አላህ አሸናፊ መሓሪ ነው፡፡»

አላህ (ሱ.ወ) በዚህ ዓለም ላይ ከሚኖሩት ፍጥረታት መሀል የተወሰኑትን ነግሮናል፡፡ ቀሪዎችን ዳግም አልነገረንም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

سُبْحَانَ الَّذِي خَلَقَ الْأَزْوَاجَ كُلَّهَا مِمَّا تُنبِتُ الْأَرْضُ وَمِنْ أَنفُسِهِمْ وَمِمَّا لَا يَعْلَمُونَ [٣٦:٣٦]

«ያ ምድር ከምታበቅለው ከነፍሶቻቸውም ከማያውቁትም ነገር ዓይነቶችን ሁሏንም የፈጠረ (አምላክ) ጥራት ይገባው፡፡»

ዩኒቨርሱን አስገንቶ ስርዓቱን ጠብቆ የሚያስኬድ ሀይል መኖሩ ጥርጥር የለውም፡፡ ይህ ሀይል ከሚከተሉት 3 አንዱ ውጪ ሊሆን አይችልም፡፡

1ኛ. ዩኒቨርሱ ከነአስገራሚ ስርዓቱ ራስ በራሱ የተገኘ ነገር ነው፡፡ ይህ መላምት ስር መሠረቱ ደካማ እና ሊሆን የማይቻል ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም አዲስ ነገር ሁሉ አስገኝ ይፈልጋልና ነው፡፡

2ኛ. ዩኒቨርሱ የተገኘው ከሌላ በፊት ከነበረ ነገር ነው፡፡ ይህ ነገር ምናልባትም አሁን ከዩኒቨርሱ የተወሰነ ክፍል ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ አዕምሮ የማይቀበለው ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ነገር አምሳያውን መፍጠር (ማስገኘት) ስለማይችል ነው፡፡

3ኛ. ዩኒቨርሱን ያስገኘው ሀይል ከዚህ ዓለም ውጪ የሆነና በሁሉም ነገር የተለየ የሆነ ሀይል ነው፡፡ እሱም የአለማት ጌታ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) ነው፡፡ ሙስሊሞች የሚያምኑበት አስተሳሰብም ይህ ነው፡፡

ኤ ቲየስቶቹ ግን በጥርጣሪያቸው ላይ እንደዋለሉ ይቀራሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

أَمْ خُلِقُوا مِنْ غَيْرِ شَيْءٍ أَمْ هُمُ الْخَالِقُونَ [٥٢:٣٥]أَمْ خَلَقُوا السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ ۚ بَل لَّا يُوقِنُونَ [٥٢:٣٦]أَمْ عِندَهُمْ خَزَائِنُ رَبِّكَ أَمْ هُمُ الْمُصَيْطِرُونَ [٥٢:٣٧]

« ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም አያረጋግጡም፡፡ ወይስ የጌታህ ግምጃ ቤቶች እነርሱ ዘንድ ናቸውን? ወይስ እነርሱ አሸናፊዎች ናቸውን?.»

⇒ አላህ ስመኖሩ የሰው ልጅ ህሊና ሌላኛው ማስረጃ ነው፡፡

የሰውልጅ ውስጡን ማዳመጥ ከቻለ ራሱንና ዩኒቨርሱን የፈጠረ ሀያል ጌታ እንዳለ ይረዳል፡፡ ይህ ምሁራኖች ተፈጥሮአዊ ሃይማኖት እንደሚሉት ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا ۚ فِطْرَتَ اللَّهِ الَّتِي فَطَرَ النَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ اللَّهِ ۚ

«ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፡፡ የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በእርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዟት)፡፡ የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፡፡»

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- "የሰው ልጅ ሁሉ በተፈጥሮ ላይ ይወለዳል፡፡ ከዛም ወላጆቹ ክርስቲያን አልያም አይሁድ ያደርጉታል፡፡ ልክ እንደ እንስሳት ልጅ ማለት ነው፡፡ እናንተ እስካልቆረጣችኋቸው ድረስ ቆማጣ ታገኛላችሁን?" "አንቱ የአላህ መልዕክተና ሆይ! ልጅ ሆኖ የሚሞት ሰው እንዴት ነው የሚሆነው?" ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ ረሱልም (ሰ.ዐ.ወ) ወደፊት ምን ሊሰሩ እንደሚችሉ አላህ አዋቂ ነው፡፡" አሉ፡፡ (ሶሒህ ቡኻሪ)

የሰው ልጅ ይህ ተፈጥሮ በሚዛባበት ወቅት እንኳን በጭንቅ እና በችግር ጊዜ የሚመካበት ሌላ ሀይል ላይ ሲጠጋ ታገኘዋለህ፡፡ የድሮዎቹ ህዝቦች ሲያደርጉት የነበረውም ይህንን ነው፡፡ ጣኦታትን እንደአምላክ ይዘው ይገዟቸው ነበር፡፡ ፀሀይን፣ ጨረቃን፣ ድንጋይን እና ዛፎችን ይገዙ ነበር፡፡ ይህ ተፈጥሮ ከሰው ልጅ በሙሉ የሚያንስ ነው፡፡ ምንም እንኳን አንድ አንዶች በኩራት እና በእንቢተኝነት ቢክዱም የተቀሩትት አምነው ያጽድቃሉ፡፡

ይህ አብሮን የሚወለደው ተፈጥሮ አዳጋች ነገር ላይ ስንወድቅ ግልፅ ይወጣል፡፡ በህመምግዜ ችግር በሚያጋጥም ግዜ ወይም ድንገተና አደጋ በማንኛውም ግዜ ሳናስበው "ያአላህ" እንላለን፡፡ አልያም ከችግሩ ሊያላቅቀው የሚችል አሸናፊ ሀይል መኖሩን በማመን ኤሁን ወደላይ ሲያንጋጥጥ ታየዋለህ፡፡ አላህም (ሱ.ወ) እውነት ተናገረ፡-

وَإِذَا مَسَّ الْإِنسَانَ الضُّرُّ دَعَانَا لِجَنبِهِ أَوْ قَاعِدًا أَوْ قَائِمًا فَلَمَّا كَشَفْنَا عَنْهُ ضُرَّهُ مَرَّ كَأَن

لَّمْ يَدْعُنَا إِلَىٰ ضُرٍّ مَّسَّهُ ۚ

« ሰውንም ጉዳት ባገኘው ጊዜ በጎኑ ላይ ተጋድሞ ወይም ተቀምጦ ወይም ቆሞ ይለምነናል፡፡ ጉዳቱንም ከእሱ ላይ በገለጥንለት ጊዜ ወደ አገኘው ጉዳት እንዳልጠራን ሆኖ ያልፋል፡፡»

የቁርዓን ፈተና፡- ቁርዓን ፍጡራን በሙሉ ተጣምረው ይሁን ለየግል ህይወት ያለውን ነገር እንዲፈጥሩ ፈተና አቅረቧል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

يَا أَيُّهَا النَّاسُ ضُرِبَ مَثَلٌ فَاسْتَمِعُوا لَهُ ۚ إِنَّ الَّذِينَ تَدْعُونَ مِن دُونِ اللَّهِ لَن يَخْلُقُوا

ذُبَابًا وَلَوِ اجْتَمَعُوا لَهُ ۖ وَإِن يَسْلُبْهُمُ الذُّبَابُ شَيْئًا لَّا يَسْتَنقِذُوهُ مِنْهُ ۚ ضَعُفَ

الطَّالِبُ وَالْمَطْلُوبُ [٢٢:٧٣]

« እናንተ ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተገለጸላችሁ፡፡ ለእርሱም አድምጡት፡፡ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸው (ጣዖታት) ዝንብን ፈጽሞ አይፈጥሩም፡፡ እርሱን (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳን (አይችሉም)፡፡ አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከእርሱ አያስጥሉትም፡፡ ፈላጊውም ተፈላጊውም ደከሙ፡፡»

**ይህ ፈተና የቀረበበት ምክንያት ህይወት አላህ ብቻ የሚያውቃት የአላህ ሚስጥር እና ማንም ሊያውቀው የሚችል ጉዳይ ባለመሆኑ ነው፡፡አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَيَسْأَلُونَكَ عَنِ الرُّوحِ ۖ قُلِ الرُّوحُ مِنْ أَمْرِ رَبِّي وَمَا أُوتِيتُم مِّنَ الْعِلْمِ إِلَّا قَلِيلًا [١٧:٨٥]

ከሩሕም ይጠይቁሃል፡፡ «ሩሕ ከጌታዬ ነገር ነው ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም» በላቸው፡፡

**ኸረ እንዲያውም ህይወት የሌለውንም ነገር ቢሆን መፍጠር የሚሳናቸው ናቸው። ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል “እንደኔ ለመፍጠል ከሚሯሯጥ ሰው በላይ በዳይ ማን አለ? እስኪ (ከቻሉ) ቅንጠት እንኳ ይፍጠሩ። አልያም ጥራጥሬን ወይም ገብስን ይፍጠሩ።” (ሶሂህ ቡኻሪ)**

⇒ **የሰው ልጅ በዚህ ዩኒቨረስ ውስጥ የፈለገውን መስራት ተስኖታል። ይህ ዩኒቨርሱን እንደፈለገ የሚያሽከረክር ሀይል እንዳለ አመላካች ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

أَلَمْ تَرَ إِلَى الَّذِي حَاجَّ إِبْرَاهِيمَ فِي رَبِّهِ أَنْ آتَاهُ اللَّهُ الْمُلْكَ إِذْ قَالَ إِبْرَاهِيمُ رَبِّيَ الَّذِي يُحْيِي وَيُمِيتُ قَالَ أَنَا أُحْيِي وَأُمِيتُ ۖ قَالَ إِبْرَاهِيمُ فَإِنَّ اللَّهَ يَأْتِي بِالشَّمْسِ مِنَ الْمَشْرِقِ فَأْتِ بِهَا مِنَ الْمَغْرِبِ فَبُهِتَ الَّذِي كَفَرَ ۗ وَاللَّهُ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ [٢:٢٥٨]

« ወደዚያ አላህ ንግሥናን ስለሰጠው ኢብራሂምን በጌታው ነገር ወደ ተከራከረው ሰው አላየህምን= ኢብራሂም «ጌታዬ ያ ሕያው የሚያደርግና የሚገድል ነው» ባለ ጊዜ «እኔ ሕያው አደርጋለሁ እገድላለሁም» አለ፡፡ ኢብራሂም፡- «አላህ ፀሐይን ከምሥራቅ በኩል ያመጣል (አንተ) ከምዕራብ በኩል አምጣት» አለው፡፡ ያም የካደው ሰው ዋለለ፤ (መልስ አጣ) አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም፡፡»

⟹ አምላክ ስለመኖሩ ሌላኛው ማስረጃ ለመላው የሰው ልጅ እስከመጨረሻው ቀን ድረስ የመጨረሻው ሰማያዊ መፅሀፍ የሆነውን ቁርዓንን የሚመሳሰል መፅሀፍ እንዲያመጡ የቀረበው ፈተና ነው፡፡አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

قُل لَّئِنِ اجْتَمَعَتِ الْإِنسُ وَالْجِنُّ عَلَىٰ أَن يَأْتُوا بِمِثْلِ هَٰذَا الْقُرْآنِ لَا يَأْتُونَ بِمِثْلِهِ وَلَوْ كَانَ

بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ ظَهِيرًا [١٧:٨٨]

«ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርአን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢሆንም እንኳ ብጤውን አያመጡም» በላቸው፡፡»

* ምንም እንኳ የቋንቋ ምሁራኖች በተለይም ደግሞ ቁርዓን ቋንቋ እናት ቋንቋቸው የሆኑ ሰዎች በጣም ከፍተኛ ፍላጎት እየኖራቸው አምሳያውን ማምጣት አቅቷቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በመኖሩ እና በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክተኛነት የሚጠራጠር ሰው ካለ ይህንን ፈተና ተቀብሎ ቁርዓንን የሚመሳሰል መፅሀፍ ማምጣት ይችላል፡

⇒ ኸረ እንደውም ፈተናው ቀለል ብሎዋል፡፡አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

أَمْ يَقُولُونَ افْتَرَاهُ ۖ قُلْ فَأْتُوا بِعَشْرِ سُوَرٍ مِّثْلِهِ مُفْتَرَيَاتٍ وَادْعُوا مَنِ اسْتَطَعْتُم مِّن دُونِ

اللَّهِ إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ [١١:١٣]

«ይልቁንም «(ቁርአንን) ቀጣጠፈው» ይላሉን=፡- «እውነተኞች እንደሆናችሁ ብጤው የሆኑን ዐስር የተቀጣጠፉ ሱራዎች አምጡ፡፡ ከአላህም ሌላ የቻላችሁትን (ረዳት) ጥሩ» በላቸው፡፡»

⇒ ከዚህ በላይም አላህ አቅልሎታል፡፡
አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَإِن كُنتُمْ فِي رَيْبٍ مِّمَّا نَزَّلْنَا عَلَىٰ عَبْدِنَا فَأْتُوا بِسُورَةٍ مِّن مِّثْلِهِ وَادْعُوا شُهَدَاءَكُم مِّن دُونِ

اللَّهِ إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ [٢:٢٣]

«በባሪያችንም ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ፡፡ እውነተኞችም እንደኾናችሁ ከአላህ ሌላ መስካሪዎቻችሁን ጥሩ፡፡»

**ይህ ቁርአን ውሸት ያልሆነ በትክክል የአላህ የሆነቃል ነው፡፡አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَمَا كَانَ هَٰذَا الْقُرْآنُ أَن يُفْتَرَىٰ مِن دُونِ اللَّهِ وَلَٰكِن تَصْدِيقَ الَّذِي بَيْنَ يَدَيْهِ وَتَفْصِيلَ الْكِتَابِ لَا رَيْبَ فِيهِ مِن رَّبِّ الْعَالَمِينَ [١٠:٣٧]

« ይህም ቁርኣን ከአላህ ሌላ (ከሆነ ፍጡር) የተቀጠፈ ሊሆን አይገባውም፡፡ ግን ያንን ከእርሱ በፊት ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥና በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን የሚዘረዝር በእርሱ ጥርጣሬ የሌለበት ሲሆን ከዓለማት ጌታ (የተወረደ) ነው፡፡»

**የሰው ንግግር ቢሆን ኖሮማ አናቅፆቹ እርስ በእርሳቸው መጋጨት ውሸት መሆኑ ግልፅ ይሆን ነበር፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ الْقُرْآنَ ۚ وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ اللَّهِ لَوَجَدُوا فِيهِ اخْتِلَافًا كَثِيرًا [٤:٨٢]

«ቁርኣንን አያስተነትኑምን= ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር፡፡»

**ስለፍጥረተ አለሙ አገናኘት እና ፍፃሜ ስለሆነ መሠረት የምናደርገው አላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

اللَّهُ خَالِقُ كُلِّ شَيْءٍ ۖ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ وَكِيلٌ [٣٩:٦٢]لَّهُ مَقَالِيدُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۗ

«አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው፡፡ የሰማያትና የምድር (ድልብ) መክፈቻዎች የእርሱ ብቻ ናቸው፡፡»

## **ተጨባጭ በሆነው አለም የመጀመሪያ ፍጥረት**

**የሰው ልጅ የማወቅ እና የመረዳት አቅም በሚኖርበት እና በሚያየው ተጨባጭ አለም የተወሰነ እንደመሆኑ መጠን፤ የጌታውን ታላቅነት የሚገልጽ፣ ወደጌታ ውዴታ እና ወዳጅነት የሚያደርስ ካልሆነ በቀር ስለማይታየው አለም ጉዳይ ለማወቅ መጣጣሩ ፋይዳ የለውም፡፡ ለዚህም ነው**

አምላካችን አላህ (ሱ.ወ) ፍጡራኖች እሱን እንዲያውቁት የሚረዳቸውን የማይታየውን አለም ሚስጥር በየጊዜው ነብዮችን እየላከ የሚያሳውቀው፡፡ የሰው ልጅ የማወቅ አቅም አይደለም የማይታውን አለም ሊደርስ ቀርቶ ጎረቤት ክፍል ውስጥ ያለውን ነገር ማወቅ አይችልም፡፡

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

الَّذِي خَلَقَ سَبْعَ سَمَاوَاتٍ طِبَاقًا ۖ مَّا تَرَىٰ فِي خَلْقِ الرَّحْمَٰنِ مِن تَفَاوُتٍ ۖ فَارْجِعِ الْبَصَرَ هَلْ تَرَىٰ مِن فُطُورٍ [٦٧:٣]ثُمَّ ارْجِعِ الْبَصَرَ كَرَّتَيْنِ يَنقَلِبْ إِلَيْكَ الْبَصَرُ خَاسِئًا وَهُوَ حَسِيرٌ [٦٧:٤]

«ያ ሰባትን ሰማያት የተነባበሩ ኾነው የፈጠረ ነው፡፡ በአልረሕማን አፈጣጠር ውስጥ ምንም መዛነፍን አታይም፡፡ ዓይንህንም መልስ፡፡ «ከስንጥቆች አንዳችን ታያለህን?» ከዚያም ብዙ ጊዜ ዓይንህን መላልስ፡፡ ዓይንህ ተዋርዶ እርሱም የደከመ ኾኖ ወዳንተ ይመለሳል፡፡»

## <u>የሰማይ፣ ምድር እና በመሀላቸው ያሉ ነገራቶች አፈጣጠር</u>

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَهُوَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ بِالْحَقِّ ۖ وَيَوْمَ يَقُولُ كُن فَيَكُونُ ۚ قَوْلُهُ الْحَقُّ ۚ وَلَهُ الْمُلْكُ يَوْمَ يُنفَخُ فِي الصُّورِ ۚ عَالِمُ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ ۚ وَهُوَ الْحَكِيمُ الْخَبِيرُ [٦:٧٣]

«እርሱም ያ ሰማያትንና ምድርን በእውነት የፈጠረ ነው፡፡ «ኹን» የሚልበትንና ወዲያውም የሚኾንበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ቃሉ እውነት ነው፡፡ በቀንዱም በሚነፋ ቀን ንግሥናው የርሱ ብቻ ነው፡፡ ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ ነው፡፡ እርሱም ጥበበኛው ውስጥ ዐዋቂው ነው፡፡»

**⇒ በሰማይና ምድር ውስጥ ካሉት ፍጥረታቶች መሀል የተወሰኑትን፡-**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

أَأَنتُمْ أَشَدُّ خَلْقًا أَمِ السَّمَاءُ ۚ بَنَاهَا [٧٩:٢٧]رَفَعَ سَمْكَهَا فَسَوَّاهَا [٧٩:٢٨]وَأَغْطَشَ لَيْلَهَا وَأَخْرَجَ ضُحَاهَا [٧٩:٢٩]وَالْأَرْضَ بَعْدَ ذَٰلِكَ دَحَاهَا [٧٩:٣٠]أَخْرَجَ مِنْهَا مَاءَهَا وَمَرْعَاهَا

[٧٩:٣١]وَالْجِبَالَ أَرْسَاهَا [٧٩:٣٢]مَتَاعًا لَّكُمْ وَلِأَنْعَامِكُمْ [٧٩:٣٣]

«ባፈጣጠር እናንተ ይበልጥ የበረታችሁ ናችሁን? ወይንስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት፡፡ከፍታዋን አጓነ፤ አስተካከላትም፡፡ሌሊቷንም አጨለመ፡፡ ቀንዋንም ገለጸ፡፡ምድርንም ከዚህ በኋላ ዘረጋት፡፡ውሃዋንና ግጦሿን ከእርሷ አወጣ፡፡ጋራዎችንም አደላደላቸው፡፡ለእናንተና ለእንስሶቻችሁ መጣቀሚያ ይኾን ዘንድ (ይህን አደረገ)፡፡»

" " " " :-

وَأَرْسَلْنَا الرِّيَاحَ لَوَاقِحَ فَأَنزَلْنَا مِنَ السَّمَاءِ مَاءً فَأَسْقَيْنَاكُمُوهُ وَمَا أَنتُمْ لَهُ بِخَازِنِينَ

‹‹ነፋሶችንም (ደመናን) ተሸካሚዎች አድርገን ላክን፡፡ ከሰማይም (ከደመና) ዝናብን አወረድን፡፡ እርሱንም አጠጣናችሁ፡፡ እናንተም ለእርሱ አድላቢዎች አይደላችሁም፡፡»

**አላህ (ሱ.ወ) እንዳብራራው ንፋስ አይነቶች አሉት፡፡ ከፊሎቹ የእዝነት ንፋስ ናቸው፡፡**
**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَهُوَ الَّذِي يُرْسِلُ الرِّيَاحَ بُشْرًا بَيْنَ يَدَيْ رَحْمَتِهِ ۖ حَتَّىٰ إِذَا أَقَلَّتْ سَحَابًا ثِقَالًا سُقْنَاهُ لِبَلَدٍ مَّيِّتٍ فَأَنزَلْنَا بِهِ الْمَاءَ فَأَخْرَجْنَا بِهِ مِن كُلِّ الثَّمَرَاتِ ۚ كَذَٰلِكَ نُخْرِجُ الْمَوْتَىٰ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ

[٧:٥٧]

«እርሱም ያ ነፋሶችን ከችሮታው (ከዝናም) በፊት አብሳሪዎች አድርጎ የሚልክ ነው፡፡ ከባዳዎችንም ደመናዎች በተሸከሙ ጊዜ ሙት ወደ ኾነ አገር እንነዳዋለን፡፡ በእርሱም ውሃን እናወርዳለን፡፡ ከፍሬዎችም ሁሉ በእርሱ እናወጣለን፡፡ እንደዚሁ ትገነዘቡ ዘንድ ሙታንን (ከመቃብር) እናወጣለን፡፡»

**ከፊሉ ደግሞ የቁጣ እና ቅጣት ንፋስ ነው፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

أَمْ أَمِنتُمْ أَن يُعِيدَكُمْ فِيهِ تَارَةً أُخْرَىٰ فَيُرْسِلَ عَلَيْكُمْ قَاصِفًا مِّنَ الرِّيحِ فَيُغْرِقَكُم بِمَا كَفَرْتُمْ ۙ ثُمَّ لَا تَجِدُوا لَكُمْ عَلَيْنَا بِهِ تَبِيعًا [١٧:٦٩]

«ወይስ ሌላ ጊዜ ወደ እርሱ (ወደ ባሕር) የሚመልሳችሁ ወዲያውም በእናንተ ላይ ብርቱን ነፋስ የሚልክ በክሕደታችሁም ምክንያት የሚያሰጥማችሁ መኾኑን ከዚያም በኛ ላይ በእርሱ ተከታይን (ረዳትን) ለእናንተ የማታገኙ መኾናችሁን አትፈሩምን፧»

" " " " :-

فَأَصَابَهَا إِعْصَارٌ فِيهِ نَارٌ فَاحْتَرَقَتْ ۗ

«በውስጡ እሳት ያለበት ውርጭ ሊያገኛትና ልትቃጠል ይወዳልን፧ »

" " " " :-

فَأَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ رِيحًا صَرْصَرًا فِي أَيَّامٍ نَّحِسَاتٍ

«በእነርሱ ላይ የሚንሻሻን ብርቱ ነፋስ መናጢዎች በኾኑ ቀናት ውስጥ ላክንባቸው፡፡»

- አላህ (ሱ.ወ) ሰባት ሰማያት እና ሰባት ምድርን ፈጥሯል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

اللَّهُ الَّذِي خَلَقَ سَبْعَ سَمَاوَاتٍ وَمِنَ الْأَرْضِ مِثْلَهُنَّ يَتَنَزَّلُ الْأَمْرُ بَيْنَهُنَّ لِتَعْلَمُوا أَنَّ اللَّهَ

عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ وَأَنَّ اللَّهَ قَدْ أَحَاطَ بِكُلِّ شَيْءٍ عِلْمًا [٦٥:١٢]

«አላህ ያ ሰባትን ሰማያት የፈጠረ ነው፡፡ ከምድርም መሰላቸውን (ፈጥሮአል)፤ በመካከላቸው ትእዛዙ ይወርዳል፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መኾኑን አላህም በነገሩ ሁሉ በዕውቀት ያካበበ መኾኑን በዕውቀት ያካበበ መኾኑን ታውቁ ዘንድ (ይህንን አሳወቃችሁ)፡፡»

- በመጀመሪያ ሰማያትና ምድር አንዱ ከአንዱ ተደራርበው የተጣበቁ ነበሩ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

أَوَلَمْ يَرَ الَّذِينَ كَفَرُوا أَنَّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ كَانَتَا رَتْقًا فَفَتَقْنَاهُمَا ۖ وَجَعَلْنَا مِنَ الْمَاءِ كُلَّ

شَيْءٍ حَيٍّ ۖ أَفَلَا يُؤْمِنُونَ [٢١:٣٠]

« እነዚያም የካዱት ሰማያትና ምድር የተጣበቁ የነበሩና የለያየናቸው መኾናችንን አያውቁምን= ሕያው የኾነንም ነገር ሁሉ ከውሃ ፈጠርን፡፡ አያምኑምን=»

- የሰማያት፣ የምድር እና በውስጣቸው ያሉ ነገራቶችን ለመፍጠር የወሰደውንም ግዜ አላህ (ሱ.ወ) ነግሮናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

قُلْ أَئِنَّكُمْ لَتَكْفُرُونَ بِالَّذِي خَلَقَ الْأَرْضَ فِي يَوْمَيْنِ وَتَجْعَلُونَ لَهُ أَندَادًا ۚ ذَٰلِكَ رَبُّ الْعَالَمِينَ [٤١:٩]وَجَعَلَ فِيهَا رَوَاسِيَ مِن فَوْقِهَا وَبَارَكَ فِيهَا وَقَدَّرَ فِيهَا أَقْوَاتَهَا فِي أَرْبَعَةِ أَيَّامٍ سَوَاءً لِّلسَّائِلِينَ [٤١:١٠]ثُمَّ اسْتَوَىٰ إِلَى السَّمَاءِ وَهِيَ دُخَانٌ فَقَالَ لَهَا وَلِلْأَرْضِ ائْتِيَا طَوْعًا أَوْ كَرْهًا قَالَتَا أَتَيْنَا طَائِعِينَ [٤١:١١]فَقَضَاهُنَّ سَبْعَ سَمَاوَاتٍ فِي يَوْمَيْنِ وَأَوْحَىٰ فِي كُلِّ سَمَاءٍ أَمْرَهَا ۚ وَزَيَّنَّا السَّمَاءَ الدُّنْيَا بِمَصَابِيحَ وَحِفْظًا ۚ ذَٰلِكَ تَقْدِيرُ الْعَزِيزِ الْعَلِيمِ [٤١:١٢]

«በላቸው «እናንተ በዚያ ምድርን በሁለት ቀኖች ውስጥ በፈጠረው አምላክ በእርግጥ ትክዳላችሁን? ለእርሱም ባለንጣዎችን ታደርጋላችሁን? ያ (ይህንን የሠራው) የዓለማት ጌታ ነው፡፡በእርሷም ከበላይዋ የረጉ ጋራዎችን አደረገ፡፡ በእርሷም በረከትን አደረገ፡፡ በውስጧም ምግቦችዋን (ካለፉት ሁለት ቀኖች ጋር) በአራት ቀናት ውሰጥ ለጠያቂዎች ትክክል ሲኾኑ ወሰነ፡፡ከዚያም ወደ ሰማይ እርሷ ጭስ ኾና ሳለች አሰበ፡፡ ለእርሷም ለምድርም «ወዳችሁም ኾነ ወይም ጠልታችሁ ኑ» አላቸው፡፡ «ታዛዦች ኾነን መጣን» አሉ፡፡ በሁለት ቀኖችም ውስጥ ሰባት ሰማያት አደረጋቸው፡፡ በሰማይቱም ሁሉ ነገሯን አዘጋጀ፡፡ ቅርቢቱንም ሰማይ በመብራቶች አጌጥን፡፡ (ከሰይጣናት) መጠበቅንም ጠበቅናት፡፡ ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው (ጌታ) ውሳኔ ነው፡፡»

## የመላዕክቶች አፈጣጠር

- መላዕክቶች ከአላህ (ሱ.ወ) ፍጡራኖች መሀል አንዱ ናቸው፡፡ የተፈጠሩትም ከብርሀን ነው፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- “መላዕክቶች ከብርሀን ተፈጠሩ፡፡ አጋንንቶች ደግሞ ከፍም እሳት ተፈጠሩ፡፡ አዳም የተፈጠረው ደግሞ ቀርዓንን እንዳብራራላችሁ ነው፡፡” (ሙስሊም)

- **አላህ (ሱ.ወ) የፈጠራቸው የተወከሉበትን ሥራ እንዲሰሩ ነው፡፡**

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَمَا مِنَّا إِلَّا لَهُ مَقَامٌ مَّعْلُومٌ [٣٧:١٦٤]وَإِنَّا لَنَحْنُ الصَّافُّونَ [٣٧:١٦٥]وَإِنَّا لَنَحْنُ الْمُسَبِّحُونَ [٣٧:١٦٦]

«(ጂብሪል አለ) ከእኛም አንድም የለም፤ ለእርሱ የታወቀ ደረጃ ያለው ቢሆን እንጅ፡፡እኛም (ጌታን ለመግገዛት) ተሰላፊዎቹ እኛ ነን፡፡እኛም (አላህን) አጥሪዎቹ እኛ ነን፡፡»

- **የተወሰኑት ስማቸውን አላህ (ሱ.ወ) ነግሮናል፡፡ ጅብሪል፣ ሚካኤል፣ እስራፊል እና የመሳሰሉትን፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

مَن كَانَ عَدُوًّا لِّلَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَرُسُلِهِ وَجِبْرِيلَ وَمِيكَالَ فَإِنَّ اللَّهَ عَدُوٌّ لِّلْكَافِرِينَ [٢:٩٨]

«ለአላህና ለመላእክቱ ለመልክተኞቹም ለጂብሪልም ለሚካልም (ሚካኤል) ጠላት የኾነ ሰው አላህ ለ(እነዚህ) ከሓዲዎች ጠላት ነው፡፡»

- **ጅብሪል (ዐ.ሰ) ከአላህ (ሱ.ወ) ወደ ነብዮች ራዕይ ለማመላለስ የተወከለ መላኢካ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

نَزَلَ بِهِ الرُّوحُ الْأَمِينُ [٢٦:١٩٣]عَلَىٰ قَلْبِكَ لِتَكُونَ مِنَ الْمُنذِرِينَ [٢٦:١٩٤]

  «እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) አወረደው፤ ከአስፈራሪዎቹ (ነቢያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)፡፡»

- **ሚካኤል (ዐ.ሰ) በዝናብ እና በቡቃያዎች ላይ፣ ኢስራፊል ደግሞ ጡርንባውን በመንፋት ላይ የተወሰከሉ ናቸው፡፡ 3 የጡሩባ ንፊቶች አሉ፡፡**
  - **የመጀመሪያው አስደንጋጩ ነው፡፡**

    **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَنُفِخَ فِي الصُّورِ فَصَعِقَ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَمَن فِي الْأَرْضِ إِلَّا مَن شَاءَ اللَّهُ ۖ

«በቀንዱም ይንነፋል፡፡ በሰማያት ውስጥ ያለው ፍጡርና በምድርም ውስጥ ያለው ፍጡር ሁሉ አላህ የሻው ሲቀር በድንጋጤ ይሞታል፡፡»

- **ሁለተኛው ሁሉንም ፍጠር የሚገድል ሲሆን**
- **ሶስተኛው ደግሞ ከሞት መቀስቀሻ ነው፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል**

وَنُفِخَ فِي الصُّورِ فَصَعِقَ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَمَن فِي الْأَرْضِ إِلَّا مَن شَاءَ اللَّهُ ۖ ثُمَّ نُفِخَ فِيهِ أُخْرَىٰ فَإِذَا هُمْ قِيَامٌ يَنظُرُونَ [٣٩:٦٨]

«በቀንዱም ይንነፋል፡፡ በሰማያት ውስጥ ያለው ፍጡርና በምድርም ውስጥ ያለው ፍጡር ሁሉ አላህ የሻው ሲቀር በድንጋጤ ይሞታል፡፡ ከዚያም በእርሱ ሌላ (መንነፋት) ይንነፋል፡፡ ወዲያውም እነርሱ (የሚሠራባቸውን) የሚጠባበቁ ኾነው ቋሚዎች ይኾናሉ፡፡»

- **ስማቸው ከተነገረን መላዕኮች መሀል የሞት መላኢካ እና አጋዞቹ ተጠቃሽ ናቸው፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَهُوَ الْقَاهِرُ فَوْقَ عِبَادِهِ ۖ وَيُرْسِلُ عَلَيْكُمْ حَفَظَةً حَتَّىٰ إِذَا جَاءَ أَحَدَكُمُ الْمَوْتُ تَوَفَّتْهُ رُسُلُنَا وَهُمْ لَا يُفَرِّطُونَ [٦:٦١]ثُمَّ رُدُّوا إِلَى اللَّهِ مَوْلَاهُمُ الْحَقِّ ۚ أَلَا لَهُ الْحُكْمُ وَهُوَ أَسْرَعُ الْحَاسِبِينَ [٦:٦٢]

«እርሱም ከባሮቹ በላይ ሲኾን ሁሉን አሸናፊ ነው፡፡ በናንተም ላይ ጠባቂዎችን (መላእክት) ይልካል፡፡ አንዳችሁንም ሞት በመጣበት ጊዜ (የሞት) መልእክተኞቻችን እነርሱ (ትእዛዛትን) የማያጓድሉ ሲኾኑ ይገድሉታል፡፡ ከዚያም እውነተኛ ወደ ኾነው ጌታቸው ወደ አላህ ይመለሳሉ፡፡ ንቁ! ፍርዱ ለእርሱ ብቻ ነው፡ ፡ እርሱም ከተቆጣጣሪዎች ሁሉ ይበልጥ ፈጣን ነው፡፡»

- **ሌሎች ደግሞ የአላህን ዙፋን የሚሸከሙ እና ለአላህ ቅርብ የሆኑ ናቸው፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

لَّن يَسْتَنكِفَ الْمَسِيحُ أَن يَكُونَ عَبْدًا لِّلَّهِ وَلَا الْمَلَائِكَةُ الْمُقَرَّبُونَ ۚ

«አልመሲሕ (ኢየሱስ) ለአላህ ባሪያ ከመኾን ፈጽሞ አይጠየፍም፡፡ ቀራቢዎች የኾኑት መላእክትም (አይጠየፉም)፡፡»

- ከፊሎቹ ደግሞ የጀነት መላኢኮች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ የጀሀነም መላኢኮች ናቸው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا قُوا أَنفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ نَارًا وَقُودُهَا النَّاسُ وَالْحِجَارَةُ عَلَيْهَا مَلَائِكَةٌ غِلَاظٌ شِدَادٌ لَّا يَعْصُونَ اللَّهَ مَا أَمَرَهُمْ وَيَفْعَلُونَ مَا يُؤْمَرُونَ [٦٦:٦]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ደንጋዮች ከኾነች እሳት ጠብቁ፡፡ በእርሷ ላይ ጨካኞች፣ ኀይለኞች የኾኑ መላእክት አልሉ፡፡ አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም፡፡ የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ፡፡»

- የሰውን ልጅ ስራ ለመመዝገብ በተጠንቀቅ የቆሙም አሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

لَهُ مُعَقِّبَاتٌ مِّن بَيْنِ يَدَيْهِ وَمِنْ خَلْفِهِ يَحْفَظُونَهُ مِنْ أَمْرِ اللَّهِ ۗ

«ለእርሱ (ለሰው) ከስተፊቱም ከኋላውም በአላህ ትዕዛዝ (ከክፉ) የሚጠብቁት ተተካኪዎች (መላእክት) አሉት፡፡»

- የሰውን ልጅ ከክፉ ነገር ለመጠበቅ የተመደቡም አሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَإِنَّ عَلَيْكُمْ لَحَافِظِينَ [٨٢:١٠] كِرَامًا كَاتِبِينَ [٨٢:١١]يَعْلَمُونَ مَا تَفْعَلُونَ [٨٢:١٢]

«በእናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ያሉባችሁ፤ ስትኾኑ፤ የተከበሩ ጸሐፊዎች የኾኑ፤ (ተጠባባቂዎች)፡፡የምትሠሩትን ሁሉ የሚያውቁ፡፡»

- የተፈጠሩበትን ሌላና አላማም ለአላህ (ሱ.ወ) መገዛት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَلَهُ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ وَمَنْ عِندَهُ لَا يَسْتَكْبِرُونَ عَنْ عِبَادَتِهِ وَلَا يَسْتَحْسِرُونَ [٢١:١٩]يُسَبِّحُونَ اللَّيْلَ وَالنَّهَارَ لَا يَفْتُرُونَ [٢١:٢٠]

‹‹በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉም የእርሱ ነው፡፡ እርሱ ዘንድ ያሉትም (መላእክት) እርሱን ከመገዛት አይኮሩም፡፡ አይሰለቹምም፡፡በሌሊትና በቀንም ያጠሩታል፤ አያርፉም፡፡››

- የቁጥራቸውን ብዛት ከአላህ ውጪ የሚያውቀው የለም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

وَمَا يَعْلَمُ جُنُودَ رَبِّكَ إِلَّا هُوَ ۚ وَمَا هِيَ إِلَّا ذِكْرَىٰ لِلْبَشَرِ [٧٤:٣١]

‹‹የጌታህንም ሰራዊት (ልክ) ከርሱ በቀር ማንም አያውቅም፡፡ እርሷም (የሰቀር እሳት) ለሰዎች መገሰጫ እንጅ ሌላ አይደለችም፡፡ >>

* በዚህ ርዕስ ላይ እውቀቱን የበለጠ ለማዳበር ሚፈልግ ሰው ካለ ስለጉዳዩ ሰፊ ማብራሪያ የሚሰጡ መፅሀፎች አሉና ማንበብ ይቻላል፡፡

## የአጋንንቶች አፈጣጠር

- አጋንንቶች ማየት ከማንችላቸው አላህ ፍጡሮች ውስጥ ናቸው፡፡ የተፈጠሩበትም አላማ አላህን (ሱ.ወ) መገዛት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ [٥١:٥٦]مَا أُرِيدُ مِنْهُم مِّن رِّزْقٍ وَمَا أُرِيدُ أَن يُطْعِمُونِ [٥١:٥٧]إِنَّ اللَّهَ هُوَ الرَّزَّاقُ ذُو الْقُوَّةِ الْمَتِينُ [٥١:٥٨]

- ሰው ልጅ ላይ ለበት ሀላፊነት እና ግዴታ ሁሉ እነርሱም ላይ አለ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

وَإِذْ صَرَفْنَا إِلَيْكَ نَفَرًا مِّنَ الْجِنِّ يَسْتَمِعُونَ الْقُرْآنَ فَلَمَّا حَضَرُوهُ قَالُوا أَنصِتُوا ۖ فَلَمَّا قُضِيَ وَلَّوْا إِلَىٰ قَوْمِهِم مُّنذِرِينَ [٤٦:٢٩]قَالُوا يَا قَوْمَنَا إِنَّا سَمِعْنَا كِتَابًا أُنزِلَ مِن بَعْدِ مُوسَىٰ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ يَهْدِي إِلَى الْحَقِّ وَإِلَىٰ طَرِيقٍ مُّسْتَقِيمٍ [٤٦:٣٠]

‹‹ከጋኔን የኾኑን ጭፍሮች ቁርአንን የሚያዳምጡ ሲኾኑ ወዳንተ ባዞርን ጊዜም (አስታውስ)፡፡ በተጣዱትም ጊዜ ዝም ብላችሁ አዳምጡ ተባባሉ፡፡ በተጨረሰም ጊዜ አስጠንቃቂዎች ኾነው ወደ

ሕዝቦቻቸው ተመለሱ፡፡ አሉም «ሕዝቦቻችን ሆይ! እኛ ከሙሳ በኋላ የተወረደን መጽሐፍ በፊቱ ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ ወደ እውነትና ወደ ቀጥተኛ መንገድ የሚመራ የኾነን ሰማን፡፡»

- **አላህ (ሱ.ወ) የፈጠራቸው ከእሳት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

خَلَقَ الْإِنسَانَ مِن صَلْصَالٍ كَالْفَخَّارِ [٥٥:١٤]وَخَلَقَ الْجَانَّ مِن مَّارِجٍ مِّن نَّارٍ [٥٥:١٥]

«ሰውን እንደ ሸክላ ከሚቅጨለጨል ደረቅ ጭቃ ፈጠረው፡፡ ጃንንም ከእሳት ከኾነ ነበልባል ፈጠረው፡፡»

**በሌላ ቦታም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል0**

وَلَقَدْ خَلَقْنَا الْإِنسَانَ مِن صَلْصَالٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ [١٥:٢٦]وَالْجَانَّ خَلَقْنَاهُ مِن قَبْلُ مِن

نَّارِ السَّمُومِ [١٥:٢٧]

«ሰውንም ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጥቁር ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው፡፡ ጃንንም (ከሰው) በፊት ከእሳት ነበልባል ፈጠርነው፡፡»

## የአዳም (ዐ.ሰ) አፈጣጠር

- **አዳም (ዐ.ሰ) የሰው ልጆች አባት እና መሠረታቸው ነው፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَائِكَةِ إِنِّي جَاعِلٌ فِي الْأَرْضِ خَلِيفَةً ۖ قَالُوا أَتَجْعَلُ فِيهَا مَن يُفْسِدُ فِيهَا

وَيَسْفِكُ الدِّمَاءَ وَنَحْنُ نُسَبِّحُ بِحَمْدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَ ۖ قَالَ إِنِّي أَعْلَمُ مَا لَا تَعْلَمُونَ [٢:٣٠]

<<(ሙሐመድ ሆይ) ጌታህ ለመላእክት፡- «እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤» ባለ ጊዜ (የኾነውን አስታውስ፤ እነርሱም) «እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፉንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን?» አሉ፡፡ (አላህ) «እኔ የማታውቁትን ነገር አውቃለሁ» አላቸው፡፡»

وَعَلَّمَ آدَمَ الْأَسْمَاءَ كُلَّهَا ثُمَّ عَرَضَهُمْ عَلَى الْمَلَائِكَةِ فَقَالَ أَنبِئُونِي بِأَسْمَاءِ هَٰؤُلَاءِ إِن كُنتُمْ

صَادِقِينَ [٢:٣١]

«አደምንም ስሞችን ሁሏንም አስተማረው፡፡ ከዚያም በመላእክት ላይ (ተጠሪዎቹን) አቀረባቸው፡፡ «እውነተኞችም እንደኾናችሁ የነዚህን (ተጠሪዎች) ስሞች ንገሩኝ» አላቸው፡፡»

قَالُوا سُبْحَانَكَ لَا عِلْمَ لَنَا إِلَّا مَا عَلَّمْتَنَا ۖ إِنَّكَ أَنتَ الْعَلِيمُ الْحَكِيمُ [٢:٣٢]

«ጥራት ይገባህ፤ ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም፡፡ አንተ ዐዋቂው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና» (አሉ)፡፡»

قَالَ يَا آدَمُ أَنبِئْهُم بِأَسْمَائِهِمْ ۖ فَلَمَّا أَنبَأَهُم بِأَسْمَائِهِمْ قَالَ أَلَمْ أَقُل لَّكُمْ إِنِّي أَعْلَمُ غَيْبَ

السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَأَعْلَمُ مَا تُبْدُونَ وَمَا كُنتُمْ تَكْتُمُونَ [٢:٣٣]

፡-«አደም ሆይ ስሞቻቸውን ንገራቸው» አለው፡፡ ስሞቻቸውን በነገራቸውም ጊዜ «እኔ የሰማያትንና የምድርን ሩቅ ምስጢር ዐውቃለሁ፤ የምትገልጹትንና ያንንም ትደብቁት የነበራችሁትን ዐውቃለሁ አላልኳችሁምን?» አላቸው፡፡»

وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَائِكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ أَبَىٰ وَاسْتَكْبَرَ وَكَانَ مِنَ الْكَافِرِينَ

[٢:٣٤]

«ለመላእክትም «ለአደም ስገዱ» ባልን ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር እምቢ አለ፤ ኮራም ከከሓዲዎቹም ኾነ፡፡»

وَقُلْنَا يَا آدَمُ اسْكُنْ أَنتَ وَزَوْجُكَ الْجَنَّةَ وَكُلَا مِنْهَا رَغَدًا حَيْثُ شِئْتُمَا وَلَا تَقْرَبَا هَٰذِهِ

الشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ الظَّالِمِينَ [٢:٣٥]

«አደም ሆይ! አንተ ከነሚስትህ በገነት ተቀመጥ፤ ከርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ፤ ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ ከበደለኞች ትኾናላችሁና» አልንም፡፡»

فَأَزَلَّهُمَا الشَّيْطَانُ عَنْهَا فَأَخْرَجَهُمَا مِمَّا كَانَا فِيهِ ۖ وَقُلْنَا اهْبِطُوا بَعْضُكُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ ۖ

وَلَكُمْ فِي الْأَرْضِ مُسْتَقَرٌّ وَمَتَاعٌ إِلَىٰ حِينٍ [٢:٣٦]

«ከርሷም ሰይጣን አዳለጣቸው በውስጡም ከነበሩበት (ድሎት) አወጣቸው፡፡ «ከፊላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ውረዱ፤ ለናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ (ሞታችሁ) ድረስ መርጊያና መጣቀሚያ አላችሁ» አልናቸው፡፡»

فَتَلَقَّىٰ آدَمُ مِن رَّبِّهِ كَلِمَاتٍ فَتَابَ عَلَيْهِ ۚ إِنَّهُ هُوَ التَّوَّابُ الرَّحِيمُ [٢:٣٧]

«አደምም ከጌታው ቃላትን ተቀበለ፡፡ በርሱ ላይም (ጌታው ጸጸትን በመቀበል) ተመለሰለት፤ እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡»

قُلْنَا اهْبِطُوا مِنْهَا جَمِيعًا ۖ فَإِمَّا يَأْتِيَنَّكُم مِّنِّي هُدًى فَمَن تَبِعَ هُدَايَ فَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ [٢:٣٨]

«ሁላችሁም ኾናችሁ ከርሷ ውረዱ፡፡ ከኔም የኾነ መመሪያ ቢመጣላችሁ ወዲያውኑ መመሪያዬን የተከተለ ሰው በነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም» አልናቸው፡፡»

وَالَّذِينَ كَفَرُوا وَكَذَّبُوا بِآيَاتِنَا أُولَٰئِكَ أَصْحَابُ النَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَالِدُونَ [٢:٣٩]

«እነዚያም (በመልክተኞቻችን) የካዱ በአንቀጾቻችንም ያስተባበሉ እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፡፡ እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡»

- **የሰው ልጆች ሙሉ የአዳም (ዐ.ሰ) ልጆች እና የሱ ዘር ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፤-**

يَا أَيُّهَا النَّاسُ اتَّقُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَاحِدَةٍ

«እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርስዋም መቀናጆዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ፡፡»

**ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን አስመልክተው የሚከተሉትን ብለዋል፦**

**"እናንተ ሰዎች ሆይ! ጌታችሁ አንድ ነው፡፡ አባታችሁም አንድ ነው፡፡ ሁላችሁም ከአዳም ስትሆኑ አዳም ደግሞ ከአፈር ነው፡፡ አላህ ዘንድ ከናንተ በላጫችሁ አላህን በጣም ፈሪያችሁ ነው፡፡ አረብ የሆነ ሰው አረብ ካልሆነ ሰው ላ ብልጫ የለውም፤ አረብ ያልሆነውም አረብ በሆነው ላይ ብልጫ**

የለውም፣ ነጭ የሆነ ሰው በቀዩ ላይ ብልጫ የለውም፣ ቀዩም ሰው በነጩ ላይ ብልጫ የለውም አላህን በመፈፍራት ቢሆን እንጂ" (አህመድ ዘግበውታል)

## አዳም (ዐ.ሰ) የተፈጠረው እንዴት ነው

- አላህ (ሱ.ወ) አዳምን የፈጠረው ከአፈር እንደሆነ ገልጿል። ይህንንም በተለያዩ መልኩ በብዙ አንቀፆች ተናግሯል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

إِنَّ مَثَلَ عِيسَىٰ عِندَ اللَّهِ كَمَثَلِ آدَمَ ۖ خَلَقَهُ مِن تُرَابٍ ثُمَّ قَالَ لَهُ كُن فَيَكُونُ [٣:٥٩]

«አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው። ከዐፈር ፈጠረው። ከዚያም ለርሱ (ሰው) «ኹን» አለው፤ ኾነም።»

- በሌላ ቦታ ደግሞ አጣባቂ ከሆነ ጭቃ እንደተፈጠረ ገልጿል።
  አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

هُوَ الَّذِي خَلَقَكُم مِّن طِينٍ ثُمَّ قَضَىٰ أَجَلًا ۖ وَأَجَلٌ مُّسَمًّى عِندَهُ ۖ ثُمَّ أَنتُمْ تَمْتَرُونَ [٦:٢]

«እርሱ ያ ከጭቃ የፈጠራችሁ ከዚያም (የሞት) ጊዜን የወሰነ ነው። እርሱም ዘንድ (ለትንሣኤ) የተወሰነ ጊዜ አልለ። ከዚያም እናንተ (በመቀስቀሳችሁ) ትጠራጠራላችሁ።»

فَاسْتَفْتِهِمْ أَهُمْ أَشَدُّ خَلْقًا أَم مَّنْ خَلَقْنَا ۚ إِنَّا خَلَقْنَاهُم مِّن طِينٍ لَّازِبٍ [٣٧:١١]

«ጠይቃቸውም፤ እነርሱ በአፈጣጠር ይበልጥ የበረቱ ናቸውን? ወይስ እኛ (ከእነርሱ በፊት) የፈጠርነው? (ፍጡር) እኛ ከሚጣበቅ ጭቃ ፈጠርናቸው።»

- በሌላ ቦታም ከጭቃ እና ሸክላ እንደሰራ ያብራራል።
  አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

خَلَقَ الْإِنسَانَ مِن صَلْصَالٍ كَالْفَخَّارِ [٥٥:١٤]

«ሰውን እንደ ሸክላ ከሚቅጨለጨል ደረቅ ጭቃ ፈጠረው።»

- ሌላ አንቀጽ ላይ ደግ ከሚገማ ጥቁር ጭቃ እንደሆነ ይነገራል።
  አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَلَقَدْ خَلَقْنَا الْإِنسَانَ مِن صَلْصَالٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ [١٥:٢٦]

«ሰውንም ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጥቁር ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው፡፡»

* **ወጣም ወረደ አላህ (ሱ.ወ) አዳምን የፈጠረው ከአፈር ሲሆን ይህም አፈር የተለያዩ እርከኖችን አልፏል፡፡ ከዛም በኋላ አላህ (ሱ.ወ) እስከፈቀደው ድረስ ቆይቶ ህይወትን አላህ ዘርቶበታል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَائِكَةِ إِنِّي خَالِقٌ بَشَرًا مِّن صَلْصَالٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ [١٥:٢٨]فَإِذَا سَوَّيْتُهُ

وَنَفَخْتُ فِيهِ مِن رُّوحِي فَقَعُوا لَهُ سَاجِدِينَ [١٥:٢٩]

‹‹ ጌታህም ለመላእክት ባለጊዜ (አስታውስ)፡፡ እኔ ሰውን ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጭቃ እፈጥራለሁ፡፡ (ፍጥረቱን) ባስተካከልኩትና በውስጡ ከመንፈሴ በነፋሁበትም ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ኾናችሁ ውደቁ፡፡»

- **በመቀጠልም የሰው ልጆችን መራቢያ ከጀርባቸው በሚወጣ ዘለግላጋ ፈሳሽ አደረገው**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

الَّذِي أَحْسَنَ كُلَّ شَيْءٍ خَلَقَهُ ۖ وَبَدَأَ خَلْقَ الْإِنسَانِ مِن طِينٍ [٣٢:٧]ثُمَّ جَعَلَ نَسْلَهُ مِن

سُلَالَةٍ مِّن مَّاءٍ مَّهِينٍ [٣٢:٨]ثُمَّ سَوَّاهُ وَنَفَخَ فِيهِ مِن رُّوحِهِ ۖ وَجَعَلَ لَكُمُ السَّمْعَ وَالْأَبْصَارَ

وَالْأَفْئِدَةَ ۚ قَلِيلًا مَّا تَشْكُرُونَ [٣٢:٩]

*‹‹ ያ የፈጠረውን ነገር ሁሉ ያሳመረው የሰውንም ፍጥረት ከጭቃ የጀመረው ነው፡፡ ከዚያም ዘሮቹን ከተንጣለለ፣ ከደካማ ውሃ ያደረገ ነው፡፡ ከዚያም (ቅርጹን) አስተካከለው፡፡ በእርሱ ውስጥም ከመንፈሱ ነፋበት፤ (ነፍስ ዘራበት)፡፡ ለእናንተም ጆሮዎችን፣ ዓይኖችንና ልቦችንም አደረገላችሁ፡፡ በጣም ጥቂትን ብቻ ታመሰግናላችሁ፡፡»*

- **የሰው ልጅ መሠረት አፈር እንደመሆኑ መጠን ወደ አፈር ይመለስና በመጪው ዓለም ደግሞ በድጋሚ ከመሬት ይቀሰቀሳል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

مِنْهَا خَلَقْنَاكُمْ وَفِيهَا نُعِيدُكُمْ وَمِنْهَا نُخْرِجُكُمْ تَارَةً أُخْرَىٰ [٢٠:٥٥]

«ከእርሷ (ከምድር) ፈጠርናችሁ፡፡ በእርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን፡፡ ከእርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን፡ ፡»

## የአዳም (ዐ.ሰ) ተክለ ሰውነት

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የአዳምን (ዐ.ሰ) ተክለ ሰውነት እንዲህ በማለት አብራርተዋል፡፡ "አላህ አደምን ስልሳ ክንድ ቁመት አድረጎ ፈጠረው፡፡ በመቀጠልም አላህ "ሂድና መላአኮቹን ሰላም በላቸው፡፡ ምን ብለው እንደሚመልሱልህም አድምጥ፡፡ አንድ እና የዘሮችህ ሰላምታ እነሱ የሚመልሱት ይሆናል፡፡" አለው፡፡ እሱም መላኢኮቹን ሄዶ "አሰላሙ አለይኩም" አላቸው፡፡ እነሱም "አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ" በለው "ወራህመቱላሂ" የሚለውን በመጨመር መለሱ፡፡ ጀነትን የሚገባ ሰው ሁሉ የሚገባው በአዳም (ዐ.ሰ) ቁመት ነው፡፡ ከዛን ግዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ቁመት እስከአሁን እየቀነሰ ነው፡፡" (ቡኻሪ)

## የአዳም ልጆች ልዩነት ምክንያት

የአዳም ልጆች በፀባይ፣ በመልክ እና በባህሪ በምን እንደሚለያዩ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ አብራርተዋል፡- "አላህ (ሱ.ወ) አዳምን ከሁሉም መሬት አይነት ፈጠረው፡፡ ስለዚህ የአዳም ልጆች እንደየመሬቱ ኤነት የተለያዩ ሆኑ፡፡ ከነሱም መሀል ቀይ፣ ጥቁር፣ ነጭ እና ቢጫ አለ፡፡ እንደዚሁም ከነሱ መሀል ገራገር ሰው፣ ሀዘንተኛ ሰው መጥፎ ሰው እና ጥሩ ሰው አለ፡፡" ሶኒህ ኢብኑ ሂባን፡፡

## የሰው ልጆች እናት የሆነችው ሀዋ አፈጣር

አላህ (ሱ.ወ) አዳምን (ዐ.ሰ) ከፈጠረ በኋላ ሀዋን ከአዳም ፈጥሯታል፡፡ ሰዎች እንዲባዙ እና አዳም (ዐ.ሰ) እርጋታ እንዲያገኝ ሚስቱን ሀዋን ከአዳም ግራ ጎድን ተፈጠረች፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

يَا أَيُّهَا النَّاسُ اتَّقُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَاحِدَةٍ وَخَلَقَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَبَثَّ مِنْهُمَا

رِجَالًا كَثِيرًا وَنِسَاءً ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ الَّذِي تَسَاءَلُونَ بِهِ وَالْأَرْحَامَ ۚ إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلَيْكُمْ رَقِيبًا

[٤:١]

«እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርስዋም መቀናጆዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ፡፡ ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ፡፡ አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና፡፡ ››

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፦ “በአላህ እና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ጎረቤቱን አያስቸግርም፡፡ ስለሴቶች በጥሩ ነገር አደራ፡፡ ሴቶች የተፈጠሩት ከጎድን አጥንት ነው፡፡ በእርግጥም ከጎድን በጣም የጎበጠው ክፍል የላይኛው ነውው፡ አስተካክለዋለሁ ብለህ ከተነሳህ ትሰብረዋለህ፡፡ ዝም ካልከው ደግሞ ተጣሞ ይቀራልና ስለሴቶች ጉዳይ በጥሩ ነገር አደራ፡፡” (ሶኒህ ቡኻሪ)

## አዳም እና የሀዋ መኖሪያ

አደም (ዐ.ሰ) ወንጀል ሰርቶ ከመባረራቸው በፊት መኖሪያቸው በጀነት ነበር፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፦

وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَائِكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ أَبَىٰ [٢٠:١١٦]

«ለመላእክትም ለአዳም ስገዱ ባልን ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ሰገዱም፤ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር እምቢ አለ፡፡»

فَقُلْنَا يَا آدَمُ إِنَّ هَٰذَا عَدُوٌّ لَّكَ وَلِزَوْجِكَ فَلَا يُخْرِجَنَّكُمَا مِنَ الْجَنَّةِ فَتَشْقَىٰ [٢٠:١١٧]

«አልንም «አደም ሆይ! ይህ ላንተም ለሚስትህም በእርግጥ ጠላት ነው፡፡ ስለዚህ ከገነት አያውጣችሁ፤ ትለፋለህና፡፡ ››

إِنَّ لَكَ أَلَّا تَجُوعَ فِيهَا وَلَا تَعْرَىٰ [٢٠:١١٨]

«ለአንተ በእርሷ ውስጥ አለመራብና አለመታረዝ አለህ፡፡»

وَأَنَّكَ لَا تَظْمَأُ فِيهَا وَلَا تَضْحَىٰ [٢٠:١١٩]

«አንተም በርሷ ውስጥ አትጠማም፤ ፀሐይም አትተኮስም፡፡»

فَوَسْوَسَ إِلَيْهِ الشَّيْطَانُ قَالَ يَا آدَمُ هَلْ أَدُلُّكَ عَلَىٰ شَجَرَةِ الْخُلْدِ وَمُلْكٍ لَّا يَبْلَىٰ [٢٠:١٢٠]

«ሰይጣንም ወደርሱ ጎተጎተ «አደም ሆይ! በመዘውተሪያ ዛፍ በማይጠፋ ንግሥናም ላይ ላመላክትህን= አለው፡፡»

فَأَكَلَا مِنْهَا فَبَدَتْ لَهُمَا سَوْآتُهُمَا وَطَفِقَا يَخْصِفَانِ عَلَيْهِمَا مِن وَرَقِ الْجَنَّةِ ۚ وَعَصَىٰ آدَمُ رَبَّهُ فَغَوَىٰ [٢٠:١٢١]

«ከእርሷም በልሉ፡፡ ለእነርሱም ኀፍረተ ገላቸው ተገለጸች፡፡ ከገነትም ቅጠል በላያቸው ላይ ይለጥፉ ጀመር፡፡ አደምም የጌታውን ትእዛዝ (ረስቶ) ጣሰ፡፡ (ከፈለገው መዘውተር) ተሳሳተም፡፡»

ثُمَّ اجْتَبَاهُ رَبُّهُ فَتَابَ عَلَيْهِ وَهَدَىٰ [٢٠:١٢٢]

«ከዚያም ጌታው መረጠው ከእርሱም ጸጸቱን ተቀበለው መራውም፡፡»

قَالَ اهْبِطَا مِنْهَا جَمِيعًا ۖ بَعْضُكُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ ۖ فَإِمَّا يَأْتِيَنَّكُم مِّنِّي هُدًى فَمَنِ اتَّبَعَ

هُدَايَ فَلَا يَضِلُّ وَلَا يَشْقَىٰ [٢٠:١٢٣]

«አላቸው «ከፊላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ሁላችሁም ከእርሷ ውረዱ ከእኔም የኾነ መሪ ቢመጣላችሁ መሪየን የተከተለ አይሳሳትም አይቸገርምም፡፡ >>

وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ أَعْمَىٰ [٢٠:١٢٤]

«ከግሣጼዬም የዞረ ሰው ለእርሱ ጠባብ ኑሮ አለው፡፡ በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን፡፡»

## <u>ወደሰዎች መልዕክተኞችን የመላክ አጀማመር</u>

- ከአዳም (ዐ.ሰ) አስር ክፍለዘመን በኋላ ሰዎች ከእውነተኛው መንገድ ማፈንገጥ ስለጀመሩ አላህ መልዕክተኞችን መላክ ጀመረ፡፡ ኢብኑ ኢባስ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- “ከኒህ (ዐ.ሰ) እና ከአዳም (ዐ.ሰ) መሀል አስር ክፍለዘመን ያህል ክፍተት ነበር፡፡ በዚህን ግዜ ውስት የሰው ዘር ሁሉ በትክክለኛው መንገድ ላይ ነበሩ፡፡ ከዛ በኋላ ግን ተለያዩ፡፡ ከዛም አላህ አስጠንቃቂ እናአብሳሪ የሆኑ ነብዮችን መላክ ጀመረ፡፡”
- ይህ ልዩነት ከመጣ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደሰዎች የተላከው ነብይ ታዲያ ኒህ (ዐ.ሰ) ነበሩ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

إِنَّا أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ كَمَا أَوْحَيْنَا إِلَىٰ نُوحٍ وَالنَّبِيِّينَ مِن بَعْدِهِ ۚ

«እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን፡፡»

- አላህ (ሱ.ወ) የተወሰኑ ነብዮችን ስም በቁርአን ጠቅሶልናል፡፡

  አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَتِلْكَ حُجَّتُنَا آتَيْنَاهَا إِبْرَاهِيمَ عَلَىٰ قَوْمِهِ ۚ نَرْفَعُ دَرَجَاتٍ مَّن نَّشَاءُ ۗ إِنَّ رَبَّكَ حَكِيمٌ

عَلِيمٌ [٦:٨٣]

«ይህችም ማስረጃችን ናት፡፡ ለኢብራሂም በሕዝቦቹ ላይ (አስረጅ እንድትኾን) ሰጠናት፡፡ የምንሻውን ሰው በደረጃዎች ከፍ እናደርጋለን፡፡ ጌታህ ጥበበኛ ዐዋቂ ነውና፡፡»

وَوَهَبْنَا لَهُ إِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ ۚ كُلًّا هَدَيْنَا ۚ وَنُوحًا هَدَيْنَا مِن قَبْلُ ۖ وَمِن ذُرِّيَّتِهِ دَاوُودَ

وَسُلَيْمَانَ وَأَيُّوبَ وَيُوسُفَ وَمُوسَىٰ وَهَارُونَ ۚ وَكَذَٰلِكَ نَجْزِي الْمُحْسِنِينَ [٦:٨٤]

‹‹ለርሱም ኢስሐቅን (የልጅ ልጁን) ያዕቁብንም ሰጠነው። ሁሉንም መራን። ኑሕንም በፊት መራን። ከዘሮቹም ዳውድን፣ ሱለይማንንም፣ አዩብንም፣ ዩሱፍንም፣ ሙሳንም፣ ሃሩንንም (መራን)። እንደዚሁም በጎ ሰሪዎችን እንመነዳለን።››

وَزَكَرِيَّا وَيَحْيَىٰ وَعِيسَىٰ وَإِلْيَاسَ ۖ كُلٌّ مِّنَ الصَّالِحِينَ [٦:٨٥]

‹‹ዘከሪያንም፣ የሕያንም፣ ዒሳንም፣ ኢልያስንም (መራን)። ሁሉም ከመልካሞቹ ናቸው።››

وَإِسْمَاعِيلَ وَالْيَسَعَ وَيُونُسَ وَلُوطًا ۚ وَكُلًّا فَضَّلْنَا عَلَى الْعَالَمِينَ [٦:٨٦]

‹‹ኢስማዒልንም፣ አልየስዕንም፣ ዩኑስንም፣ ሉጥንም (መራን)። ሁሉንም በዓለማት ላይ አበለጥናቸውም።››

وَمِنْ آبَائِهِمْ وَذُرِّيَّاتِهِمْ وَإِخْوَانِهِمْ ۖ وَاجْتَبَيْنَاهُمْ وَهَدَيْنَاهُمْ إِلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ [٦:٨٧]

‹‹ከአባቶቻቸውም፣ ከዘሮቻቸውም፣ ከወንድሞቻቸውም (መራን)። መረጥናቸውም፤ ወደ ቀጥታውም መንገድ መራናቸው።››

“ “ “ “ :-

قُولُوا آمَنَّا بِاللَّهِ وَمَا أُنزِلَ إِلَيْنَا وَمَا أُنزِلَ إِلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ وَالْأَسْبَاطِ

وَمَا أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَمَا أُوتِيَ النَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُ

مُسْلِمُونَ [٢:١٣٦]

«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ።››

"        "        "        "    :-

وَإِسْمَاعِيلَ وَإِدْرِيسَ وَذَا الْكِفْلِ ۖ كُلٌّ مِّنَ الصَّابِرِينَ [٢١:٨٥]

«ኢስማዒልንም ኢድሪስንም ዙልኪፍልንም (አስታውስ)፡፡ ሁሉም ከታጋሾቹ ናቸው፡፡»

- *ከመልዕክተኞችም መሀል አላህ (ሱ.ወ) ስለነሱ ያልነገረን አለ፡፡*

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَرُسُلًا قَدْ قَصَصْنَاهُمْ عَلَيْكَ مِن قَبْلُ وَرُسُلًا لَّمْ نَقْصُصْهُمْ عَلَيْكَ ۚ

«ከዚህም በፊት በአንተ ላይ በእርግጥ የተረከናቸውን መልክተኞች ባንተ ላይም ያልተረከናቸውን መልክተኞች (እንደላክን ላክንህ)፡፡»

- *አላህ (ሱ.ወ) ከግዜ ወደግዜ ሰዎችን ጌታቸውን አንድ አድርገው እንዲገዙ የሚጠሩ መልዕክተኞች ይልክ ነበር፡፡ ታዲያ ሁሉም መልዕክተኞች ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያሉት ጥሪያቸው አላህን በንግግርም፣ በልብም ሆነ በተግባሪ በአምልኮት ላይ አንድ ማድረግ እና ከሱ ውጪ በሚመለክ ነገር ሁሉ መካድ በሚለው ላይ ያተኮረ ነበር፡፡*

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولًا أَنِ اعْبُدُوا اللَّهَ وَاجْتَنِبُوا الطَّاغُوتَ ۖ فَمِنْهُم مَّنْ هَدَى اللَّهُ وَمِنْهُم مَّنْ حَقَّتْ عَلَيْهِ الضَّلَالَةُ ۚ فَسِيرُوا فِي الْأَرْضِ فَانظُرُوا كَيْفَ كَانَ عَاقِبَةُ الْمُكَذِّبِينَ

[١٦:٣٦]

«በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ «አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል፡፡ ከእነሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አልለ፡፡ ከእነሱም ውስጥ በእርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አልለ፡፡ በምድርም ላይ ኺዱ፤ የአስተባባዮችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከቱ፡፡»

*ነገር ግን የሚተዳደሩበት ህግጋት እና ደንቦች ከህዝብ ወደ ህዝብ የሚለያይ ነበር፡፡ አንዱ ህዝብ ላይ ግዴታ ያልነበረ ነገር አንዱ ህዝብ ላይ ግዴታ ይሆናል፡፡*

*የመለያየቱ ዋና አላማም ሰዎች ለአላህ (ሱ.ወ) ያላቸውን ፍፁም መታዘዝ ለመፈተን ነው፡፡አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-*

لِكُلٍّ جَعَلْنَا مِنكُمْ شِرْعَةً وَمِنْهَاجًا ۚ وَلَوْ شَاءَ اللَّهُ لَجَعَلَكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَلَٰكِن لِّيَبْلُوَكُمْ فِي مَا آتَاكُمْ ۖ فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ ۚ

«ከእናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፡፡ አላህም በሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር፡፡ ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ (ለያያችሁ)፡፡ በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፤»

የነብዩ ማዕረግ በመጨረሻም የተሰጠው ለነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሆን፣ እሳቸውም ለሰውልጁ በሙሉ የተላኩ ናቸው፡፡አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَا أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ اللَّهِ وَخَاتَمَ النَّبِيِّينَ ۗ

«ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፡፡ ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፡፡»

- በችግር ግዜ መጠጊያ እንደሆነ እና ለሰው ልጅ የነፍስ ደስታ፣ የህይወት እርጋታ እና የአዕምሮ እረፍት ሊያገኝ የሚችለው በዚህ እንደሆነ ማስተማር ነው፡፡›

  አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَالَمِينَ [٢١:١٠٧]

<<(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡»

በአላህ አማን የሆኑ ሰዎች ደስተኛ ስለመሆናቸው ማስጃ የሚሆነን ነገር ፈጣሪ በመኖሩ ------- ያሉ ሰዎች የሚኖሩበትን የፍራት፣ የጭንቀት እና የመዋዠቅ ህይወት ስንመለከት ነው፡፡ ይህንን አስቀያሚ ህይወታቸውን ለመርሳት አደንዛዥ እፅ፣ አስካሪ መጠጥ እና የመሳሰሉት ነገር ላይ ሲያዘወትሩ ይስተዋላል፡፡ ኧረ እንደውም አንዳንዶቹ አላህ ይጠብቀንና እራሳቸውንም ለማጥፋት ሲሞክሩ ታያለህ፡፡ ይህንን በማድረግ ደስታን የሚያገኙ መስሏቸው ተታለዋል፡፡ በእነዚህ ነገራቶ ሊያተርፉ የሚችሉት ደስታ ጊዜያዊ እና ጎዶሎ ነው፡፡ ምሳሌያቸውም ጨዋማ ውሃን እንደሚጠጣ ሰው ነው፡፡ ይህ ውሃ አይደለም ጥምን ሊቆርጥለት ቀርቶ በጥሙ ላይ ጥምን ነው የሚጨምርለት፡፡ ነገር ግ በአላህ በማመን፣ ለሱ በመተናነስ፣ ትዕዛዛቶቹን በማክበር እና አስተምህሮቶቹን በመከተል ትክክለኛውን ደስታ እና የነፍስ እርካታ ማግኘት ይቻላል፡፡

## <u>የሰው ልጅ እና የአፈጣጠሩ እርከን በእስልምና እይታ</u>

- **የሰው ልጅ አላህ (ሱ.ወ) ባማረ ቁመና የፈጠረው ፍጡር ነው፡፡**

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይሏል፡-**

لَقَدْ خَلَقْنَا الْإِنسَانَ فِي أَحْسَنِ تَقْوِيمٍ [٩٥:٤]

«ሰውን በጣም በአማረ አቋም ላይ ፈጠርነው፡፡»

- **አስተካክሎ እና አደላድሎ ፈጠረው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

يَا أَيُّهَا الْإِنسَانُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ الْكَرِيمِ [٨٢:٦]

«አንተ ሰው ሆይ! በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ?››

الَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّاكَ فَعَدَلَكَ [٨٢:٧]

«በዚያ በፈጠረህ አካለ ሙሉም ባደረገህ ባስተካከለህም፡፡»

فِي أَيِّ صُورَةٍ مَّا شَاءَ رَكَّبَكَ [٨٢:٨]

«በማንኛውም በሻው ቅርፅ በገጣጠመህ (ጌታህ ምን አታለለህ)፡፡»

- **በምርጥ እና በተሟላ ቅርፅ ፈጠረው፡፡ " " " " :-**

اللَّهُ الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الْأَرْضَ قَرَارًا وَالسَّمَاءَ بِنَاءً وَصَوَّرَكُمْ فَأَحْسَنَ صُوَرَكُمْ وَرَزَقَكُم مِّنَ

الطَّيِّبَاتِ ۚ ذَٰلِكُمُ اللَّهُ رَبُّكُمْ ۖ فَتَبَارَكَ اللَّهُ رَبُّ الْعَالَمِينَ [٤٠:٦٤]

«አላህ ያ ምድርን መርጊያ ሰማይንም ጣሪያ ያደረገላችሁ ነው፡፡ የቀረጻችሁም ቅርጻችሁንም ያሳመረ ከጣፋጮችም ሲሳዮች የሰጣችሁ ነው፡፡ ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው፡፡ የዓለማትም ጌታ አላህ ላቀ፡፡»

- **ከሁሉም ፍጡ አስበለጠን አከበረንም፡፡ " " " " :-**

وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِي آدَمَ وَحَمَلْنَاهُمْ فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ وَرَزَقْنَاهُم مِّنَ الطَّيِّبَاتِ وَفَضَّلْنَاهُمْ عَلَىٰ كَثِيرٍ

مِّمَّنْ خَلَقْنَا تَفْضِيلًا [١٧:٧٠]

«የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው፡፡ በየብስና በባህርም አሳፈርናቸው፡፡ ከመልካሞችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው፡፡ ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው፡፡»

- **በዚህ አለም ውስጥ ያሉ ነገራቶን ሁሉ አጋራልን፡፡ " " " " :-**

وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ جَمِيعًا مِّنْهُ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ [٤٥:١٣]

«ለናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ ከእርሱ ሲኾን የገራላችሁ ነው፡፡ በዚህ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ተዓምራት አልለበት፡፡»

**የሰው ልጅ እራሱን የቻለ ፍጡር እንጂ ከሌላ ፍጡር በስነተፈጥሮ ከግዚያት በኋላ የተቀየረ ፍጡር አይደለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

الَّذِي أَحْسَنَ كُلَّ شَيْءٍ خَلَقَهُ ۖ وَبَدَأَ خَلْقَ الْإِنسَانِ مِن طِينٍ [٣٢:٧]

«ያ የፈጠረውን ነገር ሁሉ ያሳመረው የሰውንም ፍጥረት ከጭቃ የጀመረው ነው፡፡»

**እንደዚህ ለሰው ልጅ ትልቅነት ቦታ ሰጥቶ የሚናገረው እስልምና እና የሰው ልጀ ከእንስሳ ጋር የሚያወዳድሩ አስተሳሰቦች ልዩነታቸው ምንኛ የሰነፍ ነው? ቁአን የሰውን ልጅ በስሜቱ ተገዥ እስካልሆነ ድረስ ስለ አስገራሚ ሰማይና ምድር አፈጣረር በተሰጠው ብሩህ አዕምሮ ማሰብ፣ በአይኑ ማየት፣ በጆሮው መስማት እስካልተሳነው ድረስ እንደ እንስሳት ገልፆት አያውቅም፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَلَقَدْ ذَرَأْنَا لِجَهَنَّمَ كَثِيرًا مِّنَ الْجِنِّ وَالْإِنسِ ۖ لَهُمْ قُلُوبٌ لَّا يَفْقَهُونَ بِهَا وَلَهُمْ أَعْيُنٌ لَّا يُبْصِرُونَ بِهَا وَلَهُمْ آذَانٌ لَّا يَسْمَعُونَ بِهَا ۚ أُولَٰئِكَ كَالْأَنْعَامِ بَلْ هُمْ أَضَلُّ ۚ أُولَٰئِكَ هُمُ الْغَافِلُونَ [٧:١٧٩]

«ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን ለገሀነም በእርግጥ ፈጠርን፡፡ ለእነርሱ በርሳቸው የማያውቁባቸው ልቦች አሏቸው፡፡ ለእነሱም በሳቸው የማያዩባቸው ዓይኖች አሉዋቸው፡፡ ለእነሱም በሳቸው የማይሰሙባቸው

ጆሮዎች አሉዋቸው፡፡ እነዚያ እንደ እንስሳዎች ናቸው፡፡ ይልቁንም እነርሱ በጣም የተሳሳቱ ናቸው፡፡ እነዚያ ዘንጊዎቹ እነርሱ ናቸው፤»

ምክንያቱም እነዚህን ስጦዎች በአግባቡ ለማስተንተን የተጠቀማቸው ሰው ከአላህ ፍድ ጋር አላህን ወደማወቅ እና በእሱ ወደማመን እንደሚመሩተ ግልፅ ነው፡፡ታላቁ አሊም ኢብኑን ቀይም እንዲህ ይላሉ፡፡ "አላህ (ሱ.ወ) ከፍጡራኖቹ ሁሉ የሰውን ልጅ የተለየ አድርጎል፣ አክብሮታል፣ አልቆለታል፣ ለራሱ ፈጥሮታል፣ የተቀረውን ነገር ሁሉ ለሱ (ሰው) ፈጥሮታል፣ በእውቀት እና በፍቅር መርጦታል፣ ለሌላ ፍጡር ባልሰጠው ነገር አቅርቦታል፣ በሰማይ፣ በምድር እና በመሀላቸው ያሉትን ነገራቶች ለሱ------------፣ ለአላህ ቅርብ የሆኑ መላኢኮችን ጭምር --------- ምክንያቱም የሰው ልጅ አገልጋይ አድርጓቸዋል፡፡ በእንቅልፍ፣ በንቃት፣ ሲቆም እንዲሁም ሲቀመጥ እንዲጠብቁት አድርጓቸዋል፡፡ መፅሀፋን አውርዶለታል፣ መልዕክተኞቹን ልኮ አናግሮታል፡፡ ከነሱ መሀልም ከፊሉን ወዳጁ አድርጎለታል፣ ከፊሉ አናግሮታል፣ ከፊሎቹን ደግሞ ወዳጆቹ አድርጓቸዋል፡፡ የሚስጥሩ ማስቀመጪ፣ የጥበቡ መኖሪያ እና የፍቅሩ ቦታ አደረጋቸው፡፡ ጀነት እና ጀሀነምን ፈጥሮላቸዋል፡፡ የአላህ መፍጠር፣ ትዕዛዝ፣ ሽልማት እና ቅጣት በሰው ዙሪ ይሽከረከራል፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ልዩ ፍጡር ነው፡፡ ትዕዛዝ እና ክልከላ የሚመለከቱት የሰውን ልጅ ሲሆን በዚህ መሠረትም ሽልማት እና ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡ (መዳሪጁ ሳሊኪን 232/1)

## የሰው ልጅ የአፈጣጠር እርከን

- ሲጀመር የሰው ልጅ የሚታሰው ነገረ እንኳ አልነበረም፡፡

  አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

هَلْ أَتَىٰ عَلَى الْإِنسَانِ حِينٌ مِّنَ الدَّهْرِ لَمْ يَكُن شَيْئًا مَّذْكُورًا [٧٦:١]

«በሰው ላይ የሚታወስ ነገር ሳይኾን ከዘመናት የተወሰነ ጊዜ በእርግጥ አልፎበታል፡፡»

- በመቀጠልም የአፈጣጠሩ መጀመሪያ ቆሻሻ እና ዘለግላጋ ፈሳሽ ሆነ፡፡

  አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

أَلَمْ نَخْلُقكُّم مِّن مَّاءٍ مَّهِينٍ [٧٧:٢٠]

«ከደካማ ውሃ አልፈጠርናችሁምን?››

فَجَعَلْنَاهُ فِي قَرَارٍ مَّكِينٍ [٧٧:٢١]

«በተጠበቀ መርጊያ ውስጥም (በማሕፀን) አደረግነው፡፡»

إِلَىٰ قَدَرٍ مَّعْلُومٍ [٧٧:٢٢]

«እስከ ታወቀ ልክ ድረስ፡፡ መጠንነውም፤ ምን ያማርንም»

فَقَدَرْنَا فَنِعْمَ الْقَادِرُونَ [٧٧:٢٣]

ኢማም አልገዛሊ (ረሂመሁሏህ) እንዲህ ይላሉ፡-
“እስኪ የሰውልጅ ወደ አላህ ፀጋ ይመልከት፡፡ እንዴት ከውርደት፣ ከዝቅጠት እና ከቆሻሻ አሁን ወዳለበት ክብር እንዳመጣው ይመልከት፡፡ ካለመኖር ወደመኖር፣ ከሞት ወደህይወት፣ ከዲዳነት ወደተናጋሪነትት ከኢምንት ወደ ተመልካችነት፣ ከደካማነት ወደ ብርታት፣ ከመሀይምነት ወደ አዋቂነት፣ ከጥመት በኋላ ወደ ቅናቻ፣ ከመሣን በኋላ ወደ ችሎታ፣ ከድህነት በኋላ ወደ ሀብት ሁሉን ነገር ትተን በራሱ ምንም ነገር ያልነበረ ነበር ምንም ካልነበረ ነገር የበለጠ ወራዳ ምን አለ? ከዛም በአላህ ፍቃድ አንዳች ነገር የሚባል ሆነ፡፡” (አህያ ኡሉመዲን)

**ሰው ልጅ የተገኘው ከምንድን ነው?**

አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጅ ለመፈጠር የግድ የወንድ ዘር ፈሳሽ እና የሴት እንቁላል መገናኘት የግድ መሆኑን አብራርቷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

ሰውም ከምን እንደተፈጠረ ይመልከት፡፡ فَلْيَنظُرِ الْإِنسَانُ مِمَّ خُلِقَ [٨٦:٥]

ከተስፈንጣሪ ውሃ ተፈጠረ፡፡ خُلِقَ مِن مَّاءٍ دَافِقٍ [٨٦:٦]

ከጀርባና ከእርግብግብቶች መካከል የሚወጣ ከኾነ (ውሃ)፡፡ يَخْرُجُ مِن بَيْنِ الصُّلْبِ وَالتَّرَائِبِ [٨٦:٧]

አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጅ የሚባዛው እና ዘር የሚኖረው በዚህ መንገድ ብቻ መሆኑን ገልጿል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እነዲህ ላል፡-

وَهُوَ الَّذِي خَلَقَ مِنَ الْمَاءِ بَشَرًا فَجَعَلَهُ نَسَبًا وَصِهْرًا ۗ وَكَانَ رَبُّكَ قَدِيرًا [٢٥:٥٤]

«እርሱም ያ ከውሃ ሰውን የፈጠረ፣ የዝምድናና የአማችም ባለቤት ያደረገው ነው፡፡ ጌታህም ቻይ ነው፡፡»

አላህ (ሱ.ወ) ይህ አዲስ የተፈጠረው ሽል በአላህ ፍቃድ እስኪወጣ ድረስ በገለልታ ቦታ፣ ሰላም ባለው እና ውጫዊ ነገራቶች ተጽዕኖ ከሚያደርጉበት ቦታ እንደሚቆይ ተናግሯል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

أَلَمْ نَخْلُقكُّم مِّن مَّاءٍ مَّهِينٍ [٧٧:٢٠] ከደካማ ውሃ አልፈጠርናችሁምን?

فَجَعَلْنَاهُ فِي قَرَارٍ مَّكِينٍ [٧٧:٢١] በተጠበቀ መርጊያ ውስጥም (በማሕፀን) አደረግነው፡፡

إِلَىٰ قَدَرٍ مَّعْلُومٍ [٧٧:٢٢] እስከ ታወቀ ልክ ድረስ፡፡ መጠንነውም፤ ምን ያማርንም

فَقَدَرْنَا فَنِعْمَ الْقَادِرُونَ [٧٧:٢٣] መጣኞች ነን!

ይህ አዲስ ፍጡር አላህ ከፈቀደ ግዜው ደርሶ ይህን አለም እስከሚቀላቀል ድረስ በሶስት ጨለማ ውስጥ እርከኖችን እያለፈ እንደሚቆይ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ በማለት ተናግሯል፡፡

يَخْلُقُكُمْ فِي بُطُونِ أُمَّهَاتِكُمْ خَلْقًا مِّن بَعْدِ خَلْقٍ فِي ظُلُمَاتٍ ثَلَاثٍ ۚ

«በእናቶቻችሁ ሆዶች ውስጥ በሦስት ጨለማዎች ውስጥ ከመፍጠር በኋላ (ሙሉ) መፍጠርን ይፈጠራችኋል፡፡»

## የሰው ልጅ የሚያልፍበት የእድገት እርከተኖች

1. የመጀመሪያው እርከን፡- የተቀላቀለ የፋትወት ጠብታ ሲሆን እሱም የወንድ እና የሴተ የዘር ፈሳሽ ቅልቅል ውጤት ነው፡፡

   አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَأَنَّهُ خَلَقَ الزَّوْجَيْنِ الذَّكَرَ وَالْأُنثَىٰ [٥٣:٤٥] እርሱም ሁለቱን ዓይነቶች ወንድንና ሴትን ፈጠረ፡

مِن نُّطْفَةٍ إِذَا تُمْنَىٰ [٥٣:٤٦] ከፍትወት ጠብታ (በማህጸን ውስጥ) በምትፈሰስ ጊዜ

አላህ ከፈቀደ የወንድ የዘር ፈሳሽ ከሴቷ እንቁላል ጋር ይገናኛል፡፡ ይህ ከሆነ የሰው ልጅ የእድገት እርከን ይጀመራል፡፡ መገናኘት ካልቻሉ ግን የወንድ ዘር ፈሳሽ ይሞትና ሰው ሊፈጠር አይችልም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

إِنَّا خَلَقْنَا الْإِنسَانَ مِن نُّطْفَةٍ أَمْشَاجٍ نَّبْتَلِيهِ فَجَعَلْنَاهُ سَمِيعًا بَصِيرًا [٧٦:٢]

«እኛ ሰውን (በሕግ ግዳጅ) የምንሞከረው ስንኾን ቅልቅሎች ከኾኑ የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው:: ሰሚ ተመልካችም አደረግነው::»

**በዚህ ደረጃ ላይ የሰወ ልጅ ባህሪ ይመጠናል::**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:-**

قُتِلَ الْإِنسَانُ مَا أَكْفَرَهُ [٨٠:١٧]

ሰው ተረገመ፤ ምን ከሓዲ አደረገው?

مِنْ أَيِّ شَيْءٍ خَلَقَهُ [٨٠:١٨]

(ጌታው) በምን ነገር ፈጠረው? (አያስብምን?)

مِن نُّطْفَةٍ خَلَقَهُ فَقَدَّرَهُ [٨٠:١٩]

ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው፤ መጠነውም::

**እንዲሁም ፆታውም በዚህ ግዜ ይወሰናል::**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:-**

لِّلَّهِ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ يَخْلُقُ مَا يَشَاءُ ۚ يَهَبُ لِمَن يَشَاءُ إِنَاثًا وَيَهَبُ لِمَن يَشَاءُ الذُّكُورَ [٤٢:٤٩]

«የሰማያትና የምድር ንግሥና የአላህ ነው:: የሚሻውን ይፈጥራል:: ለሚሻው ሰው ሴቶችን (ልጆች) ይሰጣል:: ለሚሻውም ሰው ወንዶችን ይሰጣል::»

أَوْ يُزَوِّجُهُمْ ذُكْرَانًا وَإِنَاثًا ۖ وَيَجْعَلُ مَن يَشَاءُ عَقِيمًا ۚ إِنَّهُ عَلِيمٌ قَدِيرٌ [٤٢:٥٠]

«ወይም ወንዶችና ሴቶች አድርጎ ያጠናዳቸዋል:: የሚሻውንም ሰው መካን ያደርገዋል:: እርሱ ዐዋቂ ቻይ ነውና::»

**በሌላ አንቀጽ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:-**

هُوَ الَّذِي يُصَوِّرُكُمْ فِي الْأَرْحَامِ كَيْفَ يَشَاءُ ۚ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ [٣:٦]

«እርሱ ያ በማሕጸኖች ውስጥ እንደሚሻ አድርጎ የሚቀርጻችሁ ነው፡፡ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ አሸናፊው ጥበበኛው ነው፡፡»

**የፍትወት ጠብታው ድብልቅ ማህፀን ላይ መጠበቅ ካልለም ህይወት ሊቀጥል አይችልም፡፡ ከማህፀን ይወገዳል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

اللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَحْمِلُ كُلُّ أُنثَىٰ وَمَا تَغِيضُ الْأَرْحَامُ وَمَا تَزْدَادُ ۖ وَكُلُّ شَيْءٍ عِندَهُ بِمِقْدَارٍ

[١٣:٨]

«አላህ ሴት ሁሉ የምታረግዘውን ያውቃል፡፡ ማሕጸኖችም የሚያጎድሉትን የሚጨምሩትንም (ያውቃል)፡፡ ነገሩም ሁሉ እርሱ ዘንድ በልክ የተወሰነ ነው፡፤»

**ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) ፈቅዶ የፍትወት ጠብታ ድብልቁ የማህፀን ግድግዳ ላይ መጣበቅ ከቻለ ወደ ሚቀጥለው እርከን ይሸጋገራል፡፡ ማህፀን ላይም ሰርስሮ በመግባት እራሱን መመገብ ይጀምራል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَنُقِرُّ فِي الْأَرْحَامِ مَا نَشَاءُ إِلَىٰ أَجَلٍ مُّسَمًّى ثُمَّ نُخْرِجُكُمْ طِفْلًا

«የምንሻውንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በማሕፀን ውስጥ እናረጋዋለን፡፡ ከዚያም ሕፃን ሆናችሁ እናወጣችኋለን፡፡»

2. **ሁለተኛው እርከን፡- የረጋ ደም፡-** በዚህ ስም የተሰየመበት ምክንያት በዚህን ግዜ በከብቶች ላይ **ተለጥፎ ደም እንደሚመጥ ጥገኛ ነፍሳት ፅንሱ የማህፀን ግድግዳ ላይ ተጣብቆ ምግቡን ከማህጸን ደም ስለሚያገኝ ነው፡፡**

   **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ — اقْرَأْ بِاسْمِ رَبِّكَ الَّذِي خَلَقَ [٩٦:١]

ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡ — خَلَقَ الْإِنسَانَ مِنْ عَلَقٍ [٩٦:٢]

ሰው ስድ ኾኖ መትተውን ይጠረጥራልን? — أَيَحْسَبُ الْإِنسَانُ أَن يُتْرَكَ سُدًى [٧٥:٣٦]

የሚፈሰስ ከኾነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን? [٧٥:٣٧] أَلَمْ يَكُ نُطْفَةً مِّن مَّنِيٍّ يُمْنَىٰ

ከዚያም የረጋ ደም ኾነ (አላህ ሰው አድርጎ) ፈጠረውም፡፡ አስተካከለውም፡፡ ثُمَّ كَانَ عَلَقَةً فَخَلَقَ فَسَوَّىٰ

ከእርሱም ሁለት ዓይነቶችን ወንድና ሴትን አደረገ፡፡ [٧٥:٣٩] فَجَعَلَ مِنْهُ الزَّوْجَيْنِ الذَّكَرَ وَالْأُنثَىٰ

3. ሶስተኛው እርከን፡- **ልምጥ ስጋ፡-** በዚህ ስም የተሰየመበትም ምክንያት ልክ እንደታጀከ ስኮ የሚመስል ቅርፅ ስለሚፈጥር ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

فَخَلَقْنَا الْعَلَقَةَ مُضْغَةً فَخَلَقْنَا الْمُضْغَةَ عِظَامًا

*«የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን፡፡ ቁራጪንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፡፡»*

ኢብኑ መስኡድ (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ሚከተለው ሀዲስ ላይ እነዚህ የሰው ልጅ የእድገት እርከኖች የሚወስዱት ግዜ ጭምር ተወስኖ ተብራርቷል፡፡ “አንዳችሁ በእናታችሁ ማህፀን ውስጥ 40 ቀን ያህል ፍትወት ጠብታ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ልክ እንደዚሁም (ለ40 ቀን) ያህል የረጋ ደም ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም (ለ40 ቀን) ልምጥ ስጋ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዚያም መላኢካ ተልኮ ነፍስ እንደነፋበት እና 4 ነገር እንዲመዘግብ ይታዘዛል፡፡ ሲሳዩን፣ የመሞቻ ቀኑን፣ ስራውን፣ ጥሩ ወይም መጥፎ ሰው መሆኑን ይፅፋል፡፡ ከሱ ውጪ ሌላ አምላክ በሌለው ይሁንብን፡፡ አንዳችሁ እኮ ጀነት ለመግባት የክንድ ያህል እስከሚቀረውድረስ የጀነት ሰዎችን ስራ ሲሰራ ይኖራል፡፡ ከዛም በፊት የተፃፈው ውሳኔ ይመጣበት እና የእሳት ሰዎችን ስራ ሰርቶ ወደ እሳት ገባል፡፡ እንደዚሁም አንዳችሁ ጀሀነም ለመግባት የክንደ ያህል እስከሚቀረው ድረስ የሚስት ሰዎችን ስራ ሲሰራ ይኖራል፡፡ ከዛም በፊት የተፃፈው ውሳኔ ይመጣበት እና የጀነት ሰዎችን ስራ ሰርቶ ወደጀነት ይገባል” (ቡኻሪና ሙስሊም)

## <u>ህይወት ምንድናት?</u>

የማናያቸውና በስሜት ህዋሶቻችን የማንደርስበት ነገር ቢሆንም በመኖሯ እናምንበታለን፡፡ ምክንያቱም እሷን ባናይ የሷን ውጤት እና ተፅዕኖ ተመልክተናል፡፡ ሕይወት አላህ (ሱ.ወ) ስለመኖሩ ካሉት ጠንካራ ማስረጃ ውስጥ ናትት፡ ማቴሪያሊስቶች አላህ (ሱ.ወ) ስለመኖሩ ተጨባጭ

የሆነን ማስረጃ ይፈልጋ፡፡ ነገር ግን ህይወትን አይቷትም ሆነ ነክቷት የሚያውቅ ሰው ባይኖርም መኖሯን ግን አይክዱም፡፡ ህይወት የመኖርን ውጤት ግን ተመልክተዋል፡፡ ህወት ከአላህ (ሱ.ወ) ውጪ የሚያውቃት ከሱ ሚስጥሮቸ መሀል አንዷ ናት፡፡ ለምርምርም ሆነ ለጥናት ቦታ እና ፋይዳ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَيَسْأَلُونَكَ عَنِ الرُّوحِ ۖ قُلِ الرُّوحُ مِنْ أَمْرِ رَبِّي وَمَا أُوتِيتُم مِّنَ الْعِلْمِ إِلَّا قَلِيلًا [١٧:٨٥]

«ከሩሕም ይጠይቁሃል፡፡ «ሩሕ ከጌታዬ ነገር ነው ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም» በላቸው፡፡»

ራጊብ አል አስፈሀኒ እንዲህ ይላሉ፡-

"ህይወት በአካል ውስጥ መኖሯ እንቅስቃሴ፣ ስሜት፣ እውቀት፣ ሀሳብ፣ መለየት እና ሰውነትን እንደፈለጉ ማድረግ ይችላል፡፡ እንዲሁም አካል ሌላ ነገር መሸከም እንዲችል እና ያማረ እንደሆን ታደርጋለች፡፡ እሷ አካል ውስጥ ባለመኖሯ ደግሞ አካል የሚሸከመው እቃ የሚፈልግ ጥንብ ይሆናል፡፡

ልክ ሰውነት አካልን ባህሪ ተለባሽ እንደሆነው ሁሉ ህይወትም የሕወት መኖርን ባህሪዎች ተላባሽ ናት፡፡"

ከዚህ ግዜ በኋላ አጥንት ይፈጠርና በመቀጠልም ስጋ ይለብሳል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

فَخَلَقْنَا الْمُضْغَةَ عِظَامًا فَكَسَوْنَا الْعِظَامَ لَحْمًا ثُمَّ أَنشَأْنَاهُ خَلْقًا آخَرَ ۚ فَتَبَارَكَ اللَّهُ أَحْسَنُ الْخَالِقِينَ [٢٣:١٤]

«ቁራጪንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፡፡ አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው፡፡ ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረትን አድርገን አስገኘነው፡፡ ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ፡፡ »

" " " " :-

وَانظُرْ إِلَى الْعِظَامِ كَيْفَ نُنشِزُهَا ثُمَّ نَكْسُوهَا لَحْمًا ۚ فَلَمَّا تَبَيَّنَ لَهُ قَالَ أَعْلَمُ أَنَّ اللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ [٢:٢٥٩]

«ወደ ዐፅሞቹም እንዴት እንደምናስነሳት ከዚያም ሥጋን እንደምናለብሳት ተመልከት» አለው፡፡ ለርሱም (በማየት) በተገለጸለት ጊዜ፡- «አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መኾኑን ዐውቃለሁ» አለ፡፡»

**አላህ (ሱ.ወ) ፈቅድ ወደዚህ ዓለም እስከሚመጣ ድረስ ሽሉ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሆኖ እድገቱን ይቀጥላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

إِلَيْهِ يُرَدُّ عِلْمُ السَّاعَةِ ۚ وَمَا تَخْرُجُ مِن ثَمَرَاتٍ مِّنْ أَكْمَامِهَا وَمَا تَحْمِلُ مِنْ أُنثَىٰ وَلَا تَضَعُ إِلَّا بِعِلْمِهِ ۚ

«ጊዜይቱን ማወቅ ወደእርሱ ይመለሳል ከፍሬዎችም ከሽፋኖቻቸው አይወጡም፡፡ ከሴትም አንዲትም አታረግዝም፣ አትወልድምም በዕውቀቱ ቢኾን እንጅ፡፡»

**ከአንድሺህ አራት መቶ ምናምን አመታት በፊት የወረደው ቁርአን እና ከስሜታቸው ተናግረው የማያውቁት የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክተኛነት በሚያረጋግጥ መልኩ አላህ (ሱ.ወ) ሰው ልጅ በማህፀን ውስጥ የሚያልፋቸውን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያሉትን የእድገት እርከኖች በአንድ አንቀፅ ውስጥ አብራርቶታል አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَلَقَدْ خَلَقْنَا الْإِنسَانَ مِن سُلَالَةٍ مِّن طِينٍ [٢٣:١٢]ثُمَّ جَعَلْنَاهُ نُطْفَةً فِي قَرَارٍ مَّكِينٍ [٢٣:١٣]ثُمَّ خَلَقْنَا النُّطْفَةَ عَلَقَةً فَخَلَقْنَا الْعَلَقَةَ مُضْغَةً فَخَلَقْنَا الْمُضْغَةَ عِظَامًا فَكَسَوْنَا الْعِظَامَ لَحْمًا ثُمَّ أَنشَأْنَاهُ خَلْقًا آخَرَ ۚ فَتَبَارَكَ اللَّهُ أَحْسَنُ الْخَالِقِينَ [٢٣:١٤]ثُمَّ إِنَّكُم بَعْدَ ذَٰلِكَ لَمَيِّتُونَ [٢٣:١٥]ثُمَّ إِنَّكُمْ يَوْمَ الْقِيَامَةِ تُبْعَثُونَ [٢٣:١٦]

«በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፡፡ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን፡፡ ቁራጯንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፡፡ አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው፡፡ ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረትን አድርገን አስገኘነው፡፡ ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ፡፡ ከዚያም እናንተ ከዚህ በኋላ በእርግጥ ሟቾች ናችሁ፡፡ከዚያም እናንተ በትንሣኤ ቀን ትቀሰቀሳላችሁ፡፡»

**በሌላም አንቀጽ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡0**

يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِن كُنتُمْ فِي رَيْبٍ مِّنَ الْبَعْثِ فَإِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ مِنْ

عَلَقَةٍ ثُمَّ مِن مُّضْغَةٍ مُّخَلَّقَةٍ وَغَيْرِ مُخَلَّقَةٍ لِّنُبَيِّنَ لَكُمْ ۚ وَنُقِرُّ فِي الْأَرْحَامِ مَا نَشَاءُ إِلَىٰ أَجَلٍ

مُّسَمًّى ثُمَّ نُخْرِجُكُمْ طِفْلًا ثُمَّ لِتَبْلُغُوا أَشُدَّكُمْ ۖ وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ وَمِنكُم مَّن يُرَدُّ إِلَىٰ أَرْذَلِ

الْعُمُرِ لِكَيْلَا يَعْلَمَ مِن بَعْدِ عِلْمٍ شَيْئًا ۚ وَتَرَى الْأَرْضَ هَامِدَةً فَإِذَا أَنزَلْنَا عَلَيْهَا الْمَاءَ

اهْتَزَّتْ وَرَبَتْ وَأَنبَتَتْ مِن كُلِّ زَوْجٍ بَهِيجٍ [٢٢:٥]ذَٰلِكَ بِأَنَّ اللَّهَ هُوَ الْحَقُّ وَأَنَّهُ يُحْيِي الْمَوْتَىٰ

وَأَنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ [٢٢:٦]وَأَنَّ السَّاعَةَ آتِيَةٌ لَّا رَيْبَ فِيهَا وَأَنَّ اللَّهَ يَبْعَثُ مَن فِي

الْقُبُورِ [٢٢:٧]

እናንተ ሰዎች ሆይ! ከመቀስቀስ በመጠራጠር ውስጥ እንደ ሆናችሁ (አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ)፡፡ እኛም ከዐፈር ፈጠርናችሁ፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ ከዚያም ከቁራጭ ሥጋ፣ ፍጥረትዋ ሙሉ ከሆነችና ሙሉ ካልሆነች (ችሎታችንን) ለናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ፡፡ የምንሻውንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በማሕፀን ውስጥ እናረጋዋለን፡፡ ከዚያም ሕፃን ሆናችሁ እናወጣችኋለን፡፡ ከዚያም ሙሉ ጥንካሬያችሁን ትደርሱ ዘንድ (እናሳድጋችኋለን)፡፡ ከእናንተም የሚሞት ሰው አልለ፡፡ ከእናንተም ከዕውቀት በኋላ ምንንም እንዳያውቅ ወደ ወራዳ ዕድሜ የሚመለስ ሰው አልለ፡፡ ምድርንም ደረቅ ሆና ታያታለህ፡፡ በእርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ ትላወሳለች፡፡ ትነፋፋለችም፡፡ ውበት ካለው ጎሳ ሁሉ ታበቅላለችም፡፡ ይህ አላህ እርሱ መኖሩ የተረጋገጠ፣ እርሱም ሙታንን ሕያው የሚያደርግ፣ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ በመሆኑ ነው፡፡ ሰዓቲቱም መጪ ፣ በእርሷ ፈጽሞ ጥርጣሬ የሌለባት በመሆኗ፣ አላህም በመቃብሮች ውስጥ ያለን ሁሉ የሚቀሰቅስ በመሆኑ ነው፡፡››

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ሲል እውነት ተናገረ፡-**

سَنُرِيهِمْ آيَاتِنَا فِي الْآفَاقِ وَفِي أَنفُسِهِمْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمْ أَنَّهُ الْحَقُّ ۗ أَوَلَمْ يَكْفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُ

عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ [٤١:٥٣]

ፕሮፌሰር ኬይዝ ሙር The developing human በሚል መጽሀፋቸው ውስጥ እንዲህ ይላሉ፡ “ቁርዓን የአላህ ንግግር ስመሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለኝም፡፡ በቁርኣን ውስጥ ያል የሽል ገለጣ በ7ኛ ክፍለ ዘመን በነበረው የእውቀት ደረጃ ላይ ተመስርቶ ሊነገር ሚችል ገለፃ አይደለም፡፡ አዕምሮ ሊቀበል የሚችለው ብቸኛ ማምለጫ መንገድ ይህ ገለፃ ከአላህ ወደ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የወረዳ መሆኑን ማመን ነው፡፡

## የዚህ ዓለም እውነተኛ ማንነት

ጌታችን አላህ (ሱ.ወ) የአለም እውነተኛ ምንነት ጊዝያዊ የማይዘወትር መታለያ መሆኑን ነግሮናል፡ ፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

اعْلَمُوا أَنَّمَا الْحَيَاةُ الدُّنْيَا لَعِبٌ وَلَهْوٌ وَزِينَةٌ وَتَفَاخُرٌ بَيْنَكُمْ وَتَكَاثُرٌ فِي الْأَمْوَالِ وَالْأَوْلَادِ ۖ كَمَثَلِ غَيْثٍ أَعْجَبَ الْكُفَّارَ نَبَاتُهُ ثُمَّ يَهِيجُ فَتَرَاهُ مُصْفَرًّا ثُمَّ يَكُونُ حُطَامًا ۖ وَفِي الْآخِرَةِ عَذَابٌ شَدِيدٌ وَمَغْفِرَةٌ مِّنَ اللَّهِ وَرِضْوَانٌ ۚ وَمَا الْحَيَاةُ الدُّنْيَا إِلَّا مَتَاعُ الْغُرُورِ [٥٧:٢٠]

« ቅርቢቱ ሕይወት ጨዋታና ዛዛታ፣ ማጌጫም፣ በመካከላችሁም መፎካከሪያ፣ በገንዘቦችና በልጆችም ብዛት መበላለጫ ብቻ መኾንዋን ዕወቁ፡፡ (እርሷ) በቃዩ ገበሬዎችን እንደሚያስደስት ዝናም፣ ከዚያም በቃዩ እንደሚደርቅና ገርጥቶ እንደምታየው፣ ከዚያም የተሰባበረ እንደሚኾን ብጤ ናት፣ በመጨረሻይቱም ዓለም ብርቱ ቅጣት ከአላህም ምሕረትና ውዴታ አልለ፡፡ የቅርቢቱም ሕይወት የመታለያ ጥቅም እንጅ ሌላ አይደለችም፡፡»

ይህ አለም የፈተና ነው፡፡ ጌጦቹም አጓጊ ሲሆኑ መተንቀቅ ተገቢ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

فَمَا أُوتِيتُم مِّن شَيْءٍ فَمَتَاعُ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا ۖ وَمَا عِندَ اللَّهِ خَيْرٌ وَأَبْقَىٰ لِلَّذِينَ آمَنُوا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ [٤٢:٣٦]

**ይህ አለም ለዘውተሪው መጪው ዓለም መዳረሻ መሆን አለበት፡፡ ዱንያ ለአኼራ መዝሪያ ቦታ ነው፡፡ የዘራኸውን ነው የምታጭደው፡፡ የሰራኸውን ታገኛለህ፡፡ ጥሩ ከሰራህ ጥሩ መጥፎ ከሰራህ መጥፎ ምንዳ ታገኛለህ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَاضْرِبْ لَهُم مَّثَلَ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا كَمَاءٍ أَنزَلْنَاهُ مِنَ السَّمَاءِ فَاخْتَلَطَ بِهِ نَبَاتُ الْأَرْضِ فَأَصْبَحَ هَشِيمًا تَذْرُوهُ الرِّيَاحُ ۗ وَكَانَ اللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ مُّقْتَدِرًا [١٨:٤٥]

«ለእነሱም የቅርቢቱን ሕይወት ምሳሌ አውሳላቸው፡፡ (እርሷ) ከሰማይ እንዳወረድነው ውሃ በእርሱም የምድር በቃይ እንደ ተቀላቀለበት (ከተዋበ በኋላ ደርቆ) ነፋሶችም የሚያበኑት ደቃቅ እንደ ኾነ ብጤ ናት፡፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡»

الْمَالُ وَالْبَنُونَ زِينَةُ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا ۖ وَالْبَاقِيَاتُ الصَّالِحَاتُ خَيْرٌ عِندَ رَبِّكَ ثَوَابًا وَخَيْرٌ أَمَلًا

[١٨:٤٦]

«ገንዘብና ወንዶች ልጆች የቅርቢቱ ሕይወት ጌጦች ናቸው፡፡ መልካሞቹም ቀሪዎች (ሥራዎች) እጌታህ ዘንድ በምንዳ በላጭ ናቸው፡፡ በተስፋም በላጭ ናቸው፡፤»

**ይህች ዱንያ የተዋረደች እና ዋጋ የሌላት አገር በመሆኗ አላህ (ሱ.ወ) ከሀዲ አማኝ-------- ለሁሉም ይሰጣል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَإِذْ قَالَ إِبْرَاهِيمُ رَبِّ اجْعَلْ هَٰذَا بَلَدًا آمِنًا وَارْزُقْ أَهْلَهُ مِنَ الثَّمَرَاتِ مَنْ آمَنَ مِنْهُم بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ ۖ قَالَ وَمَن كَفَرَ فَأُمَتِّعُهُ قَلِيلًا ثُمَّ أَضْطَرُّهُ إِلَىٰ عَذَابِ النَّارِ ۖ وَبِئْسَ الْمَصِيرُ

[٢:١٢٦]

«ኢብራሂም ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ጌታዬ ሆይ! ይህንን ጸጥተኛ አገር አድርግ፡፡ ቤተሰቦቹንም ከነሱ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነውን ሰው ከፍሬዎች ስጠው፡፡ (አላህም) የካደውንም ሰው፤ (እሰጠዋለሁ)፡፡ ጥቂትም እጠቅመዋለሁ፤ ከዚያም ወደ እሳት ቅጣት አስጠጋዋለሁ፤ ምን ትከፋም መመለሻ! (አለ)፡፡»

**“ “ “ “ :-**

كُلًّا نُّمِدُّ هَٰؤُلَاءِ وَهَٰؤُلَاءِ مِنْ عَطَاءِ رَبِّكَ ۚ وَمَا كَانَ عَطَاءُ رَبِّكَ مَحْظُورًا [١٧:٢٠]

«ሁሉንም እነዚህንና እነዚያን ከጌታህ ስጦታ (በዚህ ዓለም) እንጨምርላቸዋለን፡፡ የጌታህም ስጦታ (በዚች ዓለም) ክልክል አይደለም፡፡»

انظُرْ كَيْفَ فَضَّلْنَا بَعْضَهُمْ عَلَىٰ بَعْضٍ ۚ وَلَلْآخِرَةُ أَكْبَرُ دَرَجَاتٍ وَأَكْبَرُ تَفْضِيلًا [١٧:٢١]

«ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ እንዴት እንዳበለጥን ተመልከት፡፡ የመጨረሻይቱም አገር በማዕረጎች በጣም የከበረችና በመብለጥም የተለቀች ናት፡፡ »

**ሰህል ኢብኑ ሰዕድ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ከእለታት በአንድ ቀን ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ዘልሁልይፍ በሚባል ቦታ አለፍ እና አንድ እረኛ ከሲታ (ጋቷ የደረቀ) በግ ይዞ ተመለከቱት እና "ይህን በግ በባለቤቱ ዘንድ ለውን የወረደ ቦታ ትመለከታላችሁን፡፡" አሉ፡፡ ባልደረቦቻቸውም "አዎን" አሉ፡፡ ነፍሱ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ ዱንያ አላህ ዘንድ የትንኝ ክንፍ ያህል እንኳ ቦታ ቢኖራት ከሀዲ ሰው የሚጠጣው አንድ ኩባያ ውሃ እነኳን አያገንም ነበር፡፡" ቡኽሪና ሙስሊም**

**ጌታችን አላህ (ሱ.ወ) ወደ መጪው ዓለም እና ፀጋዎቿ እንድናተኩር ያነሳሳናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

بَلْ تُؤْثِرُونَ الْحَيَاةَ الدُّنْيَا [٨٧:١٦]

ይልቁንም ቅርቢቱን ሕይወት ትመርጣላችሁ፡፡

وَالْآخِرَةُ خَيْرٌ وَأَبْقَىٰ [٨٧:١٧]

መጨረሻይቱ (ሕይወት) በላጭ ሁል ጊዜ ዘውታሪም ስትኾን፡፡

**ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "ወላሂ ዱንያ ከአኼራ አንፃር ሲወዳደር አንድ ሰው ይህን ጣቱን (አውራጣታቸውን እያሳዩ) ባህር ውስጥ ከቶ ሲያወጣ ይዞ የሚያወጣውን ይመልከት፡፡" (ሶሂህ ሙስሊም)**

**አላህ (ሱ.ወ) የመጪው ዓለም ፀጋ ለሚወዳቸው ምርጥ ባሪያዎቹ እንጂ ለሌላ ሰው የሚሰጥ አይደለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

فَأَمَّا مَنْ أَعْطَىٰ وَاتَّقَىٰ [٩٢:٥]

የሰጠ ሰውማ ጌታውን የፈራም፡፡

وَصَدَّقَ بِالْحُسْنَىٰ [٩٢:٦]

በመልካሚቱም (እምነት) ያረጋገጠ፤

فَسَنُيَسِّرُهُ لِلْيُسْرَىٰ [٩٢:٧] ለገሪቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን፡፡

وَأَمَّا مَن بَخِلَ وَاسْتَغْنَىٰ [٩٢:٨] የሰሰተ ሰውማ የተብቃቃም፤ (በራሱ የተመካ)፤

فَسَنُيَسِّرُهُ لِلْعُسْرَىٰ [٩٢:١٠] ለከፉይቱ ሥራ እናዘጋጀዋለን፡፡

ይህ ማለት ግን አላህ (ሱ.ወ) የፈቀዳቸውን እንደ ምግብ፣ መጠጥ፣ ልብስ እና ሚስት ያሉ የዱንየ መነጠቀሚያዎች ትቶ ገዳም ይግባ ማለት አይደለም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

قُلْ مَنْ حَرَّمَ زِينَةَ اللَّهِ الَّتِي أَخْرَجَ لِعِبَادِهِ وَالطَّيِّبَاتِ مِنَ الرِّزْقِ ۚ

«የአላህን ጌጥ ያችን ለባሮቹ የፈጠራትን ከሲሳይም ጥሩዎቹን እርም ያደረገ ማን ነው⇒» በላቸው፡፡»

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- አላህ ዘንድ ጠንካራ አማኝ ከደካማ አማኝ የበለጠ እና የተወደደ ነው፡፡ ምንም እንኳ ሁለቱም ውስጥ ጥሩ ጎን ቢኖርም፡፡ በሚጠቅምህ ነገር ላይ ጓጓ፡፡ በአላህ ታገዝ፡፡ አትስነፍ፡፡ የሆነ ነገር ሲያጋጥምህ “እንዲህ እንዲህ አድርጌ በነበረ እኮ” አትበል፡፡ ነገርግን የአላህ ውሳኔ ነው፡፡ “እሱ የፈለገውን ሰርቷል” ብለህ በል፡፡ በእርግጥም በነበር የምትለው ቃል የሸይጣን በር ትከፍታለች፡፡ (ሰኒህ ሙስሊም)

- ሸሪዓው ከኛ የሚፈልገው ነገረ ቢኖር የአኗኗር ዘያችንን መካከለና እንድናደርገው ነው፡፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَلَا تَجْعَلْ يَدَكَ مَغْلُولَةً إِلَىٰ عُنُقِكَ وَلَا تَبْسُطْهَا كُلَّ الْبَسْطِ فَتَقْعُدَ مَلُومًا مَّحْسُورًا

[١٧:٢٩]

«እጅህንም ወደ አንገትህ የታሰረች አታድርግ፡፡ መዘርጋትንም ሁሉ አትዘርጋት፤ የተወቀስክ የተቆጨኽ ትኾናለህና፡፡»

إِنَّ رَبَّكَ يَبْسُطُ الرِّزْقَ لِمَن يَشَاءُ وَيَقْدِرُ ۚ إِنَّهُ كَانَ بِعِبَادِهِ خَبِيرًا بَصِيرًا [١٧:٣٠]

«ጌታህ ሲሳይን ለሚሻው ሰው ያሰፋል፤ ያጠባልም፡፡ እርሱ በባሮቹ ኹኔታ ውስጠ ዐዋቂ ተመልካች ነውና፡፡»

## ሰዎችን እና አጋንንቶችን የመፍጠር አላመው ምን ይሆን?

**ሁለቱ ፍጡሮች እዚህ መድደር ላይ የተረገናኙበት ዋነናው አላማ አላህን (ሱ.ወ) በብቸኝነት መገዛት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡ وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ

[٥١:٥٦]

ከነርሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም፡፡ ሊመግቡኝም አልሻም፡፡ مَا أُرِيدُ مِنْهُم مِّن رِّزْقٍ وَمَا أُرِيدُ

أَن يُطْعِمُونِ [٥١:٥٧]

አላህ እርሱ ሲሳይን ሰጪ የብርቱ ኀይል ባለቤት ነው፡፡ إِنَّ اللَّهَ هُوَ الرَّزَّاقُ ذُو الْقُوَّةِ الْمَتِينُ [٥١:٥٨]

## የሰው ልጅ ለዘዛታ እና ለቀልድ አልተፈጠረም

**አላህ (ሱ.ወ) ለሰዎች በየጊዜው ወደጌታ ውዴት የሚያደርሰውን ትክክለኛውን መንገድ የሚመራቸው እና የሚያብራራላቸው መልዕክተኖች ይልካል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

أَفَحَسِبْتُمْ أَنَّمَا خَلَقْنَاكُمْ عَبَثًا وَأَنَّكُمْ إِلَيْنَا لَا تُرْجَعُونَ [٢٣:١١٥]

**«የፈጠርናችሁ ለከንቱ መኾኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁን=» (ለከንቱ የፈጠርናችሁ መሰላችሁን=)»**

فَتَعَالَى اللَّهُ الْمَلِكُ الْحَقُّ ۖ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ رَبُّ الْعَرْشِ الْكَرِيمِ [٢٣:١١٦]

«የእውነቱም ንጉስ አላህ ከፍተኛነት ተገባው፡፡ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ የሚያምረው ዐርሽ ጌታ ነው፡፡ »

⇒ **መልዕክተኛ መላክ ለአለም በሙሉ በተላኩት በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መደምደሚያውን አግኝቷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

كَانَ النَّاسُ أُمَّةً وَاحِدَةً فَبَعَثَ اللَّهُ النَّبِيِّينَ مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ وَأَنزَلَ مَعَهُمُ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ

لِيَحْكُمَ بَيْنَ النَّاسِ فِيمَا اخْتَلَفُوا فِيهِ ۚ وَمَا اخْتَلَفَ فِيهِ إِلَّا الَّذِينَ أُوتُوهُ مِن بَعْدِ مَا

جَاءَتْهُمُ الْبَيِّنَاتُ بَغْيًا بَيْنَهُمْ ۖ فَهَدَى اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا لِمَا اخْتَلَفُوا فِيهِ مِنَ الْحَقِّ

بِإِذْنِهِ ۗ وَاللَّهُ يَهْدِي مَن يَشَاءُ إِلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ [٢:٢١٣]

«ሰዎቹ ሁሉ አንድ ሕዝብ ነበሩ፤ (ተለያዩ)፡፡ አላህም ነቢያትን አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች አድርጎ ላከ፡፡ ከእነርሱም ጋር መጻሕፍትን በሰዎቹ መካከል በዚያ በርሱ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ በእውነት አወረደ፡፡ በእርሱም (በሃይማኖት) ግልጽ አስረጂዎች ከመጡላቸው በኋላ በመካከላቸው ለኾነው ምቀኝነት እነዚያው የተሰጡት እንጂ አልተለያዩበትም፡፡ አላህም እነዚያን ያመኑትን ሰዎች ለእዚያ ከእውነት በርሱ ለተለያዩበት በፍቃዱ መራቸው፡፡ አላህም የሚሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል፡፡»

**የሰው ልጅ የተፈጠረበት ግብ ግልጽ እና የተወሰነ ነው፡፡ እሱም የፈጠረውን አላህ (ሱ.ወ) መገዛት ነው፡፡ ህይወቱን ለተፈጠረበት አላማ ያዋለ ሰው ምንም እንኳን እጁ ላይ የዱንያ ብልጭልጭ እና መጠቃቀሚያ ባይኖረውም ትክክለኛ ደስተኛ የሚባለው እርሱ ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ህይወቱን ከተፈጠረበት ዓላማውጪ ያዋለ ሰው ምንም እንኳ በእጁላይ የዱንያ ብልጭልጭ እና መጠቃቀሚያ ቢሞላም ጥፋትት የነፍስ በሽታ፣ ጥበት፣ የተሞላበት እና ደስታ የሌለውን ኑሮ ይኖራል፡፡**

**አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَمَا خَلَقْنَا السَّمَاءَ وَالْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا بَاطِلًا ۚ ذَٰلِكَ ظَنُّ الَّذِينَ كَفَرُوا ۚ فَوَيْلٌ لِّلَّذِينَ

كَفَرُوا مِنَ النَّارِ [٣٨:٢٧]

## መጨረሻ

- በዚህ አለም ላይ ያለ ማንኛውም ህይወት ያለው ነገር ሁሉ መጨረሻው መሸሻ የማይቻለው ሞት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

كُلُّ مَنْ عَلَيْهَا فَانٍ [٥٥:٢٦] በእርሷ (በምድር) ላይ ያለው ሁሉ ጠፊ ነው፡፡

وَيَبْقَىٰ وَجْهُ رَبِّكَ ذُو الْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ [٥٥:٢٧] የልቅናና የልግሥና ባለቤት የኾነው የጌታህ ፊትም ይቀራል፡፡ (አይጠፋም)፡፡

- የሰው ልጅ ከዚህ እውነታ ለመሸሽ የፈለገውን ያህለ ጥረት ቢያደርግ መሸሽ የሚቻል ነገር አይደለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

فَإِذَا جَاءَ أَجَلُهُمْ لَا يَسْتَأْخِرُونَ سَاعَةً ۖ وَلَا يَسْتَقْدِمُونَ [٧:٣٤]

«ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት አንዲትን ሰዓት አይቆዩም፡፡ (ከጊዜያቱ) አይቀደሙምም፡፡»

- አላህ (ሱ.ወ) በሚከተለው አንቀፅ ሰዎችን እና አጋንንቶች ያስገኛቸው ፈጣሪ ስለመኖሩ የሚጠራጠሩ ከሆነ ፈተና አቅርቦላቸዋል፡፡

فَلَوْلَا إِذَا بَلَغَتِ الْحُلْقُومَ [٥٦:٨٣] (ነፍስ) ጉረሮንም በደረሰች ጊዜ፡፡

وَأَنتُمْ حِينَئِذٍ تَنظُرُونَ [٥٦:٨٤] እናንተ ያን ጊዜ የምታዩ ስትኾኑ፡፡

وَنَحْنُ أَقْرَبُ إِلَيْهِ مِنكُمْ وَلَٰكِن لَّا تُبْصِرُونَ [٥٦:٨٥] እኛም ግን አታዩም እንጅ ከእናንተ ይልቅ ወደእርሱ የቀረብን ስንኾን፡፡

فَلَوْلَا إِن كُنتُمْ غَيْرَ مَدِينِينَ [٥٦:٨٦] የማትዳኙም ከኾናችሁ፡፡

እውነተኞች እንደ ኾናችሁ (ነፍሲቱን ወደ አካሉ) ለምን አትመልሷት تَرْجِعُونَهَا إِن كُنتُمْ

صَادِقِينَ[٥٦:٨٧]

**ትክክለኛው የሞት ግዜ በመጣ ወቅትም ሁሉም ያምናል ይመሰክራልም፡፡ ነገር ግን ተመልሶ ወደዚህ አለም ለመመለስ እና ጥሩ ስራ ለመስራት እድል የለም፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

حَتَّىٰ إِذَا جَاءَ أَحَدَهُمُ الْمَوْتُ قَالَ رَبِّ ارْجِعُونِ [٢٣:٩٩]

*«አንዳቸውንም ሞት በመጣበት ጊዜ እንዲህ ይላል «ጌታዬ ሆይ! (ወደ ምድረ ዓለም) መልሱኝ፡፡»*

لَعَلِّي أَعْمَلُ صَالِحًا فِيمَا تَرَكْتُ ۚ كَلَّا ۚ إِنَّهَا كَلِمَةٌ هُوَ قَائِلُهَا ۖ وَمِن وَرَائِهِم بَرْزَخٌ إِلَىٰ

يَوْمِ يُبْعَثُونَ [٢٣:١٠٠]

*«በተውኩት ነገር በጎን ሥራ ልሠራ እከጅላለሁና፡፡» (ይህን ከማለት) ይከልከል፡፡ እርስዋ እርሱ ተናጋሪዋ የኾነች ከንቱ ቃል ናት፡፡ ከስተፊታቸውም እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ ግርዶ አልለ፡፡»*

**የሰው ልጅ የሚሞትበት ግዜ እና ቦታ አላህ (ሱ.ወ) ሚስጥር አድርጎ ከያዛቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

إِنَّ اللَّهَ عِندَهُ عِلْمُ السَّاعَةِ وَيُنَزِّلُ الْغَيْثَ وَيَعْلَمُ مَا فِي الْأَرْحَامِ ۖ وَمَا تَدْرِي نَفْسٌ مَّاذَا

تَكْسِبُ غَدًا ۖ وَمَا تَدْرِي نَفْسٌ بِأَيِّ أَرْضٍ تَمُوتُ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ [٣١:٣٤]

*«አላህ የሰዓቲቱ ዕውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው፡፡ ዝናብንም ያወርዳል፡፡ በማሕፀኖችም ውስጥ ያለን ሁሉ ያውቃል፡፡ ማንኛይቱ ነፍስም ነገ የምትሠራውን አታውቅም፡፡ ማንኛይቱ ነፍስም በየትኛው ምድር እንደምትሞት አታውቅም፡፡ አላህ ዐዋቂ ውስጠ ዐዋቂ ነው፡፡»*

- ሞት ሲባል ሁለት አይነት ሞት አለ፡፡ ትንሹ እና ትልቁ በትልቁ ሞት የሚባለው ህይወት እና ስጋ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ግዜ ላለመገናኘት ሲለያዩ ነው፡፡ ትንሹ ሞት የሚባለው ደግሞ እንቅልፍ ሲሆን ሰው በሚተኛበት ግዜ ህይወቱ ከሰውነቱ ጋር ይለያይና በአላህ ፍቃድ ደግሞ ተመልሰው ይገናኛሉ፡-

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

اللَّهُ يَتَوَفَّى الْأَنفُسَ حِينَ مَوْتِهَا وَالَّتِي لَمْ تَمُتْ فِي مَنَامِهَا ۖ فَيُمْسِكُ الَّتِي قَضَىٰ عَلَيْهَا

الْمَوْتَ وَيُرْسِلُ الْأُخْرَىٰ إِلَىٰ أَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ [٣٩:٤٢]

«አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል፡፡ ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ (ይወስዳታል)፡፡ ታዲያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል፡፡ ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቅቃታል፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አልሉበት፡፡»

## <u>ከሞት በኋላ መሄጂያችን የት ነው?</u>

ከሞት በኋላ የሚጠብቀን ነገር እንደገና መቀስቀስ እና ወደፍርድ መነሳት ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

ذَٰلِكَ بِأَنَّ اللَّهَ هُوَ الْحَقُّ وَأَنَّهُ يُحْيِي الْمَوْتَىٰ وَأَنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ [٢٢:٦]

« ይህ አላህ እርሱ መኖሩ የተረጋገጠ፣ እርሱም ሙታንን ሕያው የሚያደርግ፣ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ በመሆኑ ነው፡፡»

وَأَنَّ السَّاعَةَ آتِيَةٌ لَّا رَيْبَ فِيهَا وَأَنَّ اللَّهَ يَبْعَثُ مَن فِي الْقُبُورِ [٢٢:٧]

«ሰዓቲቱም መጪ ፣ በእርሷ ፈጽሞ ጥርጣሬ የሌለባት በመሆኗ፣ አላህም በመቃብሮች ውስጥ ያለን ሁሉ የሚቀሰቅስ በመሆኑ ነው፡፡»

ከድሮ ጀምሮ ቤዘመናቱ የነበሩ ከሀዲዎች እንደገና በመቀስቀስ ያስዋሹ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ አሁን እንደ አዲስ የመጣ ነገር አይደለም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

زَعَمَ الَّذِينَ كَفَرُوا أَن لَّن يُبْعَثُوا ۚ قُلْ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتُبْعَثُنَّ ثُمَّ لَتُنَبَّؤُنَّ بِمَا عَمِلْتُمْ ۚ

وَذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ [٦٤:٧]

«እነዚያ የካዱትን በፍጹም የማይቀሰሱ መኾናቸውን አሰቡ፡፡ «አይደለም በጌታዬ እምላለሁ፡፡ በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ፡፡ ከዚያም በሠራችሁት ሁሉ ትነገራላችሁ፡፡ ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው፡፡» በላቸው፡፡»
***ሰዎችን ለማጥመም እና ከሞት በኋላ የመቀስቀስን እውነታ እንዲክዱ የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት ያደርጋሉ፡ አላህ (ሱ.ወ) ስለእነሱ እንዲህ ይላል፡-***

أَيَعِدُكُمْ أَنَّكُمْ إِذَا مِتُّمْ وَكُنتُمْ تُرَابًا وَعِظَامًا أَنَّكُم مُّخْرَجُونَ [٢٣:٣٥]

«እናንተ በሞታችሁና ዐፈርና አጥንቶችም በኾናችሁ ጊዜ እናንተ (ከመቃብር) ትወጣላችሁ በማለት ያስፈራራችኋልን?»

هَيْهَاتَ هَيْهَاتَ لِمَا تُوعَدُونَ [٢٣:٣٦]

«ያ የምትስፈራሩበት ነገር ራቀ፤ በጣም ራቀ፡፡

إِنْ هِيَ إِلَّا حَيَاتُنَا الدُّنْيَا نَمُوتُ وَنَحْيَا وَمَا نَحْنُ بِمَبْعُوثِينَ [٢٣:٣٧]

«እርሷ (ሕይወት) ቅርቢቱ ሕይወታችን እንጂ ሌላ አይደለችም፡፡ እንሞታለን፤ (ልጆቻችን ስለሚተኩ) ሕያውም እንኾናለን፡፡ እኛም ተቀስቃሾች አይደለንም፡፡»
***መኖር እና መሞት የሚባሉትን ነገራቶች ተፈጥሮአዊ ነው ብለው ራሳቸውን ያታልላሉ፡፡ እነዚህ------- እንደራሳቸው ፍጡር መሆናቸውን አላወቁም፡፡***

***አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-***

وَقَالُوا مَا هِيَ إِلَّا حَيَاتُنَا الدُّنْيَا نَمُوتُ وَنَحْيَا وَمَا يُهْلِكُنَا إِلَّا الدَّهْرُ ۚ وَمَا لَهُم بِذَٰلِكَ مِنْ عِلْمٍ ۖ إِنْ هُمْ إِلَّا يَظُنُّونَ [٤٥:٢٤]

« እርሷም (ሕይወት) የቅርቢቱ ሕይወታችን እንጅ ሌላ አይደለችም፡፡ «እንሞታለን፤ ሕያውም እንኾናለን፡፡ ከጊዜም (ማለፍ) በስተቀር ሌላ አያጠፉንም» አሉ፡፡ ለእነርሱም በዚህ (በሚሉት) ምንም ዕውቀት የላቸውም፡፡ እነርሱ የሚጠራጠሩ እንጅ ሌላ አይደሉም፡፡»

- ኸረ እንዲያውም አንዳንዶች እነዲያምኑ አዕምሮ የማይቀበለውን አሰረጂ ይፈልጋሉ፡፡
  አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

إِنَّ هَٰؤُلَاءِ لَيَقُولُونَ [٤٤:٣٤]

«እነዚህ (የመካ ከሓዲዎች) በእርግጥ ይላሉ፡-»

إِنْ هِيَ إِلَّا مَوْتَتُنَا الْأُولَىٰ وَمَا نَحْنُ بِمُنشَرِينَ [٤٤:٣٥]

«እርሷ የፊተኛይቱ ሞታችን እንጅ አይደለችም፡፡ እኛም የምንቀሰቀስ አይደለንም፡፡»

فَأْتُوا بِآبَائِنَا إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ [٤٤:٣٦]

«እውነተኞችም እንደ ኾናችሁ አባቶቻችንን አምጡልን፡፡»

أَهُمْ خَيْرٌ أَمْ قَوْمُ تُبَّعٍ وَالَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ ۚ أَهْلَكْنَاهُمْ ۖ إِنَّهُمْ كَانُوا مُجْرِمِينَ [٤٤:٣٧]

«እነርሱ በላጮች ናቸውን ወይስ የቱብበዕ ሕዝቦችና እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩት? አጠፋናቸው፡፡ እነርሱ አመጸኞች ነበሩና፡፡»

- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ በማለት ይመልስላቸዋል፡-

وَقَالُوا أَإِذَا كُنَّا عِظَامًا وَرُفَاتًا أَإِنَّا لَمَبْعُوثُونَ خَلْقًا جَدِيدًا [١٧:٤٩]

«አሉም «እንዴት= አጥንቶችና ብስብሶች በኾን ጊዜ እኛ አዲስ ፍጥረት ኾነን በእርግጥ ተቀስቃሾች ነን=»»

قُلْ كُونُوا حِجَارَةً أَوْ حَدِيدًا [١٧:٥٠]

በላቸው «ድንጋዮችን ወይም ብረትን ሁኑ»

أَوْ خَلْقًا مِّمَّا يَكْبُرُ فِي صُدُورِكُمْ ۚ فَسَيَقُولُونَ مَن يُعِيدُنَا ۖ قُلِ الَّذِي فَطَرَكُمْ أَوَّلَ مَرَّةٍ ۚ فَسَيُنْغِضُونَ إِلَيْكَ رُءُوسَهُمْ وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هُوَ ۖ قُلْ عَسَىٰ أَن يَكُونَ قَرِيبًا

[١٧:٥١]

««ወይም በልቦቻችሁ ውስጥ የሚተልቅን ፍጥረት (ኹኑ መቀስቀሳችሁ አይቀርም)::» «የሚመልሰንም ማነው?» ይላሉ:: ያ በመጀመሪያ ጊዜ የፈጠራችሁ ነው» በላቸው:: ወደ አንተም ራሶቻቸውን ይነቀንቃሉ:: «እርሱም መቼ ነው?» ይላሉ:: «(እርሱ) ቅርብ ሊኾንን ይቻላል በላቸው::»

يَوْمَ يَدْعُوكُمْ فَتَسْتَجِيبُونَ بِحَمْدِهِ وَتَظُنُّونَ إِن لَّبِثْتُمْ إِلَّا قَلِيلًا [١٧:٥٢]

«(እርሱም) የሚጠራችሁና (አላህን) አመስጋኞቹ ኾናችሁ ጥሪውን የምትቀበሉበት ጥቂትንም (ቀኖች) እንጂ ያልቆያችሁ መኾናችሁን የምትጠራጠሩበት ቀን ነው፤ (በላቸው)::»

- በመጨረሻው ቀን እና በመከሰቱ ያስዋሻሉ:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَقَالَ الَّذِينَ كَفَرُوا لَا تَأْتِينَا السَّاعَةُ ۖ قُلْ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتَأْتِيَنَّكُمْ عَالِمِ الْغَيْبِ ۖ لَا يَعْزُبُ عَنْهُ مِثْقَالُ ذَرَّةٍ فِي السَّمَاوَاتِ وَلَا فِي الْأَرْضِ وَلَا أَصْغَرُ مِن ذَٰلِكَ وَلَا أَكْبَرُ إِلَّا فِي كِتَابٍ مُّبِينٍ [٣٤:٣]

«እነዚያ የካዱትም «ሰዓቲቱ አትመጣብንም» አሉ:: በላቸው «አይደለም፤ ሩቁን ሁሉ ዐዋቂ በኾነው ጌታዬ እምላለሁ:: በእርግጥ ትመጣባችኋለች:: የብናኝ ክብደት ያክል እንኳ በሰማያትና በምድር ውስጥ ከእርሱ አይርቅም:: ከዚህ ያነሰም ኾነ የበለጠ የለም በግልጹ መጽሐፍ ውስጥ የተመዘገበ ቢኾን እንጅ::»

لِّيَجْزِيَ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ ۚ أُولَٰئِكَ لَهُم مَّغْفِرَةٌ وَرِزْقٌ كَرِيمٌ [٣٤:٤]

«እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችን የሠሩትን ሊመነዳ (ሰዓቲቱ ትመጣባችኋለች)፤ እነዚያ ለእነርሱ ምህረትና የከበረ ሲሳይ አላቸው:: »

وَالَّذِينَ سَعَوْا فِي آيَاتِنَا مُعَاجِزِينَ أُولَٰئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ مِّن رِّجْزٍ أَلِيمٌ [٣٤:٥]

« እነዚያም የሚያመልጡ መስሏቸው አንቀጾቻችንን ለማፍረስ የጣሩ እነዚያ ለእነርሱ ከመጥፎ ቅጣት የኾነ አሳማሚ ስቃይ አላቸው:: »

- **በዚያን ቀን አላህ (ሱ.ወ) ፍጥረታትን በመሉ ይቀሰቅሳል፡፡**

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

مَّا خَلْقُكُمْ وَلَا بَعْثُكُمْ إِلَّا كَنَفْسٍ وَاحِدَةٍ ۗ إِنَّ اللَّهَ سَمِيعٌ بَصِيرٌ [٣١:٢٨]

«እናንተን መፍጠርና እናንተን መቀስቀስ እንደ አንዲት ነፍስ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ አላህ ሰሚ ተመልካች ነውና፡፡»

- **አላህ (ሱ.ወ) ሰዎችን ለሂሳብ እና ለፍርድ ቀን ይሰበስባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

وَلَقَدْ عَلِمْنَا الْمُسْتَقْدِمِينَ مِنكُمْ وَلَقَدْ عَلِمْنَا الْمُسْتَأْخِرِينَ [١٥:٢٤]

«ከእናንተም ተቀዳሚዎቹን በእርግጥ ዐውቀናል፡፡ ወደ ኋላም ቀሪዎቹን በእርግጥ ዐውቀናል፡፡»

- **ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያለ ሰው ሁሉ ይመጣል፡፡ አንድ ወደኋላ የሚቀር የለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

قُلْ إِنَّ الْأَوَّلِينَ وَالْآخِرِينَ [٥٦:٤٩]

«በላቸው፡- «ፊተኞቹም ኋለኞቹም፡፡»

لَمَجْمُوعُونَ إِلَىٰ مِيقَاتِ يَوْمٍ مَّعْلُومٍ [٥٦:٥٠]

«በተወሰነ ቀን ቀጠሮ በእርግጥ ተሰብሳቢዎች ናቸው፡፡»

- **አላህ (ሱ.ወ) ሁሉንም ሰውም ይሁን አጋንንት እንደየስራቸው ይተሳሰባቸዋል፡፡**

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

يَوْمَ تَجِدُ كُلُّ نَفْسٍ مَّا عَمِلَتْ مِنْ خَيْرٍ مُّحْضَرًا وَمَا عَمِلَتْ مِن سُوءٍ تَوَدُّ لَوْ أَنَّ بَيْنَهَا وَبَيْنَهُ

أَمَدًا بَعِيدًا ۗ وَيُحَذِّرُكُمُ اللَّهُ نَفْسَهُ ۗ وَاللَّهُ رَءُوفٌ بِالْعِبَادِ [٣:٣٠]

«ነፍስ ሁሉ ከመልካም ነገር የሠራችውን የቀረበ ኾኖ የምታገኘበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ከመጥፎም የሠራችው በርሷና በርሱ (በኀጢአትዋ) መካከል በጣም የሰፋ ርቀት ቢኖር ትመኛለች፡፡ አላህ ነፍሱን ያስጠነቅቃችኋል፡፡ አላህም ለባሮቹ ሩኅሩኅ ነው፡፡»

- **የሰው ልጅ የሚሰራቸው ስራዎች ሁሉ ተቆጥረው ይመዘገባሉ።**

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡**

يَوْمَ يَبْعَثُهُمُ اللَّهُ جَمِيعًا فَيُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُوا ۚ أَحْصَاهُ اللَّهُ وَنَسُوهُ ۚ وَاللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ [٥٨:٦]

« አላህ ሁላቸውንም በሚቀሰቅሳቸው ቀን (ይቀጣቸዋል)፡፡ የሠሩትንም ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ የረሱት ሲኾኑ አላህ ዐውቆታል፡፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነው፡፡»

- **በዚህ ትልቅ ቀን ሰዎች ከሚወዱት እና ከቅርብ ዘመዶቻቸው ሁሉ ይሸሻሉ፡፡፡**

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

فَإِذَا جَاءَتِ الصَّاخَّةُ [٨٠:٣٣] አደንቋሪይቱም (መከራ) በመጣች ጊዜ፤

يَوْمَ يَفِرُّ الْمَرْءُ مِنْ أَخِيهِ [٨٠:٣٤] ሰው ከወንድሙ በሚሸሽበት ቀን፤

وَأُمِّهِ وَأَبِيهِ [٨٠:٣٥] ከናቱም ካባቱም፤

وَصَاحِبَتِهِ وَبَنِيهِ [٨٠:٣٦] ከሚስቱም ከልጆችም፤

لِكُلِّ امْرِئٍ مِّنْهُمْ يَوْمَئِذٍ شَأْنٌ يُغْنِيهِ [٨٠:٣٧]

«ከእነርሱ ለየሰው ሁሉ በዚያ ቀን (ከሌላው) የሚያብቃቃው ኹነታ አልለው፡፡»

- **ኸረ እንደውም ወንጀለኞች ቅጣቶቻቸውን ባዩ ግዜ በጣም የሚወዳቸው እና ለነሱ ቅርብ የሆኑ ሰዎች በነሱ ፋንታ እንዲቀጡላቸው ይመኛሉ፡፡**

  **አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

يَوَدُّ الْمُجْرِمُ لَوْ يَفْتَدِي مِنْ عَذَابِ يَوْمِئِذٍ بِبَنِيهِ [٧٠:١١]

«(ዘመዶቻቸውን) ያዩዋቸዋል፡፡ አመጸኛው ከዚያ ቀን ስቃይ (ነፍሱን) በልጆቹ ሊበዥ ይመኛል፡፡»

በሚስቱም በወንድሙም፡፡ وَصَاحِبَتِهِ وَأَخِيهِ [٧٠:١٢]

በዚያችም በምታስጠጋው ጎሳው፡፡ وَفَصِيلَتِهِ الَّتِي تُؤْوِيهِ [٧٠:١٣]

وَمَن فِي الْأَرْضِ جَمِيعًا ثُمَّ يُنجِيهِ [٧٠:١٤]

«በምድርም ላይ ባለው ሁሉ (ሊበዥ) ከዚያም ሊያድነው (ይመኛል)፡፡»

- **የዛን ቀን ፍርድ ቁርጥ ያለ ነው፡፡ ለይግባይ ለጉቦ እና ለማታለል ፈፅሞ ቦታ የለም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

إِنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا لَوْ أَنَّ لَهُم مَّا فِي الْأَرْضِ جَمِيعًا وَمِثْلَهُ مَعَهُ لِيَفْتَدُوا بِهِ مِنْ عَذَابِ يَوْمِ

الْقِيَامَةِ مَا تُقُبِّلَ مِنْهُمْ ۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ [٥:٣٦]

«እነዚያ የካዱት ሰዎች በምድር ላይ ያለው ሁሉ ከእርሱም ጋር ብጤው ከትንሣኤ ቀን ቅጣት በእርሱ ሊበዥበት ለእነርሱ በኖራቸው ኖሮ ከእነሱ ተቀባይን ባላገኙ ነበር፡፡ ለእነሱም አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡»

- **በዛን ቀን ተቀባይነት ያለው ነገር ቢኖር በጎ ስራ ነው፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَمَا أَمْوَالُكُمْ وَلَا أَوْلَادُكُم بِالَّتِي تُقَرِّبُكُمْ عِندَنَا زُلْفَىٰ إِلَّا مَنْ آمَنَ وَعَمِلَ صَالِحًا فَأُولَٰئِكَ لَهُمْ

جَزَاءُ الضِّعْفِ بِمَا عَمِلُوا وَهُمْ فِي الْغُرُفَاتِ آمِنُونَ [٣٤:٣٧]

«ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁም ያች እኛ ዘንድ መቅረብን የምታቀርባችሁ አይደለችም፡፡ ያመነና መልካምን የሠራ ብቻ ሲቀር፡፡ እነዚያ ለእነርሱ በሠሩት መልካም ሥራ እጥፍ ምንዳ አልላቸው፡፡ እነርሱም በገነት ሰገነቶች ውስጥ ጸጥተኞች ናቸው፡፡»

**በዛን አስፈሪ ቀን**

لَا يَنفَعُ نَفْسًا إِيمَانُهَا لَمْ تَكُنْ آمَنَتْ مِن قَبْلُ أَوْ كَسَبَتْ فِي إِيمَانِهَا خَيْرًا

«ከጌታህ ምልክቶች ከፊሉ በሚመጣ ቀን ከዚህ በፊት አማኝ ያልኾነችን ነፍስ እምነትዋ ወይም በእምነትዋ (ጊዜ) በጎ ያልሠራችን (ነፍስ ጸጸትዋ) አይጠቅማትም፡፡»

የዛን ቀን የሰው ልጅ በህይወቱ ላይ ሲታገዝባቸው የነበሩ ቁሳዊ ሀብቶች በሙሉ አይኖሩም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَلَقَدْ جِئْتُمُونَا فُرَادَىٰ كَمَا خَلَقْنَاكُمْ أَوَّلَ مَرَّةٍ وَتَرَكْتُم مَّا خَوَّلْنَاكُمْ وَرَاءَ ظُهُورِكُمْ ۖ

«መጀመሪያም ጊዜ እንደ ፈጠርናችሁ ኾናችሁ የሰጠናችሁን ሁሉ በጀርባዎቻችሁ ኋላ የተዋችሁ ስትኾኑ የሰጠናችሁን ሁሉ በጀርባዎቻችሁ ኋላ የተዋችሁ ስትኾኑ ለየብቻችሁ ኾናችሁ በእርግጥ መጣችሁን=»

ወደዛ ቦታ ይዞ ሲሄድ የሚችለው ብቸና ሀብቱ በዚህ አለም ጥሩም ይሁን መጥፎ የሰራው ስራው ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

فَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ خَيْرًا يَرَهُ [٩٩:٧] የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል፡፡

وَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ شَرًّا يَرَهُ [٩٩:٨] የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል፡፡

## <u>ከመቀስቀስ በኋላ ምንድን ን የሚከሰተው</u>

ከመቀስቀስ በኋላ ሰዎች በደል በማውቀው ፍትሀዊ አምላክ ፊት ለፍርድ ይቆማሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ)እንዲህ ይላል፡-

وَنَضَعُ الْمَوَازِينَ الْقِسْطَ لِيَوْمِ الْقِيَامَةِ فَلَا تُظْلَمُ نَفْسٌ شَيْئًا ۖ وَإِن كَانَ مِثْقَالَ حَبَّةٍ مِّنْ خَرْدَلٍ أَتَيْنَا بِهَا ۗ وَكَفَىٰ بِنَا حَاسِبِينَ [٢١:٤٧]

«በትንሣኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን፡፡ ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም፡፡ (ሥራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርሷን እናመጣታለን፡፡ ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ፡፡»

ሁሉም ህዝብ አላህ በመልዕክተኞቹ አማካኝነት በነገራቸው ህግ መሰረት ይዳኛሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

يَوْمَ نَدْعُو كُلَّ أُنَاسٍ بِإِمَامِهِمْ ۖ فَمَنْ أُوتِيَ كِتَابَهُ بِيَمِينِهِ فَأُولَٰئِكَ يَقْرَءُونَ كِتَابَهُمْ وَلَا

يُظْلَمُونَ فَتِيلًا [١٧:٧١]

«ሰዎችን ሁሉ በመሪያቸው የምንጠራበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ መጽሐፉንም በቀኙ የተሰጠ ሰው እነዚያ መጽሐፋቸውን ያነባሉ፡፡ በተምር ፍሬ ስንጥቅ ላይ ያለውን ክር ያክል እንኳ አይበደሉም፡፡»

وَمَن كَانَ فِي هَٰذِهِ أَعْمَىٰ فَهُوَ فِي الْآخِرَةِ أَعْمَىٰ وَأَضَلُّ سَبِيلًا [١٧:٧٢]

« በዚህችም ዓለም (ልበ) ዕውር የኾነ ሰው እርሱ በመጨረሻይቱም (ዓለም) ይበልጥ ዕውር ነው፡፡ መንገድንም በጣም የተሳሳተ ነው፡፤»

**አማኞች እና ሙስሊሞች እነዚያ መልዕክተኞቻቸውን እውነት ብለው የተቀበሉ፣ እድሜያቸውን የአላህን ትዕዛዝ በመተግባር እና ክልከላውን በመቆጠብ ያሳለፉ ሰዎች ዘውታሪ ደስታ፣ ቋሚ ፀጋ እና ዘውታሪ ህይወት ያለበት ጀነት ምንዳቸ ይሆናል፡፡**

**አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-**

إِنَّ الْمُتَّقِينَ فِي مَقَامٍ أَمِينٍ [٤٤:٥١] ጥንቁቆቹ በእርግጥ በጸጥተኛ መኖሪያ ውስጥ ናቸው፡፡

فِي جَنَّاتٍ وَعُيُونٍ [٤٤:٥٢] በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ናቸው፡፡

يَلْبَسُونَ مِن سُندُسٍ وَإِسْتَبْرَقٍ مُّتَقَابِلِينَ [٤٤:٥٣] ፊት ለፊት የተቅጣጩ ኾነው ከስስ ሐርና ከወፍራም ሐር ይለብሳሉ፡፡

كَذَٰلِكَ وَزَوَّجْنَاهُم بِحُورٍ عِينٍ [٤٤:٥٤] (ነገሩ) እንደዚሁ ነው፤ ዓይናማዎች የኾኑን ነጫጭ ሴቶችም እናጠናዳቸዋለን፡፡

يَدْعُونَ فِيهَا بِكُلِّ فَاكِهَةٍ آمِنِينَ [٤٤:٥٥] በእርሷም ውስጥ የተማመኑ ኾነው፤ ከፍራፍሬ ሁሉ ያዝዛሉ፡፡

لَا يَذُوقُونَ فِيهَا الْمَوْتَ إِلَّا الْمَوْتَةَ الْأُولَىٰ ۖ وَوَقَاهُمْ عَذَابَ الْجَحِيمِ [٤٤:٥٦]

« የፊተኛይቱን ሞት እንጅ (ዳግመኛ) በእርሷ ውስጥ ሞትን አይቀምሱም፡፡ የገሀነምንም ቅጣት (አላህ) ጠበቃቸው፡፡»

فَضْلًا مِّن رَّبِّكَ ۚ ذَٰلِكَ هُوَ الْفَوْزُ الْعَظِيمُ [٤٤:٥٧]

«ከጌታህ በኾነ ችሮታ (ጠበቃቸው)፡፡ ይህ እርሱ ታላቅ ዕድል ነው፡፡»

فَإِنَّمَا يَسَّرْنَاهُ بِلِسَانِكَ لَعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ [٤٤:٥٨]

,«(ቁርኣኑን) በቋንቋህም ያገራነው (ሕዝቦችህ) ይገነዘቡ ዘንድ ብቻ ነው፡፡ »

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ስለጀነት ሰዎች ፀጋ እንዲህ ይላሉ፡- "አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል ለደጋግ ባሪያዎቼ አይን አይታው የማታውቅ፣ ጆሮ ሰምታው የማታውቅ እንዲሁም በሰው ልብ ላይ ውል ብሎ የማያውቀውን አዘጋጅቼላቸዋለሁ፡፡" ማረጋገጫ ከፈለጋችሁ የሚከተለውን የአላህ ንግግር አንብቡ፡፡"

فَلَا تَعْلَمُ نَفْسٌ مَّا أُخْفِيَ لَهُم مِّن قُرَّةِ أَعْيُنٍ جَزَاءً بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ [٣٢:١٧]

«ይሠሩትም በነበሩት ለመመንዳት ከዓይኖች መርጊያ ለእነርሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም፡፡»

በሌላ ሀዲስ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- "በመጀመሪ ወደጀነት የሚገቡት ሰዎች ሙሉ ጨረቃን ይመስላሉ፡፡ በመተከተል የሚገቡት ደግ በጣም አብሪ የሆነውን ኮከብ ይመስላሉ፡፡ ሽንት፣ ሰገራ፣ አክታም ሆነ ምራቅ የለም፡፡ ማበጠሪቸው ከወርቅ የተሰራ ነው፡፡ ላባቸው ሚስክ ነው፡፡ "እጣናቸው ኡልመ" ሚስቶቻቸው ሁረል ኢን ናቸውው፡ ባህሪያቸውም ልክ እንደ አንድ ሰው ባህሪ ነው፡፡ ቁመታቸውም እንደ አባታቸው አዳም 60 ክንድ ነው፡፡ (ሶሂህ ኢብኑ ሂባን)

ጀቢር (ረ.ዐ) ንዳስተላለፉት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ "የጀነት ሰዎች ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ አይተፉም፣ አይሸኑም፣ ሰገራም ሆነ አክታ የላቸውም፡፡" ሰሃቦችም "ታዲያ የሚበሉት የት ይሄዳል?" አሉ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "በማጋሳት እና ሚስክ በሆነ ላብ መልክ ይወጣል፡፡ ሳናስበው እንደምንተነፍሰው ሁሉ እነሱም ተሰቢህ እና ተህሚድ ይላሉ፡፡" (ሰኒህ ሙስሊም)

ዘቢይር አብኒል አርቀም እንዳስተላለፉት፡- አንድ አይሁድ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና "አቡልቃሂም ሆይ! የጀነት ሰዎች ይበላሉ ይጠጣሉ ብለህ ታምናለህን?"አላቸው፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ)

እንዲህ አሉ “ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ፡፡ እያንዳንዳቸው እኮ ለመብላትት ለመጠጣትት ለስሜት እና ለግንኙነት የ100 ሰው ያህል ጉልበት ይሰጣቸዋል፡፡” አይሁዱም “የሚበላ የሚጠጣ ሰው እኮ ሌላ ጉዳይ ይመጣበታል፡፡” አለ፡፡ ረሱልም (ሰ.ዐ.ወ) “ጉዳያቸውን ከሰውነታቸው በሚወጣ ሚስክ በሆነ ላይ ይፈፅማሉ ሆዳቸውንም ይቀንስላቸዋል፡፡” (ሶሂህ ኢብኑ ሂባን)
ኢቡ ሀረይራ፡-(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ተጣሪ እንዲህ ብሉ ይጠራል “ጤነኛ ሁኑ በጨራሽ ህመም አይንካችሁ፣ በህይወት ቆዩ በጭራሽ ሞት የለባችሁም፣ ሁሌም ወጣት ሁኑ መቼም አታረጁም፣ ሁሉ በፀጋ ላይ ቆዩ ፈጽሞ ችግር አይነካችሁም፡፡ ይህም የአላህ (ሱ.ወ) ንግግር ነው፡፡ 7:43” (ሙስሊም)

وَنُودُوا أَن تِلْكُمُ الْجَنَّةُ أُورِثْتُمُوهَا بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ [٧:٤٣]

«ይህች ገነት ትሠሩት በነበራችሁት ተሰጣችኋት በማለት ይጠራሉ፡፡»
ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የጀነት ሰው ዝቅተኛ ሰውን ፀጋ አብራርተዋል፡- እኔ እኮ ከእሳት በመጨረሻ የሚወጣውን ወደጀነት በመጨረሻ የሚገባውን ሰው አውቀዋለሁ፡፡ ከጀሀነም በዳዴ ይወጣል፡፡ አላህም ሂድና ጀነት ግባ ይለዋል፡፡ ይሄድና ጀነትን ሲያያት የሞላች ይመስለዋል፡፡ ይመለስና ጌታዬ ሆይ ጀነት እኮ ሞልታለች ይለዋል፡፡ አላህም በድጋሚ ሂድና ጀነት ግባ ይለዋል፡፡ አሁንም ሂድና ጀነት ግባ ለዋል፡፡ አሁንም ሲሄድ ሞላች ይመስለዋል፡፡ ይመለስና ጌታ ይ ጀነት እኮ ሞልታለች ይላል፡፡ አላህ “ሂድና ጀነት ግባ፡፡ የዱንያን አስር እጥፍ የሚያህል ፀጋ ለአንድ አለህ፡፡” ይለዋል፡፡ ሰውየውም ንጉስ ሆነህ ሳለ በኔ ትቀልድብኛለህን? ይላል፡፡” ዘጋቢውም “የአላህ መልዕክተናና ይህንን ሲናገሩ የመንጋጋቸው ጥርስ እስኪተታ ድረስ ሲስቁ አይቻለሁ፡፡ ይህ ነው እንግዲህ የጀነት ዝቅተናው ሰው የሚያገኘው ደረጃ፡፡ (ስሂህ ቡኻሪ)
በመልዕክተኛው እና እሱ ይዞት በመጣው መልዕክት የካዱ ሰዎች የጀሀነም ባለቤት ሲሆኑ በእርሷ ውስጥም ዘውታሪ ናቸው፡፡

አላህ ((ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَالَّذِينَ كَفَرُوا لَهُمْ نَارُ جَهَنَّمَ لَا يُقْضَىٰ عَلَيْهِمْ فَيَمُوتُوا وَلَا يُخَفَّفُ عَنْهُم مِّنْ عَذَابِهَا ۚ كَذَٰلِكَ نَجْزِي كُلَّ كَفُورٍ [٣٥:٣٦]

«እነዚያ የካዱትም ለእነርሱ የገሀነም እሳት አልላቸው፡፡ ይሞቱ ዘንድ በእነርሱ ላይ (በሞት) አይፈረድም፡፡ ከቅጣቷም ከእነርሱ አይቀለልላቸውም፡፡ እንደዚሁ ከሓዲን ሁሉ እንመነዳለን፡፡»

وَهُمْ يَصْطَرِخُونَ فِيهَا رَبَّنَا أَخْرِجْنَا نَعْمَلْ صَالِحًا غَيْرَ الَّذِي كُنَّا نَعْمَلُ ۚ أَوَلَمْ نُعَمِّرْكُم مَّا يَتَذَكَّرُ فِيهِ مَن تَذَكَّرَ وَجَاءَكُمُ النَّذِيرُ ۖ فَذُوقُوا فَمَا لِلظَّالِمِينَ مِن نَّصِيرٍ [٣٥:٣٧]

«እነርሱም በርሷ ውስጥ እርዳታን በመፈለግ በኀይል ይጮሃሉ፡፡ «ጌታችን ሆይ! ከእዚያ እንሠራው ከነበርነው ሌላ በጎ ሥራን እንሠራ ዘንድ አውጣን» (ይላሉ)፡፡ «በእርሱ ውስጥ ያስታወሰ ሰው የሚገሰጽበትን ዕድሜ አላቆየናችሁምን? አስጠንቃቂውም መጥቶላችኋል (አስተባብላችኋልም)፡፡ ስለዚህ ቅመሱ፡፡ ለበደለኞችም ምንም ረዳት የላቸውም» (ይባላሉ)፡፡»

እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በጀሀነም ውስጥ ያለውን ቀላሉን ቅጣት አብራርተዋል፡፡ "በመጪው አለም ከእሳት ሰዎች ውስጥ ቀላሉን ቅጣት የሚያገኘው ሰው ከውስጥ እግሮቹ ስር ሁለት ፍም ይመጣለ፡፡ እሳት ላይ እንደተጣደ ድስት ጭንቅላቱ ይንተከተካል፡፡" (ሶሂህ ቡኻሪ)

የጀነት ሰዎችን ካሉበት ፀጋ ላይ ሌላ ፀጋን የጀሀነም ሰዎችን ደግሞ ካሉበት ስቃይ ላይ ስቃን የሚጨምርላቸው ነገር ቢኖር ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በሚከተል ሀዲስ የተናገሩት ነው፡፡

"ሞት በሽንጉርጉር በግ ተመስሎ እንዲመታ ይደረጋል፡፡ ከዛም በመቀጠል ተጠሪ ይጠራል "እናንተ የጀነት ሰዎች ሆይ!"፡፡ እነርሱም ተደራርበው ይመጡና ያያሉ፡፡ "ይህን ታውቃላችሁን?" ይላቸዋል፡ ፡ እነርሱም ሁሉም ካዩት በኋላ "አዎን ይህማ ሞት ነው፡፡" ይላሉ ከዛም በኋላ "እናንተ የእሳት ሰዎች ሆይ!" ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነርሱም ተደራርበው ያሉ "ይህንን ታውቁታላችሁን?" ይባላሉ፡፡ እነርሱም ሁሉም ካዩት በኋላ "አዎን ይህማ ሞት ነው ይላሉ፡፡" ከዛም በኋላ ይታረዳል፡፡ በመቀጠልም የጀነት ባለቤቶች ሆይ ከዚህ በኋላ ሞት የሚባል የለም ዘውትሩ፣ የእሳት ሰዎች ሆይ ከዚህ በኋላ ሞት የሚባል የለም ዘውትሩ" ይባላሉ፡፡ የሚቀጥለውን የቁርአን አንቀጽ አንብቡ (19፡ 39) (ቡኸሪ)

በሌላ ሀዲስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡-

"ሁሉም ጀነት የሚገባ ሰው ማመስገንን እንዲጨምር መጥፎ ሰሪ ሆኖ በነበር የሚገባበትን የጀሀነም ቦታ እንዲያይ ይደረጋል፡፡ እንደዚሁም ጀነትም የሚገባ ሰው ሁሉ ቁጭቱ እንዲጨምር ጥሩ ሰሪ ሆኖ በነበር የሚገባበትን የጀነት ቦታ እንዲያይ ይደረጋል፡፡" ከዚያ በኋላ ትክክለኛው እና ዘውታሪው ህይወት ይጀምራል፡፡ እናም የተዘጋጀለት ና የለፋለት ሰዎች ብቻ ደስተና ሆነው ይኖራሉ፡፡

## ስለመቀስቀስ ቁርአናዊ ማስረጃዎች

ቁርአን በብዙ አንቀፆች የሰው ልጅን ስለመሠረቱ እንዲያስብና እንዲስተነትን አሳስቧል፡፡ ምንም ካልነበረበት ያስገኘው ከተገኘ በኋላ መልሶ ማስገኘትን ቻይ ነው፡፡

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَيَقُولُ الْإِنسَانُ أَإِذَا مَا مِتُّ لَسَوْفَ أُخْرَجُ حَيًّا [١٩:٦٦]

« ሰውም «በሞትኩ ጊዜ ወደፊት ሕያው ኾኜ (ከመቃብር) እወጣለሁን=» ይላል፡፡»

أَوَلَا يَذْكُرُ الْإِنسَانُ أَنَّا خَلَقْنَاهُ مِن قَبْلُ وَلَمْ يَكُ شَيْئًا [١٩:٦٧]

« ሰው ከአሁን በፊት ምንም ነገር ያልነበረ ሲኾን እኛ የፈጠርነው መኾኑን አያስታውስምን=»

* *መሬት ምንም የህይወት ፋና በማይታይባት መልኩ ደርቃ ከሞተች በኋላ አላህ ህይወት ይዘራበት እና ቡቃያዎችን ማብቀል ትጀምራለች፡፡*

፡-

وَمِنْ آيَاتِهِ أَنَّكَ تَرَى الْأَرْضَ خَاشِعَةً فَإِذَا أَنزَلْنَا عَلَيْهَا الْمَاءَ اهْتَزَّتْ وَرَبَتْ ۚ إِنَّ الَّذِي أَحْيَاهَا لَمُحْيِي الْمَوْتَىٰ ۚ إِنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ [٤١:٣٩]

«አንተ ምድርን ደረቅ ኾና ማየትህም ከምልክቶቹ ነው፡፡ በእርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ (በቡቃያዎችዋ) ትላወሳለች፡፡ ትነፋለችም፡፡ ያ ሕያው ያደረጋት ጌታ በእርግጥ ሙታንን ሕያው አድራጊ ነው፡፡ እነርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና፡፡»

* አላህ (ሰ.ወ) የሰውን ልጅ ከመፍጠር የሚልቁትን የሰማይና የመሬት አፈጣጠር እንድናስተነትን ይነግረናል፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

أَوَلَمْ يَرَوْا أَنَّ اللَّهَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ وَلَمْ يَعْيَ بِخَلْقِهِنَّ بِقَادِرٍ عَلَىٰ أَن يُحْيِيَ الْمَوْتَىٰ ۚ بَلَىٰ إِنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ [٤٦:٣٣]

«ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ እነርሱንም በመፍጠሩ ያልደከመው አላህ ሙታንን ሕያው በማድረግ ላይ ቻይ መኾኑን አላስተዋሉምን? (በማስነሳት) ቻይ ነው፡፡ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና፡፡»

* እንደዚሁም ተኝተን መነሳታችንን እንደምናስበው ይመክረናል፡፡ ይህ ክስተት ሞቶ ከመነሳት ጋር በጣም ተመሳሳይነት አለው፡፡ ትንሹ ሞት በመባልም ይታወቃል፡፡

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

اللَّهُ يَتَوَفَّى الْأَنفُسَ حِينَ مَوْتِهَا وَالَّتِي لَمْ تَمُتْ فِي مَنَامِهَا ۖ فَيُمْسِكُ الَّتِي قَضَىٰ عَلَيْهَا

الْمَوْتَ وَيُرْسِلُ الْأُخْرَىٰ إِلَىٰ أَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ [٣٩:٤٢]

«አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል፡፡ ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ (ይወስዳታል)፡፡ ታዲያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል፡፡ ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቅቃታል፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አልሉበት፡፡»

- ኢስ ቢን ዋኢል የሚባል ከሀዲ ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የበሰበሰ አጥንት አምጥቶ ሰባበረውና "አንተ ሙሐመድ ሆይ! አላህ ይህንን አፈር ከሆነ በኋላ ይቀሰቅሰዋልን?" አላቸው፡፡ እሳቸውም "አዎን ይቀሰቅሰዋል፡፡ አንተንም ይገድልሀል፡፡ ከዛም ይቀሰቅስሀል ከዛም ጀሀነም ይከትሃል፡፡" አሉት፡፡ ይህች የቁርአን አንቀጽ እሱን አስመልክቶ ወረደች፡፡ (ኢብኑ ሂባን)

أَوَلَمْ يَرَ الْإِنسَانُ أَنَّا خَلَقْنَاهُ مِن نُّطْفَةٍ فَإِذَا هُوَ خَصِيمٌ مُّبِينٌ [٣٦:٧٧]

«ሰውየው እኛ ከፍቶት ጠብታ የፈጠርነው መኾናችን አላወቀምን? ወዲያውም እርሱ (ትንሣኤን በመካድ) ግልጽ ተከራካሪ ይኾናልን?»

وَضَرَبَ لَنَا مَثَلًا وَنَسِيَ خَلْقَهُ ۖ قَالَ مَن يُحْيِي الْعِظَامَ وَهِيَ رَمِيمٌ [٣٦:٧٨]

ለእኛም ምሳሌን አደረገልን፡፡ መፈጠሩንም ረሳ፡፡ «አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲኾኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?» አለ፡፡

قُلْ يُحْيِيهَا الَّذِي أَنشَأَهَا أَوَّلَ مَرَّةٍ ۖ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيمٌ [٣٦:٧٩]

«ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል፡፡ እርሱም በፍጡሩ ሁሉ (ኹኔታ) ዐዋቂ ነው» በለው፡፡»

الَّذِي جَعَلَ لَكُم مِّنَ الشَّجَرِ الْأَخْضَرِ نَارًا فَإِذَا أَنتُم مِّنْهُ تُوقِدُونَ [٣٦:٨٠]

«ያ ለእናንተ በእርጥብ ዛፍ እሳትን ያደረገላችሁ ነው:: ወዲያውኑም እናንተ ከእርሱ ታቀጣጥላላችሁ::»

أَوَلَيْسَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ بِقَادِرٍ عَلَىٰ أَن يَخْلُقَ مِثْلَهُم ۚ بَلَىٰ وَهُوَ الْخَلَّاقُ الْعَلِيمُ [٣٦:٨١]

«ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ብጤያቸውን በመፍጠር ላይ ቻይ አይደለምን? ነው እንጅ:: እርሱም በብዙ ፈጣሪው ዐዋቂው ነው::»

إِنَّمَا أَمْرُهُ إِذَا أَرَادَ شَيْئًا أَن يَقُولَ لَهُ كُن فَيَكُونُ [٣٦:٨٢]

ነገሩም አንዳችን በሻ ጊዜ ኹን ማለት ነው:: ወዲያው ይኾናልም::

فَسُبْحَانَ الَّذِي بِيَدِهِ مَلَكُوتُ كُلِّ شَيْءٍ وَإِلَيْهِ تُرْجَعُونَ [٣٦:٨٣]

«ያ የነገሩ ሁሉ ስልጣን በእጁ የኾነው ጌታ ጥራት ይገባው:: ወደእርሱም ትመለሳላችሁ::»

## ራስን እንዴት ማዳን ይቻላል::

**ትክክለኛውን እና ተቀባይነት ያለውን እንዲሁም ከአላህ እዝነት ጋር ወደ እውነተኛ እና ዘላቂ ደስታ የሚያደርስህንና በተቃራኒው ደግሞ በአላህ ፍቃድ ከችግር እና ጉስቁልና ኑሮ የሚያወጣህን ሀይማኖት ማወቅ የፈለክ ግዜ ይህ ሀይማኖት ወደ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የወረደ የእስልምና ሀይማኖት መሆኑን እወቅ::**

## እስልምና ምንድን ነው?

**እስልምና ወደነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የወረደ ሀይማኖት ሲሆን ከሱ በፊት የነበሩትን ሀይማኖቶች ሰርዟል:: አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ብሏል:-**

هُوَ الَّذِي أَرْسَلَ رَسُولَهُ بِالْهُدَىٰ وَدِينِ الْحَقِّ لِيُظْهِرَهُ عَلَى الدِّينِ كُلِّهِ وَلَوْ كَرِهَ الْمُشْرِكُونَ

[٩:٣٣]

«እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛውን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነው::»

**አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሀይማኖትም እሱ ብቻ ነው:: ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከመላካቸው በኋላ ከእስልምና ውጪ ያሉ ሀይማኖቶች ሁሉ ተቀባይነት የላቸውም:: አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል:0-**

وَمَن يَكْفُرْ بِهِ مِنَ الْأَحْزَابِ فَالنَّارُ مَوْعِدُهُ ۚ

«ከአሕዛቦቹም በእርሱ የሚክድ ሰው እሳት መመለሻው ናት፡፡»

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- ከህዝቦቼ መሀል አንዳቸው አይሁድም ይሁኑ ክርስቲያን ስለኔ ሰምቶ በተላኩት ነገር ሳያምን ከሞተ የእሳት ሰው መሆኑ እርግጥ ነው፡፡

የእስልምና ትርጉም ለአላህ እጅ መስጠት እና ይሁንታን በሱ ማስገዛት እንዲሁም በአላህ ላይ ከማጋራት መቆጠብ ነው፡፡ በአለም ላይም ከ1.5 ቢሊየን ሰው በላይ የሚከተለው ሀይማኖት ሆኖ ሳለ ታዲያ ይህ ሁሉ ህዝብ በስህተት አንደ ደግሞ ትክክለኛ መንገድ ላይ ነኝ ብለህ ታስባለህን? ምንም እንኳ ሀይማኖቱን ለማስፋፋት የሚውለው ቁሳዊ እና ሰዋዊ ሀብት ደካማ ቢሆንም ሰዎች በብዛት እየገቡ የሚቀላቀሉት ሀይማኖት ነው፡፡ ሀይማኖቱን አምኖ ከተቀበለ በኋላ ተመልሶ የሚክድ ሰው በጣም ትንሽ ነው፡፡

## የእስልምና ሀይማኖት ዋነኛ መሠረቶች

1. **ሸሀደተይን**

   እነርሱም ከአላህ ውጪ ለመሊክ የሚገባው አለመኖሩን እና ሙሐመድም የአላህ ባሪ እና መልዕክተና መሆናቸውን መመስከር ናቸው፡፡ ይህ መሠረት ወደ እስልምና ለመግባት ቁልፍ ሲሆን ሌሎቹ መሠረቶችም በሱላይ ነው የሚገኑት፡፡

   የአላህ አለላህ ትርጉም፡-

   - ለዚህ ፍጥረተ አለም ከአላህ ውጪ ፈጣሪ የለም
   - በዚህ ፍጥረተ አለም ውስጥ ንጉስም ሆነ የፈለገውን አድራጊ ከአላህ ውጪ የለም፡፡
   - አምልኮት የሚገባው ከአላህ ውጪ የለም፡፡ የሚሉትን አካትቶ ይይዛል፡፡

"ሙሐመድ የአላህ መልዕክተና ናቸው" የማለት ትርጉም

እርሳቸው፡ - የአላህ ባሪያ እና መልዕክተኛ መሆናቸውን ማመን

- ራዕይ እንደወረደላቸው ማመን
- ለሰዎች ሙሉ እንዲያደርሱ መታዘዛቸውን ማመን
- በእርሳቸው ነብይነት እንደተደመደበ እና ከሳቸው በኋላ ሌላ ነብይ እንደማይመታ ማመን፡፡
- ያዘዙትን ነገር መታዘዝ፣ የተናገሩትን ነገር እውነት ማለት፣ የከለከሉትን ነገር መከልከልን አጠቃሎ ይይዛል፡፡

2. **ሰላት**፡- አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَأَقِمِ الصَّلَاةَ ۖ إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَىٰ عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ ۗ وَلَذِكْرُ اللَّهِ أَكْبَرُ ۗ

وَاللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَصْنَعُونَ [٢٩:٤٥]

«ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡ አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል፡፡»

ሰላት በባሪያ እና በጌታ መሀል መገናኛ ድልድይ ስትሆን በሁሉም ወቀት ከጌታችን ጋር እንዳንለያይ ትጠብቀናለች። በ24 ሰዓት ውስጥ ሙስሊሞች 5ግዜ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር በመስጊድ ውስጥ እየተገናኙ የሚፈፅሙት አምልኮ ነው። በዚህ ግንኙነት ሙስሊሞች እርስ በእርሳቸው ይተዋወቃሉ። ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶች የማይታይበትና የሚረሱበት ቦታ ነው። ሁሉም ሙስሊም ትልቅ ትንሽ፣ ሀብታም ድሀው፣ ባለስልጣኑ ተራው ሳይለይ በእኩልነት ከአላህ ፊት ተነካክተው የሚቆሙበት ቦታ ነው።

3. __ዘካ__፡- አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ላል፡-

خُذْ مِنْ أَمْوَالِهِمْ صَدَقَةً تُطَهِّرُهُمْ وَتُزَكِّيهِم بِهَا

«ከገንዘቦቻቸው ስትኾን በእርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የኾነችን ምጽዋት ያዝ፡፡»

ዘካ ሀብታም ሙስሊሞች ደሀ ባለጉዳይ እና ሚስኪን ሙስሊሞችን እንዳይቸገሩ እና የመለመን ውርደት እንዳያገኛቸው በተወሰነ መስፈርት የሚሰጡት የተወሰነ ገንዘብ ነው። የዚህ እስልምና መሠረት ዋና አላማው ከህብረተሰቡ ውስጥ ድህነትን እና የድህነት መዘዞችን እንደ ስርቆት፣ ግድያ እና የመሳሰሉትን ማጥፋት ነው። በሙስሊሞች መሀልም የመደጋፍ እና የማህበረሰባዊ ሃላፊነት ስሜት ህያው የማድረግ ጥቅም አለው። አላህ (ሰ.ወ) ዘካው የሚገባቸውን ሰዎች እንዲህ በማለት ዘርዝሮልናል፡-

إِنَّمَا الصَّدَقَاتُ لِلْفُقَرَاءِ وَالْمَسَاكِينِ وَالْعَامِلِينَ عَلَيْهَا وَالْمُؤَلَّفَةِ قُلُوبُهُمْ وَفِي الرِّقَابِ وَالْغَارِمِينَ

وَفِي سَبِيلِ اللَّهِ وَابْنِ السَّبِيلِ ۖ فَرِيضَةً مِّنَ اللَّهِ ۗ وَاللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ [٩:٦٠]

«ግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድኾች፣ ለምስኪኖችም፣ በርሷም ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች፣ ልቦቻቸውም (በእስልምና) ለሚለማመዱት፣ ጫንቃዎችንም (በባርነት ተገዢዎችን) ነጻ በማውጣት፣ በባለ ዕዳዎችም፣ በአላህ መንገድም በሚሠሩ፣ በመንገደኛም ብቻ ነው፡፡ ከአላህ የተደነገገች ግዴታ ናት፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡»

ዘካ የሀብታሞችን ልብ ከቋጣሪነት፣ ከስግብግብነት፣ ከዱንያ ፍቅር እና በብልጭልጭ ተታላይ ከመሆን ይጠብቃል ያጠራልም፡፡ እንደዚሁም የደሀዎችን ልብ ከጥላቻ እና ከምቀኝነት ይጠብቃል ያጠራልም፡፡

4. <u>የረመዷን ፆም</u>

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ

تَتَّقُونَ [٢:١٨٣]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡»

ሙስሊሞች ከአመቱ ውስጥ አንዷን ወር ፀሀይ ከመውጣቷ አንስቶ ፀሀይ እስኪገባ ድረስ ምግብ ከመብላት፣ መጠጥ ከመጠጣት እና ሚስትን ከመገናኘት በመቆጠብ ያመው ይውላሉ፡፡ ይህ አምልኮ በእስልምና ብቻ ያለ ለየት ያለ ነገር ሳይሆን እሱ ከመምጣቱ በፊት በነበሩ ህዝቦች ላይም የነበረ ግዴታ ነው፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ

تَتَّقُونَ [٢:١٨٣]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡»

ያም ሲባል ብዙ ሰው እንደሚረዳው እንደምግብ እና መጠጥ ካሉ ቁሳዊ ከሆኑ ነገራቶች ብቻ መቆጠብ ሳይሆን መንፈሳዊ ከሆኑ ያምን ከሚጎድፉ ነገራቶች መቆጠብ ተገቢነው፡፡ በዚህም መሠረት ከውሸት፣ ከሀሜት፣ ነገር-------------፣ ከማታለል፣ ከመክዳት፣ ከዛዛት እና ከመሳሰሉት መጥፎ ነገር መራቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን እነዚህ ነገራቶች አንድ ሰው ያመኛ እስካልሆነ ድረስ ይፈቀዳሉ ማለት አይደለም፡፡ ረመዳን ላይ ሲሆን ይበልጥ ይርቃቸዋል ለማለት ተፈልጎ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- "ውሸት መናገሬን እና በሱ መስራትን ያልተወ ሰው አላህ (ሰ.ወ) ምግብና መጠጥ ከመተው ጉዳይ የለውም፡፡" (ሰኒህ ቡኻሪ)

5. <u>ሀጅ</u>

ሀጅ ማለት በተወሰነ ግዜ፣ በተወሰኑ ቦታዎች የሚሰሩ የተወሰኑ ሥራዎችን ለመስራት ብሎ ወደተከበረው የአላህ ቤት መጓዝ ነው፡፡ ይህ መሠረት ግዴታ የሚሆነው አዕምሮው ጤናው በሆነ፣ በአቅማዳም በደረሰ እና የአካል እና የገንዘብ አቅም ባላቸው ወንድም ይሁን ሴት ሙስሊም ላይ ሲሆን በእድሜ ቆይታ አንድ ጊዜ ብቻ መሄድ በቂ ይሆናል፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَلِلَّهِ عَلَى النَّاسِ حِجُّ الْبَيْتِ مَنِ اسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلًا ۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ اللَّهَ غَنِيٌّ عَنِ الْعَالَمِينَ [٣:٩٧]

«ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡»

ለሀጅ የሚደረገው አምልኳዊ ስብሰባ በእስልምና ትልቁ የሙስሊሞች መሰብሰቢየ ሲሆን በዚህ ስብሰባ ሙስለሞች በአንድ ቦታ፣ በተወሰነ ግዜ፣ አንድን ጌታ እየለመኑ፣ ተመሳሳይ ልብስ ለብሰው፣ ተመሳሳይ ስራ እየሰሩ ይቆያሉ፡፡

ደሀና ሀብታም፣ ተራ እና ባለስልጣን፣ ነጭ እና ጥቁር፣ አረብና አረብ ያልሆነ ሁሉ በእኩልነት አላህ ፊት እሱን በመፍራት እንጂ በሌላ ነገር ሳይሌዩ ይቆማሉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በሙስሊሞች መሀል ያለው ወንድማማችነት ጠንካራ ስለሆነና አላማቸው እና ስሜታቸው ተመሳሳይ ስለሆነ ነው፡፡

## <u>የእምነት መሰረቶች</u>

1. <u>በአላህ ማመን</u>

አላህ በመኖሩ ማመን የሚከተሉተን አካትቶ ይይዛል፡-

* ከሱ ውጪ ሌላ አምላክ አለመኖሩን እና በፈጣሪነትም፣ በተንከባካቢነቱም ሆነ በአስተባባሪነቱ ሌላ ተጋሪ አለመኖሩን

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

أَلَا لَهُ الْخَلْقُ وَالْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ اللَّهُ رَبُّ الْعَالَمِينَ [٧:٥٤]

«ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡»

* **በአምልኮትም እንዲሁ ተጋሪ አለመኖሩን**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِي إِلَيْهِ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنَا فَاعْبُدُونِ [٢١:٢٥]

«ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም፡፡»

* **በስሞቹም ሆነ በባህሪያቶቹ ተጋሪ አለመኖሩን አካትቶ ይዟል**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَلِلَّهِ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ فَادْعُوهُ بِهَا ۖ وَذَرُوا الَّذِينَ يُلْحِدُونَ فِي أَسْمَائِهِ ۚ

«ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፡፡ (ስትጸልዩ) በእርሷም ጥሩት፡፡ እነዚያንም ስሞቹን የሚያጣምሙትን ተውዋቸው፡፡»

* **አምልኮ የሚገባው እሱ ብቻ ሲሆን ማንኛውም አይነት አምልኮ ለሱ ብቻ ሊደረግ ተገቢ ነው፡፡**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ [٦:١٦٢]

«ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል፡፡»

لَا شَرِيكَ لَهُ ۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ [٦:١٦٣]

«ለእርሱ ተጋሪ የለውም፡፡ በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ፡፡ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)፡፡ ››

**ለአላህ (ሰ.ወ) የሚያማምሩ ስሞች እና የላቁ ባህሪያቶች አሉት፡፡**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَلِلَّهِ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ فَادْعُوهُ بِهَا ۖ وَذَرُوا الَّذِينَ يُلْحِدُونَ فِي أَسْمَائِهِ ۚ سَيُجْزَوْنَ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ [٧:١٨٠]

« ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፡፡ (ስትጸልዩ) በእርሷም ጥሩት፡፡ እነዚያንም ስሞቹን የሚያጣምሙትን ተውዋቸው፡፡ ይሠሩት የነበሩትን ነገር በእርግጥ ይምመነዳሉ፡፡»

**ከጎዶሎ እና ነውር ካለው ነገር ሁሉ የጠራ ነው፡፡**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ ۖ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ [٤٢:١١]

«የሚመስለው ምንም ነገር የለም፡፡ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡»

2. **<u>በመልዓኮች ማመን</u>**

**ይህም ለአላህ (ሰ.ወ) ቁጥራቸው የማይታወቅ ብዙ መላኢኮች እንዳሉት ማመን ነው፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እነርሱን የፈጠረበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- ✓ **እሱን እንዲገዙት፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

لَّن يَسْتَنكِفَ الْمَسِيحُ أَن يَكُونَ عَبْدًا لِّلَّهِ وَلَا الْمَلَائِكَةُ الْمُقَرَّبُونَ ۚ

«አልመሲሕ (ኢየሱስ) ለአላህ ባሪያ ከመኾን ፈጽሞ አይጠየፍም፡፡ ቀራቢዎች የኾኑት መላእክትም (አይጠየፉም)፡፡»

- ✓ **አላህ (ሰ.ወ) ስራ የሚላቸውን ስራ እንዲፈጽሙ፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

عَلَيْهَا مَلَائِكَةٌ غِلَاظٌ شِدَادٌ لَّا يَعْصُونَ اللَّهَ مَا أَمَرَهُمْ وَيَفْعَلُونَ مَا يُؤْمَرُونَ [٦٦:٦]

«በእርሷ ላይ ጨካኞች፣ ኀይለኞች የኾኑ መላእክት አልሉ፡፡ አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም፡፡ የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ፡፡»

* **መላዕኮች ባጠቃላይ አላህ ልጅም ሆነ ጓደኛ አይደሉም፡፡**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَقَالُوا اتَّخَذَ الرَّحْمَٰنُ وَلَدًا ۗ سُبْحَانَهُ ۚ بَلْ عِبَادٌ مُّكْرَمُونَ [٢١:٢٦]

«አልረሕማንም (ከመላእክት) ልጅን ያዘ» አሉ፡፡ ጥራት ተገባው፡፡ አይደለም (መላእክት) የተከበሩ ባሮች ናቸው፡፡»

لَا يَسْبِقُونَهُ بِالْقَوْلِ وَهُم بِأَمْرِهِ يَعْمَلُونَ [٢١:٢٧]

«በንግግር አይቀድሙትም፤ (ያላለውን አይሉም)፡፡ እነርሱም በትእዛዙ ይሠራሉ፡፡»

**ከነሱ መሀከል አላህ (ሰ.ወ) ስማቸውንና ስራቸውን የነገረን እንዳለ ሁሉ ያልነገረንም አሉ፡፡ ነገር ግን በሁሉም ማመን ግዴታ ነው፡፡**

3. **<u>በመፅሀፍቶች ማመን</u>**

**ይህም አላህ (ሰ.ወ) ለሰዎች መልዕክቱን ለማድረስ በመልዕክተኞቹ ላይ ሰማያዊ መፅሀፎችን እንዳወረደ ማመን ነው፡፡**

**ከነዚህ መፅሀፍቶች መሀል**

**1ኛው. ተውረት፡- ወደ ሙሣ (ዐ.ሰ) የወረደ የተቀደሰ ሰማያዊ መፅሀፍ ነው፡፡**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

إِنَّا أَنزَلْنَا التَّوْرَاةَ فِيهَا هُدًى وَنُورٌ ۚ يَحْكُمُ بِهَا النَّبِيُّونَ الَّذِينَ أَسْلَمُوا لِلَّذِينَ هَادُوا وَالرَّبَّانِيُّونَ وَالْأَحْبَارُ بِمَا اسْتُحْفِظُوا مِن كِتَابِ اللَّهِ وَكَانُوا عَلَيْهِ شُهَدَاءَ ۚ فَلَا تَخْشَوُا النَّاسَ وَاخْشَوْنِ وَلَا تَشْتَرُوا بِآيَاتِي ثَمَنًا قَلِيلًا ۚ وَمَن لَّمْ يَحْكُم بِمَا أَنزَلَ اللَّهُ فَأُولَٰئِكَ هُمُ الْكَافِرُونَ [٥:٤٤]

«እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በእነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በኾኑት (ይፈርዳሉ)፡፡ ሰዎችንም አትፍሩ፡፡ ፍሩኝም፡፡ በአንቀጾቼም አነስተኛን ዋጋ አትለውጡ፡፡ አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡»

**2ኛው. ኢንጂል፡- ወደ ኢሳ (ዐ.ሰ) የወረደ የተቀደሰ ሰማያዊ መጽሀፍ ነው፡፡**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَقَفَّيْنَا عَلَىٰ آثَارِهِم بِعِيسَى ابْنِ مَرْيَمَ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ التَّوْرَاةِ ۖ وَآتَيْنَاهُ الْإِنجِيلَ

فِيهِ هُدًى وَنُورٌ وَمُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ التَّوْرَاةِ وَهُدًى وَمَوْعِظَةً لِّلْمُتَّقِينَ [٥:٤٦]

« በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፡፡ ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው፡፡»

3ኛው. ቁርአን፡- በጅብሪል (ዐ.ሰ) አማካኝነት ወደ መሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) የወረደ የአላህ ንግግር ነው፡፡ የመጨረሻው ሰማያዊ መጽሀፍ ነው፡፡ ከሱ በፊት የነበሩት ሰማያዊ መፅሀፍቶችን ሁሉ ሽሯል፡፡

4. **<u>በመልዕክተኞች ማመን</u>**

ይህም አላህ (ሰ.ወ) ከፍጡራኖች መሀል ነብዮቹን እንደመረጠ፣ መፅሀፍ እና ህግ እንደሰጣቸው እና ሰዎች አላህ ላይ መከራከሪያ ነጥብ እንዳይኖራቸው መልዕክቱን ለሰዎች እንዲያዳርሱ መታዘዛቸውን ማመን ነው፡፡ የአላህ (ሰ.ወ) መልዕክተኞች እና ነብዮች ቁጥራቸው በጣም ብዙ ሲሆን ከአላህ ውጪ ማንም አያውቀውም፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلًا مِّن قَبْلِكَ مِنْهُم مَّن قَصَصْنَا عَلَيْكَ وَمِنْهُم مَّن لَّمْ نَقْصُصْ

عَلَيْكَ ۗ

« ካንተ በፊትም መልክተኞችን በእርግጥ ልከናል፡፡ ከእነርሱ ባንተ ላይ የተረክንልህ አልለ፡፡ ከእነርሱም ባንተ ላይ ያልተረክነው አልለ፡፡»

ነብዮች በሙሉ ደግሞ የተመረጡት ከሰው ዘር ብቻ ነው፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ إِلَّا رِجَالًا نُّوحِي إِلَيْهِمْ ۚ فَاسْأَلُوا أَهْلَ الذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ

[١٦:٤٣]

አላህ (ሰ.ወ) ስለ ሚሳ (ዐ.ሰ) ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

مَّا الْمَسِيحُ ابْنُ مَرْيَمَ إِلَّا رَسُولٌ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِهِ الرُّسُلُ وَأُمُّهُ صِدِّيقَةٌ ۖ كَانَا يَأْكُلَانِ

الطَّعَامَ ۗ انظُرْ كَيْفَ نُبَيِّنُ لَهُمُ الْآيَاتِ ثُمَّ انظُرْ أَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ [٥:٧٥]

« የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፡፡ (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት፡፡»

**በሁሉም መልዕክተኞች ማመን ግዴታ ነው በከፊሎቹ አምኖ ቀሪዎቹን የካደ ሰው አላህ (ሰ.ወ) እንደገለጸው ከሀይማኖቱ ይወጣል፡፡**

إِنَّ الَّذِينَ يَكْفُرُونَ بِاللَّهِ وَرُسُلِهِ وَيُرِيدُونَ أَن يُفَرِّقُوا بَيْنَ اللَّهِ وَرُسُلِهِ وَيَقُولُونَ نُؤْمِنُ بِبَعْضٍ وَنَكْفُرُ بِبَعْضٍ وَيُرِيدُونَ أَن يَتَّخِذُوا بَيْنَ ذَٰلِكَ سَبِيلًا [٤:١٥٠]

« እነዚያ በአላህና በመልክተኞቹ የሚክዱ፣ በአላህና በመልክተኞቹም መካከል መለየትን የሚፈልጉ፣ «በከፊሉም እናምናለን በከፊሉም እንክዳለን» የሚሉ፣ በዚህም መካከል መንገድን ሊይዙ የሚፈልጉ፤»

أُولَٰئِكَ هُمُ الْكَافِرُونَ حَقًّا ۚ وَأَعْتَدْنَا لِلْكَافِرِينَ عَذَابًا مُّهِينًا [٤:١٥١]

«እነዚያ በውነት ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡ ለከሓዲዎችም አዋራጅን ቅጣት አዘጋጅተናል፡፡››

**የመጀመሪው ረሱል ኑህ (ዐ.ሰ) ሲሆን የመጨረሻው እና መደምደሚያው ደግሞ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው፡፡**

5. **<u>በመጨረሻው ቀን ማመን</u>**

**ይህም የዚህ አለም ኑሮ የሚያልቅበት እና የሚጠፋበት ቀን መኖሩን ማመን ነው፡፡**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

كُلُّ مَنْ عَلَيْهَا فَانٍ [٥٥:٢٦]

በእርሷ (በምድር) ላይ ያለው ሁሉ ጠፊ ነው፡፡

وَيَبْقَىٰ وَجْهُ رَبِّكَ ذُو الْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ [٥٥:٢٧]

«የልቅናና የልግሥና ባለቤት የኾነው የጌታህ ፊትም ይቀራል፡፡ (አይጠፋም)፡፡»

በመጨረሻው ቀን ማመን ሲባል፡-

1. **የበርዙኽ ዓለም መኖሩን ማመን**፡- በርዙኽ አንድ ሰው ከሞተ አንስቶ እስከመጨረሻው ቀን ድረስ ያለው ግዜ ነው፡፡ በዚህ አለም ላይ አማኞች እንደሚሸለሙ እና በፀጋ ላይ እንደሚቆዩ ከሀዲዎች እና አስተባባዮች ደግሞ በቅጣት ላይ እንደሚቆዩ ማመን፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَحَاقَ بِآلِ فِرْعَوْنَ سُوءُ الْعَذَابِ [٤٠:٤٥]

«በፈርዖን ቤተሰቦችም ላይ ክፉ ቅጣት ሰፈረባቸው፡፡»

2. **በመቀስቀስ ማመን**

   አላህ (ሰ.ወ) ፍጢራኑን በሙሉ በፊቱ አቁሞ ለመዳኘት ከሞቱበት ይቀሰቅሳቸዋል፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

زَعَمَ الَّذِينَ كَفَرُوا أَن لَّن يُبْعَثُوا ۚ قُلْ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتُبْعَثُنَّ ثُمَّ لَتُنَبَّؤُنَّ بِمَا عَمِلْتُمْ ۚ

وَذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ [٦٤:٧]

«እነዚያ የካዱትን በፍጹም የማይቀሰሱ መኾናቸውን አሰቡ፡፡ «አይደለም በጌታዬ እምላለሁ፡፡ በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ፡፡ ከዚያም በሠራችሁት ሁሉ ትነገራላችሁ፡፡ ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው፡፡ » በላቸው፡፡»

3. **ወደ ፍርድ በመነዳት ማመን**፡- ሰው ሁሉ በሰራው ለመዳን ወደ አላህ ይጓዛል፡፡

   አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

إِنَّ يَوْمَ الْفَصْلِ كَانَ مِيقَاتًا [٧٨:١٧]

«የመለያው ቀን የተወሰነ ጊዜ ነው፡፡»

4. **ለመዳኘት አላህ ፊት ቢሰለፉ እንደምንም ቆሞ ማመን**፡፡

   አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَعُرِضُوا عَلَىٰ رَبِّكَ صَفًّا لَّقَدْ جِئْتُمُونَا كَمَا خَلَقْنَاكُمْ أَوَّلَ مَرَّةٍ ۚ بَلْ زَعَمْتُمْ أَلَّن

نَّجْعَلَ لَكُم مَّوْعِدًا [١٨:٤٨]

«የተሰለፉም ኾነው በጌታህ ላይ ይቀረባሉ፡፡ (ይባላሉም) «በመጀመሪያ ጊዜ እንደ ፈጠርናችሁ (ራቁታችሁን) በእርግጥ መጣችሁን= በእውነቱ ለእናንተ (ለመቀስቀሻ) ጊዜን አናደርግም መሰሏችሁ ነበር፡፡»

5. **ሰርተን ባሳለፍነው ነገር እንደምንጠየቅ ማወቅ**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَقِفُوهُمْ ۖ إِنَّهُم مَّسْئُولُونَ [٣٧:٢٤]

የሚወቃቀሱም ሆነው ከፊላቸው በከፊሉ ላይ ይመጣሉ፡፡

قَالُوا إِنَّكُمْ كُنتُمْ تَأْتُونَنَا عَنِ الْيَمِينِ [٣٧:٢٨]

(ለአስከታዮቹ) እናንተ ከስተቀኝ ትመጡብን ነበር ይላሉ፡፡

6. **አካላቶቻችን ስንሰራው በነበረው ነገር እንደሚመሰክሩብን ማመን፡፡**

**አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይለል፡-**

حَتَّىٰ إِذَا مَا جَاءُوهَا شَهِدَ عَلَيْهِمْ سَمْعُهُمْ وَأَبْصَارُهُمْ وَجُلُودُهُم بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ

[٤١:٢٠]

«በመጧትም ጊዜ ጆሮዎቻቸው፣ ዓይኖቻቸውና ቆዳዎቻቸውም ይሠሩት በነበሩት ነገር በእነርሱ ላይ ይመሰክሩባቸዋል፡፡»

وَقَالُوا لِجُلُودِهِمْ لِمَ شَهِدتُّمْ عَلَيْنَا ۖ قَالُوا أَنطَقَنَا اللَّهُ الَّذِي أَنطَقَ كُلَّ شَيْءٍ وَهُوَ

خَلَقَكُمْ أَوَّلَ مَرَّةٍ وَإِلَيْهِ تُرْجَعُونَ [٤١:٢١]

«ለቆዳዎቻቸውም «በእኛ ላይ ለምን መሰከራችሁብን?» ይላሉ፡፡ «ያ አንዳቹን ነገር ሁሉ ያናገረው አላህ አናገረን፡፡ እርሱም በመጀመሪያ ጊዜ ፈጠራችሁ፡፡ ወደእርሱም ትመለሳላችሁ» ይሏቸዋል፡፡»

وَمَا كُنتُمْ تَسْتَتِرُونَ أَن يَشْهَدَ عَلَيْكُمْ سَمْعُكُمْ وَلَا أَبْصَارُكُمْ وَلَا جُلُودُكُمْ وَلَٰكِن ظَنَنتُمْ

أَنَّ اللَّهَ لَا يَعْلَمُ كَثِيرًا مِّمَّا تَعْمَلُونَ [٤١:٢٢]

«ጆሮዎቻችሁ ዓይኖቻችሁና ቆዳዎቻችሁም በእናንተ ላይ ከመመስከራቸው የምትደበቁ አልነበራችሁም፡፡ ግን አላህ ከምትሠሩት ብዙውን አያውቅም ብላችሁ ጠረጠራችሁ፡፡»

7. **እንደ የስራችን ከመመንዳት በፊት ሂሳብ በመኖሩ ማመን፡፡ ነብያቶችን የተቀቡ እና በጎ ሥራዎች ላይ ያዘወተሩ የማይገባችን ቅጣት ያገኛሉ፡፡**

   **አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

فَأَمَّا مَنْ أُوتِيَ كِتَابَهُ بِيَمِينِهِ [٨٤:٧]

መጽሐፉን በቀኙ የተሰጠ ሰውማ፤

فَسَوْفَ يُحَاسَبُ حِسَابًا يَسِيرًا [٨٤:٨]

«በእርግጥ ቀላልን ምርመራ ይመረመራል፡፡»

وَيَنقَلِبُ إِلَىٰ أَهْلِهِ مَسْرُورًا [٨٤:٩]

«ወደ ቤተሰቦቹም ተደሳች ኾኖ ይመለሳል፡፡»

8. **የሲራጥን ድልድይ ማለፍ እንዳለ ማመን፡፡ ይህ ድልድይ በጀ ሀነም ላይ የተዘረጋው ሲሆን ከፀጉር የቀጠነ እና ከሰይፍ የሳለ ነው፡፡ ታዲያ ሰዎች እንደየስራች ደረጃ ያልፉታል፡፡**

   **አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

وَإِن مِّنكُمْ إِلَّا وَارِدُهَا ۚ كَانَ عَلَىٰ رَبِّكَ حَتْمًا مَّقْضِيًّا [١٩:٧١]

«ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም፡፡ (መውረዱም) ጌታህ የፈረደው ግዴታ ነው፡፡ »

ثُمَّ نُنَجِّي الَّذِينَ اتَّقَوا وَّنَذَرُ الظَّالِمِينَ فِيهَا جِثِيًّا [١٩:٧٢]

«ከዚያም እነዚያን የተጠነቀቁትን እናድናለን፡፡ አመጸኞቹንም የተንበረከኩ ኾነው በውስጧ እንተዋቸዋለን፡፡»

9. **ዘውታሪ በሆነው አለም ላይ በጀነት ወይም በእሳት እንደምንመነዳ ማመን፡፡**

   **አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-**

إِنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا مِنْ أَهْلِ الْكِتَابِ وَالْمُشْرِكِينَ فِي نَارِ جَهَنَّمَ خَالِدِينَ فِيهَا ۚ أُولَٰئِكَ

هُمْ شَرُّ الْبَرِيَّةِ [٩٨:٦]

«እነዚያ ከመጽሐፉ ሰዎች የካዱት፣ አጋሪዎቹም በገሀነም እሳት ውስጥ ናቸው፤ በውስጧ ዘውታሪዎች ሲኾኑ እነዚያ እነርሱ ከፍጥረት ሁሉ ከፉ ናቸው፡፡»

إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ أُولَٰئِكَ هُمْ خَيْرُ الْبَرِيَّةِ [٩٨:٧]

«እነዚያ ያመኑትና መልካሞችንም የሠሩት፣ እነዚያ እነርሱ ከፍጥረት ሁሉ በላጭ ናቸው፡፡ »

جَزَاؤُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ جَنَّاتُ عَدْنٍ تَجْرِي مِن تَحْتِهَا الْأَنْهَارُ خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا ۖ رَّضِيَ اللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُوا عَنْهُ ۚ ذَٰلِكَ لِمَنْ خَشِيَ رَبَّهُ [٩٨:٨]

«በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው የመኖሪያ ገነቶች ነው፡፡ በውስጣቸው ዘለዓለም ዘውታሪዎች ሲኾኑ (ይገቡባቸወል)፡፡ አላህ ከእነርሱ ወደደ፡፡ ከእርሱም ወደዱ፡፡ ይህ ጌታውን ለፈራ ሰው ነው፡፡»

ከዚህም ውጪ ያሉትን ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የነገሩንን ሁሉ አካትቶ ይይዛል፡፡

## <u>በቀዳ እና በቀድር ማመን</u>

ይህ አላህ (ሰ.ወ) ማንኛውንም ነገር ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ እንደሚያውቅ ከተከሰተ በኋላም ምን እንደሚሆን የሚያውቅ ጌታ መሆኑን ማመን ነው፡፡ በመቀጠልም አላህ በእውቀቱ እና በሀይሉ እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَخَلَقَ كُلَّ شَيْءٍ فَقَدَّرَهُ تَقْدِيرًا [٢٥:٢]

«ነገሩንም ሁሉ የፈጠረና በትክክልም ያዘጋጀው ነው፡፡»

ሁሉም ተከስቶ ያለፈ ነገር? እየተከሰተ ያለም ነገር ይሁን ወደፊት የሚከሰት ነገር በአላህ እውቀት ስር ናቸውው፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- “ለሁሉም ነገር እውነተኛ ደረጃ አለው፡፡ አንድ ባሪያ ያጋጠመው ነገር ሊያመልጠው እንደማይችል፣ ያመለጠው ነገረ ደግሞ ሊያጋጥመው እንደማይችል እስካላወቀ ድረስ የአማንን እውነተኛ ደረጃ አይደርስም፡፡” (መስነድ ኢማሙ አህመድ)

⇒ በዚህ መሠረት ማመን የፍላጎትን ለማግኘት ከመልፋት አያግድም፡፡ ልጅ እንዲኖረው የፈለገ ሰው ልጅ ለማግኘት መደረግ ያለበትን ነገር ማድረግ ግድ ይለዋል፡፡ እሱም ሚስት ማግባት

ነው፡፡ መስራት ያለበትን ነገር ሁሉ ከሠራ በኋላ የሚፈልገውን ነገር ሊያገኝም ሆነ ላያገኝ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የፈለገውን ነገር እንዲያገኝ የሚወስነው ልፋቱ እና ጥሩ ብቻ ሳይሆን የአላህ (ሰ.ወ) ይሁንታ ሲታከልበት የግድ ስለሆነ ነው፡፡ ውጤቱ ብቻ ሳይሆን ራሱ የምንሰራው ሰበብ እና የምንፈለፋው ልፋት በአላህ ቅድመ ውሳኔ ስር ነው፡፡ ለዚህ ነው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሀቦቹ "አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ እራሳችንን ለማዳን የምንጠቀማቸው የቁርአን አንቀፆች፣ --------------አልያም መድሀኒቶች የአላህን ውሳኔ የመቀልበስ አቅም አላቸውን? በማለት ጠይቋቸው፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "እነሱ እራሳቸው የአላህ ውሳኔ ናቸው፡፡" አሉ (ቡኻሪና ሙስሊም)

ረሀብ፣ ጥማት፣ ብርድ ሁሉ የአላህ ቅጽር ሲሆኑ ሰዎች ይህንን ለማስወገድ ለርሀባቸው ምግብ ለጥማታች መጠጥ ለብርዳቸው ደግሞ ሙቀትን ይፈልጋሉ፡፡ አላህ የወሰነባቸውን ርሀብ፣ ጥማት እና ብርድ አላህ በወሰነላቸው ምግብ፣ መጠጥ እና ሙቀት ይከላከላሉ፡፡

በቀደር ማመን ብዙ ሰው እንደሚያስበው ሥራን ፈትቶ በመቀመት ውሳኔን መጠበቅ አይደለም፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሰው መጥቶ "ግመሌን ልልቀቃትና በአላህ ልመካ ወይ?" ብሎ ሲጠይቃቸው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "እሰራትና ተመካ" ነበር ብለው የመለሱለት፡፡ (ሶኒህ ኢብኑ ሂባን)

## <u>ስለ እስልምና ምን አሉ?</u>

በርናርድ ሾው ኢስላም ከ100 ዓመት በኋላ በሚለው መፅሀፍ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- "በዚህ ዓለም ያለ ሰው ሁሉ እስልምናን ይቀበላል፡፡ በግልፅ በትክክለኛ ስሙ ባይቀበሉት እንኳ በሌላ መልኩ ይቀበሉታል፡፡ ምዕራባዊያን እስልምናን የሚቀበሉት ቀን ይመጣል፡፡ በእርግጥም እስልምና ላይ በውሸት የተሞሉ መፅሀፎችን እያነበበ ምዕተ ዓመታቶችን አልፈዋል፡፡ ስሙሐመድ ብዙ መፅሀፎች ተፅፈዋል ነገር ግን በእንግሊዝ አማካኝነት እንዳይታተሙ እገዳ ላይ ናቸው፡፡"

እንዲሁም እንዲህ ይላል፡- "እስልምና የሌላ ሀይማኖቶችን በጎ ነገር በሙሉ አጠቃሎ ይዟል፡፡ ሌሎች ሀይማኖቶች ግን የእስልምናን ጥቅም አሟልተው አልያዙም፡፡"

## <u>የኢስላም ነብይ ማን ናቸው፡</u>

ሙሐመድ ቢን አብደላህ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሆኑ የመልዕክተኞች መጨረሻ እና መደምደሚያ ናቸው፡ አላህ (ሰ.ወ) የላከው ለአረብ ብቻ ሳይሆን ለሰው ዘር በሙሉ ነው፡፡ አላህ (ሰ.ወ) የላከቸው የሰው ልጅ ደስታ እንዲያገኝ፣ ጥሩውን እና እውነተኛውን መንገድ እንዲያመላክቱት እንዲሁም ከመጥፎ እና ከውሸት መንገድ እንዲስጠነቅቁት ነው፡፡ ህይወታች በሙሉ በእውነተኝነት እና በአደራ ጠባቂነት የተሞላ ነበር፡፡ ውሸት፣ ማታለል እና ክህደት በህይወት ታሪካቸው ውስጥ የለም፡፡ ህዝቦቻቸውም ታማኙ በሚል ቅፅል ስም ያውቋቸው ነበርር፡ ሰዎች አደራቸውን በሙሉ አመኔታ

እሳቸው ዘንድ ያኖሩ ነበር፡፡ እውነተኛም በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ የሚናገሩት እና የሚያወሩት ነገር ሁሉ እውነት ነበር፡፡ 40 ዓመት ሲሞላቸው ራዕይ ይወርድላቸው ጀመር፡፡ በመካ ውስጥ ለ13 ዓመታት ያህል ሰዎችን ወደ ተውሒድ እና ለጣዖታት መገዛትን ወደመተው ሲጣሩ ቆዩ፡፡ በመቀጠልም ወደ መዲና ተሰድደው የመዲና ሰዎችን ወደ እስልምና ተጣርተው እንዲቀበሉ አደረጉ፡፡ የቀረው ሀይማኖታዊ ህግጋት በመዲና ላይ እንዳሉ ወርዶ ህግጋቱ ተሟላ፡፡ 8 ዓመት በመዲና እንደቆዩ መካን መቆጣጠር ቻሉ፡፡ እድሜያቸው 63 ዓመት ሲሞላ ቁርአን፣ እና የሀይማኖቱ ህግጋቶች ተሟልተው አረብ በሙሉ ወደ እስልምና ገብቶ ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል፡፡

## ስለ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ምን አሉ?

- ✓ ጀርመናዊው ተጣሚ ጎታ እንዲህ ብሏል፦
  "በታሪክ ምህዳር ላይ የሰው ዘር በሙሉ ቁንጮ የሆነውን ሰው ፈለኩኝ፡፡ እርሱም የአረቡ ነብይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.) ሁነው አገኘኋቸው፡፡"
- ✓ ዎውል ዲውራንት The Story of Civilization በሚለው መፅሀፍ ውስጥ እንዲህ ይላል፦ "ስለ አንድ ሰው ታላቅነት የሚለካው በሰዎች ዘንድ ባሳደር ተፅዕኖ የምንወስን ከሆነ የኢስላም ነብዩ የታላላቆች ሁሉ ታላቅ ነው፡፡ ---------ዘረኝነትን እና አስመሳይነትን አስወግዷል፡፡ ከክርስትናም፣ ከአይሁድም ሆነ እዛ አገር ከነበሩ ሌላ ሀይማኖቶች በላይ ግልፅ፣ ገር እና ጠንካራ የሆነ ሀይማኖት አቋቁሟል፡፡ እስከ ዛሬ ድረስም የሱ ሀይማኖት አስተማማኝ በሆነ ጥንካሬ ላይ ይገኛል፡፡

## ቁርአን ምንድን ነው?

ቁርአን በጅብሪል አማካኝነት ወደ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የወረዳ የአላህ (ሰ.ወ) ንግግር ነው፡፡ ቁርአን ከሱ በፊት ከነበሩት ሰማያዊ መፅሀፎች በሚከተሉት ነጥቦች ይለያል፡፡

1. የመጨረሻ ሰማዊ መፅሀፍ በመሆኑ፡፡ ለዚህም ሲባል አላህ (ሰ.ወ) የመጨረሻው ቀን እስኪደርስ ድረስ እንደሚጠብቀው ቃል ገብቷል፡፡ ወደነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከመጣ ጀምሮ እስካለበንበት ግዜ ድረስ በመጨመርም ሆነ በመቀነስ ብረዛ አልተደረገበትም፡፡
   አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፦

   إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ [١٠:٩]

«እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡»

2. እሱን ማንበብ ከአምልኮ ተግባራት ውስጥ ነው፡፡

ከመበረዝ ለመጠበቁ ዋነኛ ምክንያትም ይህ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- “አአላህ መጽሀፍ ውስት አንድን ፊደል ያነበበ ሰው ምንዳ አለው። ምንዳውም በ10 ይባዛል። አለፍ ላምሚም አንድ ፊደል አይደለም።ነገር ግን አሊፍ አንድ ፊደል ላም አንድ ፊደል እንዲሁም ሚም አንድ ፊደል ናቸውለለ” ።

- በልብ ውስጥ ሽምድዶ መያዝም በአምልኮ ተግባራት ውስጥ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- “በልብ ውስጥ ምንም የቁርአን አንቀጽ የሌለው ሰው ልክ እንደወና ቤት ነው።”
  ለቁርአን ትኩረት መስጠት እና ማስተማርም ከአምልኮ ተግባራት ውስጥ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- “ከእናንተ ውስጥ በላቹ ቁርአንን ተምሮ ያስተማረ ነው።።”

3. ቁርአን የማህበራዊ ህይወትን የሚመለከቱ እና የደስታ ምንጭ የሚሆኑ ህግጋቶችን በሙሉ አጠቃሎ ይዟል። አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይሏል፡-

وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ الْكِتَابَ تِبْيَانًا لِّكُلِّ شَيْءٍ

«መጽሐፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ፣ መሪም፣ እዝነትም፣ ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው፡፡»

4. አላህ (ሰ.ወ) ያወረደው ለሰው ልጅ ባጠቃላይ የደስታ እና የሰላም ምንጭ እንዲሆን ዘንድ ነው፡ ፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

الر ۚ كِتَابٌ أَنزَلْنَاهُ إِلَيْكَ لِتُخْرِجَ النَّاسَ مِنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ بِإِذْنِ رَبِّهِمْ

«አ.ለ.ረ (አሊፍ ላም ራ፤ ይህ ቁርአን) ሰዎችን በጌታቸው ፈቃድ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን አሸናፊ ምስጉን ወደ ኾነው፡፡»

## <u>ስለ ቁርዓን ምን አሉ?</u>

W.Durrant “The story of Civilization” በሚለው መፅሀፍ ውስጥ እንዲህ ይላል “ቁርዓን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች አዕምሮ ውስጥ ተጣብቆ ስነምግባራቸውን እየቀረጸ፣ አስተሳሰባቸውን እየሞረደ 14 ምዕተ ዓታትን መቆየት ችሏል። ሙስሊሞችን በስነምግባር በማነፅ እና በእውቀት በማስፋፋት ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። የአንድነት እና የማህበራዊ ስርአትን በመሀላቸው መትከል ችሏል። ትክክለኛ አስተሳሰቦችን እንዲከተሉም ገፋፍቷቸዋል። አእምሮዋቸው ከጨለማ፣ ከጭፍን አስተሳሰብ፣ ከድርቅና ከመጥፎ ባህል ነፃ አውጠቷቸዋል። በተዋረዱ ልቦች ውስጥ ስለክብርና አሸናፊነት ዘርቷል። ነጮች በሚኖሩበት ቦታ ሁሉ የማታገኘውን ከስሜታዊነት የራቀ አስተሳሰብን የሙስሊሞች ልብ ላይ መትከል ችሏል።

## <u>እውቀት በእስልምና ያለው ቦታ</u>

የእስልምና ሀይማኖት እውቀት መቅሰምን በጣም አበረታቷል፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

قُلْ هَلْ يَسْتَوِي الَّذِينَ يَعْلَمُونَ وَالَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ ۗ

«እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ የማያውቁ ይስተካከላሉን?» በላቸው፡፡»

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ያላል፡-

يَرْفَعِ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا مِنكُمْ وَالَّذِينَ أُوتُوا الْعِلْمَ دَرَجَاتٍ

«አላህ ከናንተ እነዚያን ያመኑትንና እነዚያንም ዕውቀትን የተሰጡትን በደረጃዎች ከፍ ያደርጋል፡፡»

እውቀት----------------እንደማይገባን አላህ ነግሮናል፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ብሏል፡፡

እስልምና አዋቂ የሆነች ሰው ታላቅ ቦታ ሰጥቶቷል፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- “ታላላቆቹን የማያከብር ለታናናሾቹ የማያዝን፣ ለአዋቂ ሰዎች ተገቢወን ክብር የማይሰጥ ሰው ከኔ አይደለም፡፡” ሙስነድ ኢማም አህመድ፡፡

እስልምና እውቀትን መፈለግ፣ መማር እና ማስተማር ወደጀነት የሚያደርስ መንገድ መሆኑን ያስተምራል፡፡

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- እውቀትን ፍለጋ ጉዞ የወጣ ሰው አላህ የጀነትን መንገድ ያገራለታል፡፡ መላዕክቶችም እውቀት ለሚፈልግ ሰው ክንፎቿን ዝቅ ታደርጋለች፡፡ በሰማይ እና በምድር ውስጥ ያሉ በባህር ውስጥ ያለ ዓሳ ሳይቀር ለአዋቂ ሰው ምህረትን ይጠይቁለታል፡፡ አዋቂ ሰው አላህን ከሚገዛ ሰው በላይ ያለው ብልጫ ልክ ሙሉ ጨረቃ ከሌላ ኮከቦች ላይ ላትን ብልጫ ነው፡፡ አዋቂዎች የነብያቶች ወራሽ ናቸው፡፡ ነብያቶች ዲናርን ወይም ዲርሀምን አያወርሱም፡፡ እነሱ የሚያወርሱት እውቀትን ሲሆን እውቀትን ያገኘ ሰው ትልቅ እጣ አግኝቷል፡፡ (ሰሂህ ኢብኑ ሂባን)

## <u>ገንዘብ በኢስልማና መነፅር</u>

በእስልምና መነፅር ገንዘብ በባሪያዎች ዘንድ በአደራ መልክ የተቀመጠ ስለዚህ በተፈቀዱ ነገራቶች ላይ እና በተፈቀዱ መንገዶች ማዋል አለብን፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- በመጪው አለም ማንም ሰው እድሜውን በምን እንዳሳለፈውና ሰውነቱ በምን እንዳለቀ ሳይጠየቅ እግሩ ንቅንቅ አይልም፡፡እስልምና የሰው ልጅ የራሱንና የቤተሰቡን ቀለብ እንዲችል እና በሚያጋጥሙት ጉዳይ

ላይ እንዲያግዘው ሀብት ለማግኘት መስራት እና መልፋት እንዳለበት ያበረታታል፡፡ በበጎ ስራዎች ላይ ሲያውለውም ምንዳን ያገኛል፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- ጠንካራ አማኝ ከደካማ አማኝ አላህ ዘንድ በላጭ እና የተወደደ ነው፡፡ ምንም እንኳን ሁለቱም ላይ በጎ ጎን ቢኖርም በሚጠቅምህ ነገር ላይ በርታ፡፡ ከዛም በአላህ ታገዝ፡፡ ሰነፍ አትሁን፡፡ የሆነ ነገር ሲያጋጥምህ እንዲህ ሰርቼ ነበር እንዲህ ሆን ነበር አትበል፡፡ ነገር ግን የአላህ ውሳኔ ነው፡፡ የሚሻውንም ፈፃሚ በል፡፡ "በነበር" የሚለው ቃል የሸይጣንን በር ይከፍታል፡፡ በሀብትህ ላይ ዘካ ከማውጣት የዘለለ ሌላ ብዙ ሀላፊነቶች አሉብህ፡፡ ገንዘብ ማውጣት ያለብህ በዚህ ወይም በመጪው አለም ጥቅም ሊሰጥህ በሚችል ጉዳይ ብቻ ነው፡፡

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ያላል፡-

وَابْتَغِ فِيمَا آتَاكَ اللَّهُ الدَّارَ الْآخِرَةَ ۖ وَلَا تَنسَ نَصِيبَكَ مِنَ الدُّنْيَا ۖ وَأَحْسِن كَمَا أَحْسَنَ اللَّهُ إِلَيْكَ ۖ وَلَا تَبْغِ الْفَسَادَ فِي الْأَرْضِ ۖ

«አላህም በሰጠህ ሀብት የመጨረሻይቱን አገር ፈልግ፡፡ ከቅርቢቱም ዓለም ፋንታህን አትርሳ፡፡ አላህም ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ (ለሰዎች) መልካምን አድርግ፡፡ በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፡፡»

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላል፡- "ጥሩ ገንዘብ ጥሩ ሰው ጋር ሲሆን ምንኛ ያምራል"

እስልምና ገንዘብን ጥቅም በሌለው ነገር ላይ ማባከንን አጥብቆ ይከለክላል፡፡

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ያልል፡-

وَلَا تُبَذِّرْ تَبْذِيرًا [١٧:٢٦] ማባከንንም አታባክን፡፡

إِنَّ الْمُبَذِّرِينَ كَانُوا إِخْوَانَ الشَّيَاطِينِ ۖ وَكَانَ الشَّيْطَانُ لِرَبِّهِ كَفُورًا [١٧:٢٧]

አባካኞች የሰይጣናት ወንድሞች ናቸውና፡፡ ሰይጣንም ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው፡፡

## መደምደሚያ:-

በዚህች አነስተኛ መፅሀፍ የተከበሩ አንባቢዎች እንዳይሰለቹ በመፈራት በተቻለኝ አቅም ዝርዝር ጉዳችን በመት ለማሳጠር ሞክሬያለሁ። እስልምናን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች በተለይም የሀይማኖቱ ተከታይ ላልሆኑና በአሳሳች መረጃዎች ለተታለሉ ሰዎች ጮራ ፈንጣቂ እና አስተዋዋቂ እንዲሆን ምኞቴ ነው። ዘላቂ ደስታ እና መዳን የሚገኘው እስልምናን በመተግበር መሆኑን አላወቁም። እናም ለእነዚህ ሰዎች የማስተላልፈው መልዕክት ቢኖር በሌላ ሰው ጭንቅላት እንዳያስቡ እና በሌሎች ሰዎች ምኞት የራሳቸውን መውደቂያ እንዳያበላሹ ነው።

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል:

وَإِن تُطِعْ أَكْثَرَ مَن فِي الْأَرْضِ يُضِلُّوكَ عَن سَبِيلِ اللَّهِ ۚ

‹‹ በምድርም ካሉት ሰዎች አብዛኞቹን ብትከተል ከአላህ መንገድ ያሳስቱሃል።››

አሁንም የምትከተሏቸው ሰዎች በመጪው አለም በመጀመሪ የሚሸሿቹህ እነርሱ ናቸው። አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል:-

إِذْ تَبَرَّأَ الَّذِينَ اتُّبِعُوا مِنَ الَّذِينَ اتَّبَعُوا وَرَأَوُا الْعَذَابَ وَتَقَطَّعَتْ بِهِمُ الْأَسْبَابُ [٢:١٦٦]

‹‹ እነዚያ አስከታዮቹ ቅጣትን ያዩ ሲኾኑ ከእነዚያ ከተከታዮች በተጥራሩና በእነርሱም (መካከል) ምክንያቶች በተቆረጡ ጊዜ (የሚኾኑትን ባወቁ ኖሮ በተጸጸቱ ነበር)።››

በአስተሳሰባችሁ ጥገኛ ላለመሆን ጣሩ። ነገራቶችን አመዛዝኖ ለመረዳት ፍላጎት ይኑራችሁ። አላህ በሰጣችሁ አዕምሮ እውነትን ከውሸት ለመለየት ልፋት አድርጉ። አላህ በሰጣችሁ አዕምሮ ጭፍን ተከታይነትን፣ ጠርዘኝነትንና ሀይማኖትን ከሩቅ ለመራቅ ሞክሩ።

አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል:-

وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ تَعَالَوْا إِلَىٰ مَا أَنزَلَ اللَّهُ وَإِلَى الرَّسُولِ قَالُوا حَسْبُنَا مَا وَجَدْنَا عَلَيْهِ آبَاءَنَا ۚ

أَوَلَوْ كَانَ آبَاؤُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ شَيْئًا وَلَا يَهْتَدُونَ [٥:١٠٤]

‹‹ ለእነርሱም አላህ ወደ አወረደውና ወደ መልክተኛው ኑ በተባሉ ጊዜ «አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበት ነገር ይበቃናል» ይላሉ፡፡ አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና የማይመሩ ቢኾኑም= (ይኸንን ማለት ይበቃቸዋልን=)››

ይህንን ለሚፈልግ ሰው በሩ ክፍት መንገዱም ገር ነው፡፡ ነገር ግን በተቻለ መጠን ትክክለኛውን የኢስላም ስዕል በሚያሳዩ መንገዶች ይሁን፡፡ የእስልምና ተከታይ ነን ያለ ሰው ሁሉ ሙስሊም አይደለም፡፡ በእስልምና ሽፋን የሚፅፉ ሰዎች ሁሉ ትክክለኛውን እስልምና የሚወክሉ አይደሉም፡፡ ስለዚህ በተቻለ መጠን እስልምናን ከታማኝ ምንጮች ለመቅሰም ጥረት አድርጉ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደህ ይላሉ፡- "አይሁዶች ወደ 71 ስብሰቦች ተለያይተዋል፡፡ ክርስቲያኖች ወደ 72 ስብስቦች ተለያይተዋል፡፡ የኔ ህዝቦችም ወደ 73 ስብስቦች ይለያያሉ፡፡ ከአንዱ በቀር ሁሉም የእሳት ናቸው፡፡" ሰሀቦችም "እሱ ማን ነው?" ብለው ጠየቁ፡፡ "እኔ እና ባልደረቦቼ ባለንበት መንገድ ላይ ያለ ነው፡፡" ብለው መለሱ፡፡

ስለ እስልምና ይበልጥ ማወቅ የፈለገ ሰው ከዚህ መፅሀፍ ስር ከተዘረዘሩት እስላማዊ ድርጅቶች ውስጥ አንዱን ማግኘት ይችላል፡፡ አላህ ይበልጥ አዋቂ እና ጥበበና ነው፡፡

በነብችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ሰላትና ሰላም ይስፈን፡፡